(قُلْ هَٰذِهِۦ سَبِيلِىٓ أَدْعُوٓا۟ إِلَى ٱللَّهِ ۚ عَلَىٰ بَصِيرَةٍ أَنَا۠ وَمَنِ ٱتَّبَعَنِى ۖ وَسُبْحَٰنَ ٱللَّهِ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ)

[سورة يوسف 108]

ሙሐመድ ሆይ! እንዲህ በላቸው፤ "መንገዴ ይህች ናት!
በግልጽ ማስረጃ ላይ ሆኜ ወደ አላህ እጠራለሁ፡፡
የተከተለኝም ሰው እንዲሁ በማስረጃ ይጣራል።
ጥራትም ለአላህ ይገባው፤ እኔም ከአጋሪዎቹ አይደለሁም"
(ዩሱፍ 108)

www.sarhaan.net
www.attasseel-alelmi.com

ለሁሉም ሙስሊም አሳሳቢ የሆኑ ትምህርቶች ማብራሪያ

ሸይኽ ሀይሠም ሰርሐን

مترجم باللغة الأمهرية
ወደ አማርኛ ቋንቋ የተተረጎመ

شرح الدروس المهمة لعامة الأمة

# ለሁሉም ሙስሊም አሳሳቢ የሆኑ ትምህርቶች ማብራሪያ


تأليف فضيلة الشيخ:
عبدالعزيز بن عبدالله بن باز
شرح فضيلة الشيخ:
هيثم بن محمد جميل سرحان

ፀሀፊ:
ሸይኽ ዐብዱልዐዚዝ ቢን ባዝ
ትንታኔ:
በሸይኽ ሀይሠም ሰርሐን
ትርጉም እና ህትመት:
ኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር

# የ "አሳሳቢ ትምህርቶች ለብዙሃኑ ህዝብ" ማብራሪያ

በክቡር ሸይኽ:

**ኢማም ዓብደል ዓዚዝ ቢን ዓብደላህ ቢን ባዝ**

አላህ ይዘንለት መኖሪያውንም ያስፋለትና

ዝግጅት በክቡር ሸይኽ:

**ሀይሠም ቢን ሙሓመድ ጀሚል ሰርሓን**

በክቡር መስጅድ ነበውይ -ነባር- አስተማሪና የታእሲለል ዒልምይ ድረ ገፅ ሹም

http://attasseel-alelmi.com

ለሱም ለወላጆቹም ኪታቡ እንዲወጣ እገዛ ላደረገም ሁሉ አላህ መሃርታውን ይለግስ

**ይህች እትም ለአላህ ሲባል ወቅፍ የተደረገች ነች**

**በፋጢማህ ቢንት ጀይላልይ ቢን ፋረይሓህ ልገሳ የታተመ – አላህ መሃርታውን ይለግሳት በሰፊው ጀነቱም ያስገባትና-**

የመጀመሪያ እትም

መብቱ በህግ የተጠበቀ

ምናልባት ሸይኹ ካረጋገጡለት በኋላ በነፃ ለማደል ማተም ወይም መተርጎም ለፈለገ ካልሆነ በቀር

ያግኙን:

islamtorrent@gmail.com

በመረጃ ሚኒስቴር ፍቃድ

# የሸይኹ መግቢያ ማብራሪያ

ሸይኽ ኢማም ዓብደል ዓዚዝ ቢን ዓብደላህ አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ይላሉ፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው
ምስጋና ባጠቃላይ ለአላህ፤ ፍፃሜ ለጥንቁቆች፤ የአላህ ሶለዋትና ሰላም በነብያችን ሙሐመድ፣
በተከታዮቻቸውና በባልደረቦቻቸውም ላይ ይሁን።
በመቀጠል፡
ይህች ብዙሃኑ ከኢስላም ማወቁ ግዴታ የሚሆንበትን የምትገልፅ አጠር ያለች ንግግር ነች። ስሟንም "አ-ድ-ዱሩሱ-ል- ሙሂማህ ሊዓሙቲ ል ኡማህ" ብየ ሰይሜያታለሁ። *(አሳሳቢ ትምህርቶች ለብዙሃኑ ህዝብ)።*
በሷ ሙስሊሞችን እንዲጠቅም፤ ከኔም ሊቀበለኝ ዘንድ አላህን እለምነዋለሁ እርሱ ቸርና ለጋስ ነውና።
ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ዓብደላህ ቢን ባዝ

## ለምንድን ነው "አሳሳቢ ትምህርቶች"ን የምንማማረው?

ምክንያቱም ሸይኹም አላህ ይዘንላቸውና እንዳሏት አሳሳቢ ስለሆነች፤ ዑለሞችም የሚመከሩባት ስለሆነች።
እዚህላይ የሆነ ሰው "አዎ በርግጥ አሳሳቢ ነች፤ ነገር ግን ለብዙሃኑ ህዝብ ነው። እኔ ደሞ የበቃሁ ተማሪ(ጧሊቡ ዒልም) እንደመሆኔ ደረጃየ ከብዙሃኑ ህዝብ ከፍ ያለ ነው።" ቢልስ
ምላሹ፡ በውስጧ ካለው (አውጣጥተን) እንጠይቀዋለን፤ መልሱን ካላገኘ ብዙሃኑ ህዝብ ከሱ የተሻለ ነው፤ ዒልም ፈላጊ ደግሞ መተናነስ፣ በዒልም ላይም ሆነ በዓሊሞች ላይ አለመኩራራት፣ በእውቀታቸው ሰሪ በሆኑ ዑለሞችም አካሄድ ሊጓዝ ነው የሚገባው።
በሶሒሕ ቡኻሪይ፡ ሙጃሂድ "(እልፍ ያለ) ሓያእ ያለውና ኩራተኛ እውቀትን አያገኝም" ብለዋል።

## "አሳሳቢ ትምህርቶች" በምን ዙሪያ የምታጠነጥን ነች?

1. ደጋግ ቀደምቶች ቁርአን ከመቅራት፣ ከመሓፈዝ፣ ከማስተንተኑና ከመተግበሩ በኩል የነበራቸው አካሄድ
2. ስለኢስላም፣ ስለኢማን፣ ስለኢሕሳን፣ ስለተውሒድና ስለሽርክ አይነቶች ማብራሪያ
3. ስለሶላት ማብራሪያ
4. ስለውዱእ ማብራሪያ
5. በተደነገገ ስነምግባር ስለማሸብረቅና በኢስላማዊ ስነስርዓት ስርዓትን ስለመያዝ
6. ከሽርክና ከአመፅ አይነቶች ስለማስጠንቀቅ
7. ሟችን ስለመሸፈኑት፣ እሱ ላይ ስለመስገድና እሱን ስለመቅበር

# የመጀመሪያው ትምህርት

**ዑለሞች ለምንድን ነው ኪታቦቻቸውን በቢስሚላህ የሚጀምሩት?**

- በታላቁ ኪታብ፣ በነብያቶችና ብመመልዕክተኞች ከመመራት አንፃር
- “ጣጣ ኖሮበት በቢስሚላህ ያልተጀመረ ሁሉ የተቆረጠ ነው” የሚለውን ሓዲሥ ትርጉም ከመስጠት አንፃር፤ ዶዒፍ ቢሆንም
- አላህ ይዘንላቸውና ቀደምት ዑለሞን ከመከተል አንፃር
- በአላህ ስም በመጀመር በሚገኘው በረካ ከመቀናት አንፃር

**ሱረቱ -ል- ፋቲሓ እና አጫጭር ሱራዎች**

ሱረቱ -ል- ፋቲሓ እና ከአጫጭር ሱራዎች የተቻለውን ያክል፤ ከሱረቱ-ል ዘልዘላህ እስከ ሱረቱ-ን-ናስ አቀራሩን በማስያዝና በማስተካከል፤ መረዳቱ ግድ ለሚለውም ደሞ ማብራሪያ።

**ማብራሪያ**

ልክ የቀደምቶች አካሄድ እንደነበረው አላህ ይዘንለትና የኢብኑ ሰዕዲን ከመሰሉ ኣጫጭር የተፍሲር ኪታቦች ማብራሪያቸውን ከመቅራትም ጋ አስር አንቀፆችን በየቀኑ መሓፊዝ ይገባል።

**አንድ የዒልም ፈላጊ የሆነ ሰው በየትኛው የተፍሲር ኪታብ ይጀምር?**

አንድ እውቀት ፈላጊ የሆነ ሰው አላህ መሃርታውን ይለግሰውና በሸይኽ ዓብዱራሕማን ሰዕዲ “ተይሲሩ-ል ከሪሙ ራሕማን ፊ ተፍሲሪ ከላሚ-ል መናን” ቢጀምር ይመከራል።

**ለምን?**

- ዑለሞች በሱ ከሰጡት ምክርና ሃሳብ አንፃር
- አጠር ያለ እንደመሆኑ ጀማሪ ሊቀራው ተመራጭ ነው።
- አገላለፁ አጠር ያለ፣ ቀላል፣ ግልፅና ድብስብስነት ስለሌለበት
- በአላህ ፍቃድ በቁርአኑ በመስራት ላይ ስለሚያግዝ
- አላህ ይዘንለትና ሸይኹ በተውሒድ ላይ መሰረት ስለሚያስይዝ

## የመጀመሪያው ትምህርት ማብራሪያ

**ሰዎች ከቁርአን ጋ ባላቸው መስተጋብር ስንት አይነት ናቸው?**

ከቁርአን አንፃር ሰዎች ሁለት ጠርዝ ላይና ሚዛናዊ አቋም አላቸው።

**ለዘብተኛ:**

ቁርአንን የተወ ክፍል ሲሆን ፤ የሚገለፅበትም በ:

- ማንበቡን በመተው
- መሓፈዙን በመተው
- ማስተንተኑን በመተው
- መስራቱን በመተው
- መተካከሙን በመተው

**ድንበር የሚያልፍ:**

ማስተንተንም ሆነ መተግበር ሳይኖረው የሚያነብና የሚሓፍዝ ክፍል

**ሚዛናዊ:**

በማንበቡም ሆነ በሒፍዙ ላይ ተጠምዶ፤ እያስተነተነ ለተግባሩም በአላህ የሚታገዝ ክፍል

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል: { መልክተኛውም «ጌታዬ ሆይ! ሕዝቦቼ ይህንን ቁርኣን የተተወ ነገር አድርገው ያዙት» አለ።} (አል-ፉርቃን 30) የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል "ከዚህ መሰረት" ማለትም (በሓዲሡ ከተወሳው ግለሰብ) ከዝርያውና ከቤተሰቡ "ቁርአን እየቀሩ ከጉሮሯቸው የማይወርድ፤ የኢስላም ጓዶችን እየገደሉ የጣኦት ጓዶችን የሚተው፤ ከውርወራው ብርታት አንፃር የተወረወረ ቀስት ከተወረወረበት እንደሚሾልከው እነርሱም በዛ መልኩ ከኢስላም የሾለኩ ናቸው፤ እኔ ባገኛቸው ኖሮ ልክ የዓድ ህዝቦች እንደጠፉት ነበር የማጠፋቸው።"

**ከ የእውቁ ዓብዱራሕማን አስ-ሰዕዲይ አላህ ይዘንትለና "*ተይሲር አል-ከሪሙ-ር-ራሕማን ፊ ተፍሲሪ ከላም አል-መናን*" የተወሰኑ ቅንጫቢዎችና ጥያቄዎች**

**[ የሱረቱል ፋቲሓ ተፍሲር፤ ሱራዋ መክይ ነች ]**

{**መክይ:** ሲባል ነብዩ ﷺ ከመካ ወደ መዲና ሂጅራ ከማድረጋቸው በፊት የወረዱ ሱራዎችን ማለት ሲሆን **መደንይ:** ደግሞ ከ የነብዩ ﷺ ከመካ ወደ መዲና መሰደት በኋላ የወረዱ ሱራዎችን ማለት ነው።}

(**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (1) ምስጋና ባጠቃላይ ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው። (2) እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ (3) የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው። (4) አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን። (5) ቀጥተኛውን መንገድ ምራን። (6) የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ (ምራን፤ በሉ)። (7)** )

---

**(1)** ማለትም: በመላው ከፍ ያለው አሏህ ስም ሁሉ እጀምራለሁ። ይህም "ኢስም" የሚለው ቃል በዓረብኛ ቋንቋው መደበኛ ነጠላ ቃል (ኢስሙን ሙፍረድ) በመሆኑ እያንዳንዱን የአሏህን መልካም ስም ሁሉ ያጠቃልላል። "**አሏህ**" በአምልኮ ሊነጠል የሚገባው ተመላኪው አምላክ ነው። ይህም ካለው የአምላክነት መገለጫ ባህሪ አንፃር ነው። ሁሉም ደሞ ምሉእ የሆኑ ባህሪያት ናቸው። "**እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ**" እነኝህ ህይወት ያለውንም ጭምር ሁሉ ያካለለች የሆነችዋ ባለ ሰፊና ታላቅ እዝነት ባለቤት ወደሆነው ከፍያለው አሏህ አዛኝነት የሚጠቁሙ ሁለት ስያሜዎች ናቸው።ይህችን እዝነቱን ለነዚያ ነብያቶቹንና መልዕክተኞቹን ለሚከተሉት ጥንቁቆች ፅፏታል፤ ለነኝህ ልቅ የሆነው እዝነቱ ያላቸው ሲሆን ከነሱ ውጭ ያለው ከሷው የተወሰነ ድርሻ አላቸው።

እወቅ! በቀደምቶችና ኢማሞቻቸው ዘንድ ወጥ በሆነ መልኩ ከሚስማሙባቸው መርሆዎች መካከል በአሏህ ስምና ባህሪያት እንዲሁም ተያያዥ ህጎች ማመን ነው። ለምሳሌ “ራሕማን” መሆኑንና “ረሒም” (ሁሉን አቀፍ ርኅሩህና በጣም አዛኝ) መሆኑን ሲያምኑ እሱ የሚገለፅባት የሆነችው ከሚታዘንለት ጋ በተሳሰረችው አይነት እዝነት፤ እያንዳንዷ ፀጋ ከእዝነቱ ፋናዎች አንዷ በመሆኗም ያምናሉ። በሌሎች ስያሜዎችም እንዲሁ (መልዕክቱን ተቀብለው ያምናሉ) ማለት ነው።

አል-ዓሊም (ሁሉን አዋቂ) ስለሚለው ስያሜም የሚባለው ‘እንዲሁ ሁሉንም የሚያውቅ የእውቀት ባለቤት ነው’ ነው። “ቀዲር” (ሁሉን ቻይ) ነው ስንልም ‘እንዲሁ በሁሉም ነገር ላይ የሚችል የሆነ ቻይ ነው’ ማለት ነው።

**(2) "ምስጋና ባጠቃላይ ለአላህ ይገባው..."** ይህ በምሉእነት ባህሪያቱ፣ በችሮታ እና ፍትህ መካከል የሚሽከረከሩ በሆኑት ድርጊቶቹ አሏህን ማወደስ ነው፤ በየትኛውም መልኩ የተሟላ ውዳሴ ለሱው ነው።

(3) **"... የዓለማት ጌታ ለኾነው።"** ጌታ፡ መላው አለምን የሚንከባከብ ነው፤ ማለትም ከሱ ውጭ ያለውን ሁሉ ማለት ሲሆን ያም እነሱን የፈጠረ፣ አስፈላጊውን ትጥቅ ሁሉ ያሟላላቸው፣ ቢያጧት ህልውና የማይኖራቸው አይነት ታላላቅ ፀጋዎችን የዋለላቸው በመሆኑ ነው። እነሱ ዘንድ ያለች የትኛዋም ፀጋ ከታላቁ አሏህ ነች።
አሏህ ፍጡራኖቹን የሚንከባከበው በሁለት አይነት አኳኋን ነው: ጥቅል እና ልዩ በሆነ መልኩ።
ጥቅል የምንለው ፍጡራኖቹን መፍጠሩ፣ ሲሳይ መለገሱ፣ ዱኒያ ላይ ላላቸው ህልውና ለሚበጃቸው ነገር መምራቱ ነው።
ልዩ የምንለው ደግሞ ለወዳጆቹ ለይቶ በሚያደርግላቸው በእምነት ይንከባከባቸዋል፤ ለሷው ይገጥማቸዋል፤ የተሟሉ ያደርጋቸዋል፤ በእርሱ እና በእነርሱ መካከል ግርዶሽ ሊሆኑ የሚችሉ መሰናክሎችንና እንቅፋቶችን ይመክትላቸዋል። ተጨባጩም ለመልካሙ ሁሉ በመግጠምና ከመጥፎው ሁሉ በመጠበቅ ነው። ምናልባትም አብዛኞቹ የነብያት ዱዓዎች “ጌታዩ!” በሚል ቃል የተቆራኙበትም ሚስጥር ለዚሁ ይሆናል። የሚፈልጉት ነገር ባጠቃላይ በሱ ልዩ ጌትነት ስር ያለ ነውና። **"... የዓለማት ጌታ ለኾነው።"** የሚለው ቃሉ በመፍጠሩ፣ በማስተናበሩ፣ ፀጋን በመዋሉና ባለው የተሟላ መብቃቃት እንዲሁም አለም ሁሉ በየትኛውም መልክና ሚዛን ወደሱ ያለውን ሙሉ በሙሉ ፈላጊነት ይጠቁማል።
**(4) "የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው።"** **ባለቤት፡** የሚባለው የባለቤትነት ማንነት ያለው ሲሆን ከፋናዎቹም ማዘዝና መከልከል፣ መመንዳትና መቅጣት መቻል፤ በባለቤትነቱም ላይ በፈለገው መልኩ መሆን መቻል ከፋናዎቹ ነው። ባለቤትነቱን ታዲያ የገለፀው ከፍርዱ ቀን ጋ በማያያዝ ነው። ያም የትንሳኤ ዕለት ነው። የሰው ልጆች በመልካምም ይሁን በክፉው ስራቸው የሚመነዱበት ቀን፤ ምክንያቱም የዛን እለት የንግስናው፣ የፍትሁና የጥበቡ ሙሉነት፤ የፍጡራን ባለቤትነት መቋረጥ በተሟላ መልኩ ግልፅ የሚሆንበት ቀን ነው። ብሎም የዛን `ለት ነገስታትና እረኞች፣ ጨዋ እና ባሪያዎች እንኳ እኩል ሆነው፤ ሁሉም ለታላቅነቱ አጎብድደው፤ ለልቅናው ተናንሰው፤ ፍርዱን በመጠባበቅ፤ ምንዳውን ተስፋ አድርገው፤ ቅጣቱን ሰግተው፤ የሚጠባበቁበት ቀን ነው። ለዚህም ነው ለየት አድርጎ ያወሳው እንጅ የትንሳኤ ቀንም ይሁን የሌላው ቀን ባለቤት እርሱው ነው።
(5) **"አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን።"** የሚለው ቃሉ በአምልኮና እገዛን በመሻት እንነጥልሃለን ማለት ነው። ምክንያቱም እንደዓረብኛ ቋንቋ ስዋስዋዊ አገባቡ ድርጊት ተቀባዩ(መቅደም ያለበት)ን ማዘግየት ገደብን ነው የሚጠቁመው። ማለትም ተቆራኝቶ የመጣው ፍርድ ለተወሳው የሚሆንና ከሱ ውጭ ካለው ደግሞ የሚያወግዝ ነው። ልክ እናመክልሃለን ካንተ ውጭ ሌላን ሳናመልክ፤ እገዛ እንጠይቅሃለን ካንተ ውጭ ሌላን እገዛ ሳንጠይቅ እንደማለት ነው።

አምልኮን እገዛ ከመጠይቅ ማስቀደሙ ጥቅል የሆነውን ልዩ ከሆነው ማስቀደምና ከባሮቹ መብት በፊት በራሱ መብት ቅድሚያ ለማሳሰብ ያክል ነው።

ዒባዳ (አምልኮ)፡ የሚለው ቃል **"ከጉልሁም፣ ከድብቁም፣ ውጫዊም ይሁን ውስጣዊ፣ ከንግግርም ይሁን ከተግባር አሏህ የሚወደውንና የሚደሰትበትን ሁሉ የሚያጠቃልል ስም ነው።"** እገዛን መጠየቅ 'ኢስቲዓና' ደግሞ **"ጥቅምን በማምጣትም ይሁን ክፋትን በመመከት በኩል እውን እንደሚያደርገው ተማምኖ አሏህ ላይ መደገፍ ነው።"**

አሏህን ማምለክና በሱም መታገዝ የዘላለማዊ ስኬትና ከአጠቃላይ ክፋት የመዳን መንገዱ ነው። ከሁለቱ ውጭ ለስኬት የሚያደርስ ምንም አይነት መንገድ የለም። አምልኮ አምልኮ የምትሆነው ከነብዩ ﷺ የተያዘች እና የአሏህ ፊት የተፈለገባት ስትሆን ብቻ ነው። አምልኮ አምልኮ ልትሆን የምትችለው በነኝህ ሁለቱ መሰረቶች ላይ ነው። በአሏህ መታገዝ በአልምኮው ሊካተት የሚችል ከመሆኑም ጋ ከአምልኮ በኋላ መወሳቱ ባርያ በየትኛውም አምልኮው በታላቁ አሏህ መታገዝ ለሱ ካለው አስፈላጊነት አንፃር ነው። አሏህ ካላገዘው ትእዛዛትን መፈፀምና ክልክላቶችን መራቅን አይነት የሚፈልገው ነገር (እንኳ) አይከሰትለትም።

ከዚያም በማስከተል ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ አለ፡

**(6) "ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።"** ወደ ቀጥተኛው መንገድ ጠቁመን፤ አቅናን ግጠመን ማለት ነው። ያም ብሩህ የሆነ ወደ አሏህና ወደ ጀነት የሚያደርሰው መንገድ ነው። እሱም እውነትን አውቆ በሱው መስራት ነውና ወደ መንገዱ ምራን፤ በመንገዱም ላይ ምራን። ወደ መንገዱ መመራት በጥቅሉ ዲነል ኢስላምን አጥብቆ መያዝና ከሱም ውጭ ያለውን ሃይማኖት መተው ሲሆን በመንገዱ ላይ መመራት ደሞ ከእውቀትም ሆነ ከተግባር አንፃር በእያንዳንዱ የሃይማኖቱ ዝርዝር ጉዳይ መመራትን የሚያጠቃልል ነው። ይህ ዱዓእ እጅግ ጥቅል ከሆኑና ለባሪያ እጅግ ጠቃሚ ከሆኑ ዱዓዎች መካከል ነው። ስለዚህም ይህ ዱዓእ ለሰው ልጅ ካለው አስፈላጊነት አንፃር በሶላት በእያንዳንዱ ረከዓ ላይ መለመኑ ግድ የሚለው ነው።

**(7)** ይህ መንገድ **"የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን..."** ከነብያቶች፣ ከሲዲቆች፣ ከሸሂዶችና ከሷሊሖች የሆኑትን መንገድ ምራን። እንደአይሁዶች ያሉትን እውነትን አውቀው በመተው የጠመሙትን **"...የተቆጣህባቸውን..."** እንዲሁም እንደክርስትያን ያሉትን እነዚያ ባለማወቅና በመሃይምነት እውነቱን ስተው **"የጠመሙትን" ም "...ሳይሆን..."** ቀጥተኛውን መንገድ ምራን። ይህች ሱራ ይዘቷ አጭር ከመሆኗም ጋ (በመልዕክት ደረጃ) ሌላ ሱራ ያላካለለችውን አካልላለች።

በመሆኑም ሶስቱንም የተውሒድ አይነቶችን አካትታለች: *ተውሒደል-ሩቡቢያህ* (የጌትነት አሃዳዊነቱ) **"የአለማት ጌታ"** በሚለው ስር ይገኛል፤ *ተውሒደል-ኢላሂያህ* (የአምላክነት አሃዳዊነቱ) አሏህን በአምልኮ መነጠል ማለት ሲሆን **"ለአሏህ"** በሚለውና **"አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን።"** በሚለው ቃል ስር ይገኛል፤ እንዲሁም *ተውሒደል-አስማእ ወሲፋት* (በስምና ባህሪያቱ ያለው አሃዳዊነት) ሲባል ራሱን የገለፀባቸውን ወይም መልዕክተኛው የገለፁበትን የሙሉነት መገለጫ የሆኑ ባህሪያትን ውድቅ ባለማድረግ፣ ምሳሌ ባለመስጠትና ባለማመሳሰል ለሱው ማፅደቅ ነው። ይህም እንዳሳለፍነው **"ምስጋና ባጠቃላይ..."** በሚለው ላይ ይገኛል።

**"ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።"** በሚለው ደግሞ ነብይነትን ማፅደቅ ይዛለች። ምክንያቱም ያ ከነብያዊ ተልዕኮ ውጭ የማይሳካ በመሆኑ ነው።

**"የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው።"** በሚለው ቃሉ ደግሞ በስራ መመንዳትን ማፅደቅ እና መመንዳቱም በፍትህ እንደሆነ እናገኛለን። ምክንያቱም (በአንቀፁ መሰረት) **“አድ-ዲን”** የተባለው ፍትሃዊ የሆነ ምንዳን ነውና።

በቀደር ማፅደቅንም አካትታለች፤ ቀደርያን እና ጀበርያን በተቃረነ መልኩ ባርያም (በፍቃዱ) የሚሰራ እንደሆነ ይዛለች።

ኧረ እንደውም **"ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።"** በሚለው ቃሉ ላይ በአጠቃላይ የቢድዓ ሰዎች እና የጠመሙ ሰዎች ላይ ሁሉ ረድ(አፀፋዊ ምላሽ) በውስጧ ይዛለች። ይህንንም ያልነው የአንቀፁ ጭብጥ እውነትን አውቆ በሱው መስራት በመሆኑ ነው። የቢድዓ እና የጥመት ባለቤት ሁሉ ደግሞ ይህንኑ ነው የተቃረኑት።

**"አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን።"** በሚለው ቃልም ስራን በአምልኮውም እገዛ በመሻቱም ኢኽላስን ለአሏህ ጥርት ማድረግን ይዛለች።

☼☼☼☼☼

## የ"አየተል ኩርሲይ" ተፍሲር

**"አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። ሕያው ራሱን ቻይ ነው። ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም። በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው። ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል። በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)። መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ። ጥበቃቸውም አያቅተውም። እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው።(255)"**

**(255)** የአሏህ መልዕክተኛ ﷺ ይህች አንቀፅ በውስጧ ካለው አሏህን ብቸኛ ማድረግ፣ ስለአስገኛችን አሏህ ከያዘችው ታላቅነትና የባህርይ ጥልቀት አንፃር ከቁርአን አናቅፆች ሁሉ የበላይ አንቀፅ መሆኗን ተናግረዋል። **"አሏህ"** አጠቃላይ የአምላክነት ማንነት ያለው፤ አምላክነትና አምልኮት ከሱ ውጭ ላለ የማይገባ መሆኑንና ከሱ ውጭ ያለ አካል አምላክነት እንዲሁም ከሱ ውጭ ያለው መመለኩ ውድቅ መሆኑን አሳወቀን። እሱ የመስማት፣ የመመልከት፣ የችሎታ፣ ፍላጎትና ሌሎችም በተሟላ መልኩ ፍፁም የህይወት ትርጉም መገለጫዎች የሆኑ ሁሉ ያለው **"ህያው"** ነው። እንዲሁም ራሱን ችሎ የቆመ አል-ቀዩም እና ከፍጡራኑ ሁሉ የተብቃቃ ነው፤ አጠቃላይ ድርጊታዊ የሆኑ ባህርያትን ሁሉ "**አል-ቀዩም**" የምትለዋ እንዳካተተችው ሁሉ ማለት ነው። እሱ አለች ለተባለች ነገር ሁሉ አለኝታዋ ነው፤ አስገኛት፣ አቆያት፣ ለህልውናዋም ለቆይታዋም የሚያስፈልጋትን ሁሉ አጣቀማት። የእርሱ ህያውና ራሱን ቻይነት ካለው ሙሉነት አንፃር **"ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም።"** ምክንያቱም እንቅልፍና ማንገላጀት የሚጋረጠው ድክመት፣ መሳንና ብክለት ለሚያጋጥመው ፍጡር ነው እንጅ ለታላቅነት፣ ለኩራትና ለልቅና ባለቤት ለሆነው አሏህ የሚጋረጡበት አይደሉም። አጠቃላይ የሰማዩም የምድሩም ሁሉ ባለቤት መሆኑንም ተናገረ። ሁሉም የርሱው ተገዥ ባርያዎች ናቸው። ከዚሁ ሁኔታ ደግሞ መውጣት የሚቻለው የለም።

**"በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ (በትንሣኤ ቀን) ለአልራሕማን ባሪያ ኾነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም።"** (19:93) የተገኘው ሁሉ ባለቤት እርሱው ነው፤ የሙሉ ባለቤትነት፣ የማስተናበር፣ የስልጣን፣ የኩራት ባህሪያት ለሱው ነው።

ከስልጣኑ ሙሉነት አንፃር **"እርሱ ዘንድ የሚያማልድ"** አንድም የለም **"በፍቃዱ ቢሆን እንጅ"**። ጎምቱዎች (ታላላቆች) እና አማላጆች ሁሉ እስኪፈቅድላቸው ድረስ ለሽምግልናው ወደፊት የማይሉ ተገዥ ባርያዎቹ ናቸው። **"«ምልጃ መላውም የአላህ ብቻ ነው፡፡ የሰማያትና የምድር ሥልጣን የእርሱ ብቻ ነው፡፡ ከዚያም ወደእርሱ ትመለሳላችሁ» በላቸው።..."** (39:44) አሏህም ደግሞ ማንንም እንዲያማልድ አይፈቅድም ለተደሰተበት ካልሆነ በቀር፤ ደሞም አይደሰትምም የሱን ብቸኛ መደረግን እና መልዕክተኞቹን ﷺ መከተልን መሰረት በማድረግ ቢሆን እንጅ (በየትኛውም ነገር አይደሰትም)። እነኝህ መገለጫዎች የሌሉት ከሷው ድርሻ የለውም።ከዚያም ስለሰፊና አካታች ዒልሙ አሳወቀን፤ እሱ ማለቂያ በሌለው መልኩ ለወደፊቱ ፍጡራኖቹ የሚጠብቃቸውን **"በስተኋላቸውም ያለውን"**፤ እንዲሁም ገደብ በሌለው መልኩ ስላለፈውም ሁሉ እንደሚያውቅ አሳወቀን። አንዳችም ተደባቂ ነገር ከሱ የሚደበቅ አይደለም። **"(አላህ) የዓይኖችን ክዳት ልቦችም የሚደብቁትን ሁሉ ያውቃል።"** (ጋፊር 19)

አሏህ ዘንድ ስላለው መረጃና እውቀት (እንዲያውቁ) "በሻውም ነገር እንጂ" የሚያካብብ አንዳችም የለም። ከነኝህም አሏህ ያሳወቃቸው ሸሪዓዊ እና ተፈጥሯዊ እውነታዎች ይገኙበታል። ይህ ግን እጅግ ኢምንትና እዚህ ግባ የማይባል ተራ ነገር ነው፤ ከአስገኘው አሏህ እውቀትና መረጃ አንፃር። ልክ ከፍጡራኖቹ መካከል እጅግ በጣም አዋቂዎቹ መልዕክተኞቹና መላእክቶቹ በሚከተለው መልኩ እንዳሉት **"«ጥራት ይገባህ፤ ከአስተማርከን ነገር በስተቀር ለኛ ዕውቀት የለንም። አንተ ዐዋቂው ጥበበኛው አንተው ብቻ ነህና» (አሉ)።"** (2:32)

ስለታላቅነቱና ስለልቅናውም እንዲሁ አሳወቀን፤ መንበሩ ሰማያትንና ምድርን መስፋቱ፣ እነርሱንም በውስጣቸው ያለውንም ህልውና ሁሉ በፍጡራኖቹ ላይ ባደረጋቸው አስባቦችና አለም አቀፍ ስርዓት ይጠብቃቸዋል። ይህ ከመሆኑም ጋ ካለው ሙሉ ታላቅነትና ችሎታ፤ በህግጋቶቹም ላይ ካለው ሰፊ ጥበብ አንፃር እነርሱን መጠበቁ የሚከብደው አይደለም። **"እርሱም የሁሉ በላይ..."** በአካሉም ከአጠቃላይ ፍጡራኑ ሁሉ፣ በባህሪው ታላቅነትም የበላይ እርሱው ነው፤ ፍጡራኑን ሁሉ ያሸነፈው የበላይ እሱው ነው፤ ህላዌው ሁሉ ያጎበደደለት፤ አስቸጋሪውም ሆነ ባርያው ሁሉ የሚዋረድለት ለሱው ነው። **"...የሁሉ ታላቅ ነው"** የታላቅነት፣ የኩራት፣ የልቅናና የግርማ ባህርያትን ሁሉ የሰበሰበ፤ ያ ልቦች የሚወዱት፤ ነፍሶች የሚያልቁት፤ ከባህሪው በኩል የቱንም ያክል ልቃ የሁሏም ነገር ታላቅነት ቢጠራቀም እንኳ ከልዕለ ሃያሉ ታላቅነት አንፃር የተኮላሸች መሆኗን አዋቂዎች ያውቃሉ።

ይህን የመሰለውን ከመልዕክቶች ሁሉ እጅግ ምጡቅ የሆነን መልዕክት የሰበሰበች አንቀፅ በርግጥ የቁርአን አናቅፅ ሁሉ የበላይ መሆኗ ይገባታልም፤ መልዕክቷን በማስተነተንና በመገንዘብ መልኩ ላጠናትም ልቦናው በእርግጠኝነት(የቂን)፣ በእውቀትና በኢማን የተሟላ መሆኑ ብሎም ከሸይጧን ክፋት ሁሉ መጠበቁም የሚገባ ነው።

☼☼☼☼☼

**የሱረቱ-ል-ዘልዘላህ ተፍሲር፤ መደንይ ነች**

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (ምድር (በኀይል) መንቀጥቀጥዋን በተንቀጠቀጠች ጊዜ፤ 1. ምድር ሸክሞችዋን ባወጣችም ጊዜ፤ 2. ሰውም "ምን ኾነች?" ባለ ጊዜ፤ 3. በዚያ ቀን ወሬዎችዋን ትናገራለች። 4. ጌታህ ለእርሷ በማሳወቁ ምክንያት። 5. በዚያ ቀን ሰዎች ሥራዎቻቸውን (ምንዳዋን) እንዲያዩ ይደረጉ ዘንድ (እንደየሥራቸው) የተለያዩ ኾነው (ከመቆሚያው ስፍራ) ይመለሳሉ። 6. የብናኝ ክብደት ያክልም መልካምን የሠራ ሰው ያገኘዋል። 7. የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሠራ ሰው ያገኘዋል። 8. )**

**(1-2)** አሏህ በትንሳኤ እለት ስለሚሆነው እያሳወቀን ነው፤ መሬቷ አጠቃላይ እሷ ዘንድ ያለው ግንባታም ይሁን ሌላ ምልክት እስኪንኮታኮት ድረስ በመርበትበት፣ በመናጋትና በመንቀጥቀጥ ትናጣለች፤ ኮረብታዎቿ ሜዳ ይሆናሉ፤ *«ትክክል ሜዳም ትኾናለች። በርሷ ዝቅታና ከፍታ የሌለባት»* **"ምድር ሸክሞችዋን ባወጣችም ጊዜ፤"** ማለትም በውስጧ ያሉ ሙታንም ይሁን ድልብ ይወጣሉ።

**(3) "ሰውም "ምን ኾነች?" ባለ ጊዜ፤"** የተጋረጠባትን ከባድ ጉዳይ ሲመለከት፤ በጉዳዩ ከባድነት: **"ምን ሆነች?"** ማለትም፡ ምን አይነት ነገር ተጋርጦባት ነው?!

**(4-5) "በዚያ ቀን...ትናገራለች። 4."** መሬት ነች **"ወሬዎችዋን"** (የምትናገረው)። ማለትም፡ መሬት ባሪያዎች በሰሩት ነገር ላይ ከሚመሰክሩባቸው አንዷ በመሆኗ ሰሪዎች እሷው ላይ ሆነው መልካምም ይሁን መጥፎ የሰሩትን ትመሰክራለች። ይህም የሚሆነው **"ጌታህ ለእርሷ በማሳወቁ ምክንያት። 5."** ነው። ማለትም፡ እሷው ላይ ሆነው የተሰራውን እንድትናገር አዘዛት እሷም ትእዛዙን የምታምፅ አይደለችም።

**(6)** "**በዚያ ቀን ሰዎች... (ከመቆሚያው ስፍራ) ይመለሳሉ። 6.**" በመካከላቸው ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ከመሰብሰቢያ ሜዳው "...**(እንደየሥራቸው) የተለያዩ ኾነው ...**" ማለትም፡ የሚበላለጡ ቡድን **"...ሥራዎቻቸውን (ምንዳዋን) እንዲያዩ ይደረጉ ዘንድ..."** ማለትም፡ የሰሩትን በጎና መጥፎ ስራ እንዲሁም ምንዳውን የተከማቸ አድርጎ ያሳያቸው ዘንድ (ሰዎቹ ከመቆሚያ ስፍራው ይመለሳሉ)።

**(7-8) "የብናኝ ክብደት ያክልም መልካምን የሠራ ሰው ያገኘዋል። 7. የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሠራ ሰው ያገኘዋል። 8."** ይህ በጎውንም መጥፎውንም ሁሉ አጠቃሎ የሰበሰበ (አገላለፅ) ነው። ምክንያቱም ከነገራቶች ሁሉ እጅግ በጣም አናሳ የሆነችዋን የብናኝ ክብደት ያክል እንዲያያትና እንዲመነዳባት ከተደረገ ከዛ በላይ በሆነውማ በቀዳሚነት የተገባ ይሆናል። ልክ ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ እንዳለን፡ "ነፍስ ሁሉ ከመልካም ነገር የሠራችውን የቀረበ ኾኖ የምታገኝበትን ቀን (አስታውስ)። ከመጥፎም የሠራችው በርስዋና በርሱ (በኀጢአትዋ) መካከል በጣም የሰፋ ርቀት ቢኖር ትመኛለች።" "የሰሩትንም ነገር ሁሉ ቀራቢ ኾኖ ያገኙታል።" በዚህ ላይ ትንሽም ቢሆን መልካሙን በመስራት ማነሳሳትን እና የሚናቅም ቢሆን መጥፎ ከመስራት ማስጠንቀቅን ይዟል።

☼☼☼☼☼

**የሱረቱ-ል-ዓድያት ማብራሪያ፤ መክይ ነች**

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። ( እያለከለኩ ሩዋጮች በኾኑት (ፈረሶች) እምላለሁ። 1 (በሰኮናቸው) እያጋጩ እሳትን አውጪዎች በኾኑትም፤ 2. በማለዳ ወራሪዎች በኾኑትም፤ 3. በእርሱ አቧራን በቀሰቀሱትም፤ 4. በ(ጠላት) ክቢ መካከል በእርሱ (በጧት) በተጋፈጡትም እምላለሁ። 5. ሰው ለጌታው ብርቱ ከሓዲ ነው። 6. እርሱም በዚህ ላይ መስካሪ ነው። 7. እርሱም ገንዘብን ለመውደድ በጣም ብርቱ ነው። 8. (ሰው) አያውቅምን? በመቃብሮች ያሉት (ሙታን) በተቀሰቀሱ ጊዜ፤ 9. በልቦች ውስጥ ያለውም ሁሉ በተገለጸ ጊዜ (እንዴት እንደሚኾን)?! 10. ጌታቸው በዚያ ቀን በእነርሱ (ነገር) በእርግጥ ውስጠ አዋቂ ነው። 11.)**

---

**(1)** ከፍ ያለው አሏህ በሷ ላይ ካለው ፍጡራን ዘንድ የታወቀ ደማቅ ምልክትና ጉልህ ፀጋ አንፃር በፈረስ ይምላል። የማለበትን ከሁኔታም አንፃር ሲታይ ሌሎች መሰል እንስሳት በማይጋሩባት ሁኔታ ነው የማለው። እንዲህም አለ **"እያለከለኩ ሩዋጮች በኾኑት (ፈረሶች) እምላለሁ።"** ከብርታቱ የተነሳ ማለክለክ የሚያደርሳቸው የሆነን ሃይለኛና ጥግ የደረሰ ሩጫን ሯጮች የሆኑት። ያም (ማለክለክ) ሩጫዋ ሲበረታ ከደረቷ የሚወጣ የስትንፋሷ ድምፅ ነው።

**(2) "(በሰኮናቸው) እያጋጩ እሳትን አውጪዎች በኾኑትም፤"** በሚሮጡበት ጊዜ በሰኮናቸው ድንጋዩ ላይ የሚወጡበት ብርታትና ሃይላቸው እሳትን ያወጣል።

**(3)** በጠላት ላይ **"በማለዳ ወራሪዎች በኾኑትም"**፤ ይህም አብዛኛውን ጊዜ ወረራ የሚካሄደው በማለዳ በመሆኑ ነው።

**(4-5) "በቀሰቀሱበትም"** በሩጫቸውና በማጋጨታቸው **"አቧራ"** (የሚቀሰቅሱት)። **"በ(ጠላት) ክቢ መካከል በእርሱ (በጧት) በተጋፈጡትም እምላለሁ።"** ወረራው በታቀደበት የጠላት ስብስብ መሃል ይጋፈጣሉ።

**(6)** መሃላው የተማለበት (ጭብጥ) ቀጣዩ ቃሉ ነው፡ "**ሰው ለጌታው ብርቱ ከሓዲ ነው።**" ለአሏህ ተገቢ የሆነውን መልካም ነገር ታቃቢ (ነው)። የሰው ልጅ በተፈጠረበት ማንነት ነፍስ ያለባትን ግዴታ በተሟላ መልኩ ለመወጣት የምትመች ሆና አይደለም። ይልቅ ተፈጥሮዋ ከሚጠበቅባት ኢኮኖሚያዊም ሆነ አካላዊ ግዴታ መወጣት መስነፍና መታቀብ ነው። አሏህ መርቶት ከዚህ ባህሪ ግዴታን ወደ መወጣት የገጠመው ካልሆነ በቀር።

**(7) "እርሱም በዚህ ላይ መስካሪ ነው።"** ማለትም፡ የሰው ልጅ ስለራሱም ከሚያውቀው አንፃር ያለበትን የማቀብና የከሃዲነት ማንነቱ ላይ መስካሪ የሆነ እንጅ የሚያስተባብለውና የሚያወግዘውም አይደለም። ምክንያቱም ግልፅና ጉልህ የሆነ ጉዳይ ነውና። በርግጥ በአንቀፁ ላይ መስካሪ ነው የተባለው ለአሏህ ቢባልም ያስኬዳል። ማለትም፡ የሰው ልጅ ለጌታው ብርቱ ከሃዲ ነው፤ ለዛም ደሞ አሏህ መስካሪ ነው። በአንቀፁ ላይ ለጌታው ከሃዲ ለሆነ ሰው ከባድ ዛቻ አለበት። በሱ ላይ አሏህ መስካሪው ነውና።

**(8) "እርሱም**፡ ማለትም፡ የሰው ልጅ "...**መልካምን ለመውደድ...**" ማለትም፡ ገንዘብን "...**በጣም ብርቱ ነው።**" ማለትም፡ ለገንዘብ ያለው ውዴታ እጅግ የበዛ ነው። ለዛ ያለው ውዴታ ነው እሱ ላይ ያሉበትን ግዴታዎች ከመወጣት ያቀበው። የነፍሱን ፍላጎት ከጌታው ውዴታ በፊት እንዲያስቀድም ያደረገው። ይህ ሁሉ የሆነው ታዲያ እይታውን በዝች አለም ላይ ስለገደበና ከአኼራውም ስለተዘናጋ ነው።

**(9-10)** ለዚህም ነው ታድያ ለቀጠሮው ቀን ፍርሃት እንዲኖረው በማነሳሳት መልኩ እንዲህ ያለው፡ "**(ሰው) አያውቅምን?!...**" ማለትም፡ ይህ ተላላ አያውቅምን? "**በመቃብሮች ያሉት (ሙታን) በተቀሰቀሱ ጊዜ፤**" ማለትም፡ ሙታኖችን ለመሰብሰብና ለመቀስቀስ ከቀብራቸው ባወጣቸው ጊዜ፤ "**በልቦች ውስጥ ያለውም ሁሉ በተገለጸ ጊዜ (እንዴት እንደሚኾን)?!**" ማለትም፡ ልቦና ውስጥ የተደበቀው የመልካምም ይሁን የመጥፎ እምቅ ግልፅ በሆነና በጎላ ጊዜ፤ ሚስጥሩ ግልፅ የውስጡም ጉልህ በሚሆንበት ጊዜ፤ በፍጡራኖች ፊትም የስራቸው ውጤት ግልፅ በሆነበት ጊዜ ማለት ነው።

**(11) "ጌታቸው በዚያ ቀን በእነርሱ (ነገር) በእርግጥ ውስጠ አዋቂ ነው።"** ማለትም፡ በግልፅና ውስጣዊ፤ በድብቁም በጉልሁ ስራቸው ላይ የሚመለከትና በሷውም ላይ የሚመነዳቸው ነው። ዘላለሙን የሚያውቃቸው ከመሆኑም ጋ ስለነሱ በዛንለት ያለውን መረጃ ነጥሎ ጠቀሰ፤ ይህም ምክንያቱ አሏህ የሚመነዳበት ሁኔታ መነሻነቱ በራሱ ከሚያውቀውና ከተመለከተው የሆነን ምንዳ በመሆኑ ነው።

☼☼☼☼☼

## የሱረቱ አልቃሪዓህ ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (ቆርቋሪይቱ (ጩኸት)፤ 1. ምን አስደናቂ ቆርቋሪ ናት! 2. ቆርቋሪይቱም ምን እንደኾነች ምን አሳወቀህ? 3. ሰዎች እንደ ተበታተነ ቢራቢሮ (ወይም ኩብኩባ) በሚኾኑበት ቀን፤ 4. ጋራዎችም እንደ ተነደፈ ሱፍ በሚኾኑበት (ቀን ልቦችን በድንጋጤ ትቆረቁራለች።) 5. ሚዛኖቹ የከበዱለት ሰውማ፤ 6. እርሱ በምትወደድ ኑሮ ውስጥ ይኾናል። 7. ሚዛኖቹም የቀለሉበት ሰውማ፤ 8. መኖሪያው ሃዊያህ ናት 9. እርሷም ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ? 10. (እርሷ) በጣም ተኳሳ እሳት ናት።11.)**

---

**(1-3) "ቆርቋሪይቱ (ጩኸት)፤"** ከእለተ ተንሳኤ ስያሜዎቿ መካከል አንዱ ነው። በዚህም የተሰየመችበት ምክንያት ሰዎችን ብሽብሯ የምትቆረቁርና የምታስደነግጣቸው በመሆኗ ነው። ለዚህም ነው ጉዳይዋን ከፍ ከበድ አድርጎ በተከታዩ ቃሉ የገለፀው **"ቆርቋሪይቱ (ጩኸት)፤ 1. ምን አስደናቂ ቆርቋሪ ናት! 2. ቆርቋሪይቱም ምን እንደኾነች ምን አሳወቀህ? 3"**

**(4) “ሰዎች እንደ ...በሚኾኑበት ቀን፤”** ካለው የድንጋጤ ብርታትና ከባድነት አንፃር። **“...እንደ ተበታተነ ቢራቢሮ (ወይም ኩብኩባ) . . . ”** ከፊሉ በከፊሉ ላይ እንደሚዋልል የአንበጣ መንጋ፤ በአንቀፁ ላይ “አልፈራሽ” የተባሉት አቅጣጫዋን ሳታውቅ በለሊቱ ክፍለጊዜ የሚበርሩ እሳት ቢቀጣጠልላት እንኳ ምንነቱን ባለማወቋ ጥልቅ የምትል (የእሳት እራት) ነች። የዛንለት እነዚያ የአእምሮ ባለቤት የሆኑት የሰውልጆችም ሁኔታቸው እንዲሁ ነው።

**(5)** እነኚህ ብርቱ የሆኑ የማይሰሙት ተራሮች ደግሞ **“... እንደ ተነደፈ ሱፍ...”** ይሆናሉ። ማለትም፡ ተነድፎ በመበጠሩ እጅጉን ደካማ ሆኖ እንደቀረ ሱፍ የትኛውም የንፋስ ቀላል ሳይቀር ይዞት የሚበር ይሆናል። ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ ይላል፡ “ጋራዎችንም እርሷ እንደ ደመና አስተላለፍ የምታልፍ ስትኾን የቆሞች ናት ብለህ የምታስባት ሆና ታያታለህ። የዚያን ነገሩን ሁሉ ያጠነከረውን የአላህን ጥበብ (ተመልከት)። እርሱ በምትሠሩት ሁሉ ውስጥ ዐዋቂ ነው።” (ነምል 88) ከዚህም በኋላ የተበተነ አቧራ ትሆናለች፤ የሚታይ ነገር የሌላት ሆና ትወድማለች። የዚህኔ ሚዛኖችም ይቆማሉ ሰዎችም ለሁለት ይከፈላሉ፤ ለዘላለሙ እድለኛና እድለቢስ ሆነው።

**(6-7) “ሚዛኖቹ የከበዱለት ሰውማ፤”** ማለትም፡ በጎው ከክፋቱ በላይ ያመዘነችለት **“እርሱ በምትወደድ ኑሮ ውስጥ ይኾናል።”** በመደሰቻ ጀነቶች ውስጥ ይሆናል።

**(8-11) “ሚዛኖቹም የቀለሉበት ሰውማ፤”** ክፋቱን መቋቋም የሚችል በጎ የሌለው **“መኖሪያው ሃዊያህ ናት።”** ማለትም፡ መኖሪያና መጠለያው ከስያሜዎቿ አንዱ ሃዊያህ የሆነችው እሳት ነች። ልክ እንደዛች የማትለየው እናቱ። ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ እንዳለው፡ **“... ቅጣቷ የማይለቅ ነውና”** (አል-ፉርቃን) የዚህን ትርጉም በማስመልከት እንዲህ ተብሏል፡ መሃል አናቱ የእሳቱ ውስጥ ማገዶ ነች። ማለትም፡ ወደ እሳቱ በጭንቅላቱ ይወረወራል ማለት ነው።

**“እርሷም ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ?”** ይህ የሷን ጉዳይ ከፍ ከማድረግ አንፃር ነው። ከዚያም በተከታዩ ቃሉ አብራራት፡ **“(እርሷ) በጣም ተኳሳ እሳት ናት።”** ማለትም፡ ብርቱ አቃጣይ፤ የማቃጠል ብርታቷ ከዱንያዋ እሳት የማቃጠል ብርታት በሰባ እጥፍ የምትበልጥ የሆነች ነች። ከሷ በአሏህ እንጠበቃለን።

✿✿✿✿✿

### የሱረቱ ተካሡር ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በብዛት መፎካከር (ጌታችሁን ከመገዛት) አዘነጋችሁ። 1. መቃብሮችን እስከ ጎበኛችሁ ድረስ። 2. ተከልከሉ፤ ወደፊት (ውጤቱን) ታውቃላችሁ። 3. ከዚያም ተከልከሉ፤ ወደ ፊት ታውቃላችሁ። 4. በእውነቱ (የሚጠብቃችሁን) እርግጠኛ ዕውቀትን ብታውቁ ኖሮ፤ (ባልዘናጋችሁ ነበር)። 5. ገሀነምን በእርግጥ ታያላችሁ. 6. ከዚያም እርግጠኛን ማየት ታዩዋታላችሁ። 7. ከዚያም ከድሎታችሁ ሁሉ በዚያ ቀን ትጠየቃላችሁ። 8.)**

**(1)** ተጋሪ ሳያደርጉ እሱን በብቸኝነት ማምለክ፤ እሱኑ ማወቁ፣ ወደሱው መመለሱ፤ የሱን ውዴታ ከሁሉም ነገር ማስቀደም የሆነውን የመፈጠራቸው አላማ ለመዘናጋታቸው ባርያዎቹን በመውቀስ መልኩ ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ ይላል፡ **"...(ጌታችሁን ከመገዛት) አዘነጋችሁ።"** አሁን ካወሳነው። "**በብዛት መፎካከር...**" ሰዎች የሚፎካከሩበትን ሁሉ ሊያካትት ዘንድ የፉክክሩን ምንነት አላወሳም፤ የአሏህ ፊት ያልተፈለገበት ተፎካካሪዎች የሚፎካከሩበትን፤ ተመፃዳቂዎች የሚመፃደቁበትን በገንዘብም፣ በልጅም፣ በረዳትም፣ በሰራዊትም፣ በሰራተኛም፣ በክብርም፣ ሌላ ሌላም አንዱ ለሌላው "እኔ እበልጥ" ብሎ የሚፎካከረትን ሁሉ ሊያካትት ዘንድ።

**(2)** ይህ ዝንጉነታችሁ፣ ጨወታችሁ፣ መዘናጋታችሁ ቀጥሎ "**መቃብሮችን እስከ ጎበኛችሁ ድረስ**" ዘለቀችሁ። የዚህኔ ነው ግርዶሹ የተነሳላችሁ፤ ምን ይሁን መካሱን በማትችሉበት ጊዜ ሆነ እንጅ፤ "**መቃብሮችን እስከ ጎበኛችሁ ድረስ**" የሚለው አንቀፅ "በርዘኽ" ከሱ የሚፈለገው ወደቀጣዩ አገር መሸጋገር የሆነ አገር እንደሆነ ያመላክተናል። ምክንያቱም አሏህ "ዛያሪዎች" ብሎ ነው እንጅ የገለፃቸው "የሚቆዩ" ብሎ አይደለም፤ ይህም ከሞት መቀስቀስን እና ቀሪ በሆነችዋ ጠፊ ባልሆነችዋ አገር መመንዳትን ይጠቁማል።

**(3-6)** ለዚህም ነው **"ተከልከሉ፤ ወደፊት (ውጤቱን) ታውቃላችሁ። 3. ከዚያም ተከልከሉ፤ ወደ ፊት ታውቃላችሁ። 4. በእውነቱ (የሚጠብቃችሁን) እርግጠኛ ዕውቀትን ብታውቁ ኖሮ፤ (ባልዘናጋችሁ ነበር)። 5."** ማለትም፡ ልበናችሁ ድረስ የሚዘልቅ እውቀት ቢኖራችሁ ኖሮ መፎካከር ባላዘናጋችሁ፤ ወደ መልካም ስራም በተሯሯጣችሁ ነበር። ነገር ግን ተጨባጩን አለማወቃችሁ ወደምታዩት ነገር አደረሳችሁ። "**ገሀነምን በእርግጥ ታያላችሁ።**" ማለትም፡ ትንሳኤን እንደምትመለከቱ ነው፤ አሏህ ለካፊሮች ያዘጋጃትን ቅጣት እንደምትመለከቱ ነው።

**(7)** **"ከዚያም እርግጠኛን ማየትን ታዩዋታላችሁ።"** ማለትም፡ የአይን እይታ፤ ከፍ ያለው አሏህ እንዳለው "ከሓዲዎችም እሳትን ያያሉ። እነርሱም በውስጧ ወዳቂዎች መኾናቸውን ያረጋግጣሉ። ከእርሷም መሸሻን አያገኙም።"

**(8)** **"ከዚያም ከድሎታችሁ ሁሉ በዚያ ቀን ትጠየቃላችሁ።"** ያ በዱንያ ላይ ለተጣቀማችሁበት ተገቢውን ሹክር አደረሳችሁን? በሱ ላይ ለአሏህ የሚገባውን መብቱን ተወጣችሁን? እሱን ለማመፅ አልተጠቀማችሁበትምን? (አግባቡን ጠብቃችሁ ከነበር) የተሻለ በላጭ ፀጋውን ይውልላችሁ ዘንድ። ወይስ ተሸንግላችሁ የሚገባውን ሹክር አላደረሳችሁም? ምናልባትም ጭራሽ እሱኑ ለማመፅ ነው የተጠቀማችሁበት? በዛውም ይቀጣችኋልና። ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ ይላል፡ "እነዚያም የካዱት በእሳት ላይ በሚጋፈጡ ቀን «ጣፋጮቻችሁን በአነስተኛይቱ ሕይወታችሁ አሳለፋችሁ። በእርሷም ተጣቀማችሁ። ስለዚህ በምድር ላይ ያለ አግባብ ትኮሩ በነበራችሁትና ታምጹ በነበራችሁት ዛሬ የውርደትን ቅጣት ትምመነዳላችሁ» (ይባላሉ)።"

☼☼☼☼☼

### የሱረቱ አል-ዓስር ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በጊዜያቱ እምላለሁ። 1. ሰው ሁሉ በእርግጥ በከሳራ ውስጥ ነው። 2. እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሠሩት፣ በእውነትም አደራ የተባባሉት፣ በመታገስም አደራ የተባባሉት ብቻ ሲቀሩ። 3.)**

---

**(1-3)** ከፍ ያለው አሏህ የለሊትና ቀን መፈራረቅ፤ የባሮቹ ስራና ድርጊቶች መድረክ በሆነው ጊዜ ይምላል። የሰው ልጅ ሁሉ ከስሯል፤ ከሳሪ ደግሞ የአትራፊ ተቃራኒ ነው። ክስረት የሚበላለጥ የሆነ የተለያየ በርከት ያለ ደረጃ አለው። ክስረቱ ልቅ የሆነበት ዱኒያውንም አኼራውንም እንደከሰረው፤ ፀጋ ሁሉ አምልጦበት ለዓዛብ እንደተዳረገው አይነቱ ሊሆን ይችላል፤ እንዲሁም ክስረቱ በተሰነ መልኩ ብቻ የሆነ ሊሆንም ይችላል። ለዚህም ነው ከነኝህ አራቱን ባህርያት ከተላበሰ ውጭ ኪሳራ ላይ መሆኑን በጥቅሉ የገለፀው።

- አላህ እንዲያምን ባዘዘው ነገር ሁሉ ማመን፤ እምነትም ደሞ ያለ እውቀት ሊመጣ ወይም ሊሟላ የማይችል በመሆኑ ከሱ ውጭ ሙሉ ሊሆንበት የማይችልበት ቅርንጫፉ ነው።

- እንዲሁም በጎ መስራት፤ ውጫዊ ይሁን ውስጣዊ፣ ከአላህ ሙብቶች ጋ የተቆራኘ ይሁን ከባሮቹ ሙብቶች ጋር የተቆራኙ፤ ግዴታ ይሁን የሚመከር መልካም ሥራን ሁሉ መስራት

- እንዲሁም ያ ኢማንና በጎ መስራት የሆነው እውነት ላይ አደራ መባባል፤ ማለትም፡ ከፊሉ ሌላውን በዚሁ አደራ ሊለውና ሊያነሳሳው ብሎም እንዲወደውም ሊያደርገው ማለት ነው።

- አሏህን በመታዘዝ ላይ፣ አሏህን ከማመፅና አሳማሚ በሆነው ቀደር መታገስ።

አንድ ባርያ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ነገራቶች ነፍሱን ሙሉ የሚያደርግ ሲሆን በመጨረሻዎቹ ሁለት ነገራቶች ደግሞ ሌላውን ሙሉ የሚያደርግበት ነው። እነዚህ አራት ነገሮች አሟልቶ ሲገኝ ደግሞ ከኪሳራ ተጠብቆ ታላቅ ስኬትን የተጎናፀፈ ይሆናል።

☼☼☼☼☼

### የሱረቱ አል-ሁመዛህ ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (ለሃሜተኛ ለዘላፊ ሁሉ ወዮለት። 1. ለዚያ ገንዘብን የሰበሰበና የቆጣጠረው (ያደለበውም) ለኾነ ፤(ወዮለት)። 2. ገንዘቡ የሚያዘወትረው መኾኑን ያስባል። 3. ይከልከል፤ በሰባሪይቱ (እሳት) ውስጥ በእርግጥ ይጣላል። 4. ሰባሪይቱም ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ? 5. የተነደደችው የአላህ እሳት ናት። 6. ያቺ በልቦች ላይ የምትዘልቅ የኾነችው። 7. እርሷ በእርግጥ በእነርሱ ላይ የተዘጋጀች ናት። 8. በተዘረጋች አዕማድ ውስጥ (የተዘጋች ናት)። 9.)**

(1) “... **ወዮለት**” ማለትም፡ ከባድ ዛቻ፣ ጣጣ፣ ጭንቅ ቅጣት አለበት። “**ለሃሜተኛ ለዘላፊ ሁሉ...** ” ማለትም፡ ያ ሰዎችን ባካሉም በቃሉም የሚዘልፈው፤ “ሃማዝ” ማለት ያ ሰዎችን የሚያነውር፤ በአሽሙርና በአካክል ሰዎችን የሚተች ነው። “ለማዝ” ማለት ደግሞ በምላሱ የሚያነውር ነው።

(2) ከዚህ ሃሜተኛና ዘላፊ ባህርያት መካከል ገንዘብ እያከማቹ እየቆጠሩ በዛው ከመቦረቅ በስተቀር ሌላ ለምንም ግድ የሌለው ሰው ነው። በጥሩ መንገዶች ላይ በማዋል ፣ ዝምድናን በመቀጠል እና የመሳሰሉት ላይ ለማዋል ፍላጎት የለውም።

(3) ባለማወቁ “**ገንዘቡ የሚያዘወትረው መኾኑን ያስባል።**” በዚህ ዓለም ውስጥ (የሚያዘወትርው መሆኑን ያስባል) ለዚህም ነው የህይወት ዘመናቸው የሚጨምርለት መስሎት ጥረቱ እና ትግሉ ሁሉ ገንዘቡን ለማሳደግ የሚውለው። በእውነቱ ስስት የሰዎችን ሕይወት እንደሚያጠፋ እና ቤቶችን እንደሚያፈርስ እና በጎነት ደግሞ የህይወት ዘመን እንዲጨምር ግን አያውቅም።

(4-7) “**ይከልከል፤ በሰባሪይቱ (እሳት) ውስጥ በእርግጥ ይጣላል።**” ማለትም፡ ይወረወራል። “**በሰባሪይቱ (እሳት) ውስጥ 4. ሰባሪይቱም ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ? 5.**” እሷን በማላቅና ጉዳይዋን ከባድነት በመጠቆም ነው፤ ከዚያም በቀጣዩ ቃሉ አብራራት፡ “**የተነደደችው የአላህ እሳት ናት።**” ያች መቀጣተያዋ እሳትና ድንጋይ የሆነች። ከብርታቷም የተነሳ “**ያቺ በልቦች ላይ የምትዘልቅ የኾነችው።**” ማለትም፡ (መቀጣጫዋ) ከሰውነት አካል ልቦና ድረስ የሚዘልቅ የሆነ።

(8) ከዚህ ጥግ የደረሰ ቃጠሎም ጋ እነሱ እሷው ውስጥ የታገቱ ናቸው። ከሷ መውጣቱም ተስፋ የቆረጡበት ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው “**እርሷ በእርግጥ በእነርሱ ላይ የተዘጋጀች ናት።**” ያለው። ማለትም፡ የተቆለፈች። “**በተዘረጋች አዕማድ ውስጥ**” ከኋላ በርም “**(የተዘጋች ናት።**” ከሷ እንዳይወጡ ማለት ነው። “ከጭንቀት ብርታት የተነሳ ከእርሷ ለመውጣት በፈለጉ ቁጥር ከእርሷ ውስጥ እንዲመለሱ ይደረጋሉ።” ከሷም በአሏህ እንጠበቃለን፤ መሃርታውንና ጥበቃውንም እንጠይቀዋለን።

۞۞۞۞۞

**የሱረቱ አል-ፊል ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች**

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በዝሆኑ ባለቤቶች ጌታህ እንዴት እንደሠራ አላወቅህምን? 1. ተንኮላቸውን በጥፋት ውስጥ (ከንቱ) አላደረገምን? (አድርጓል)። 2. በእነርሱም ላይ መንጎች የኾኑን ዎፎች ላከ። 3. ከተጠበሰ ጭቃ በኾነ ድንጋይ የምትወረውርባቸው የኾነችን፤ (አዕዋፍ)። 4. ቅጠሉ እንደ ተበላ አዝመራም አደረጋቸው። 5. )**

(1-5) ማለትም፡ የአሏህን ችሎታ፣ የማንነቱን ታላቅነት፣ በባሮቹ ላይ ያለውን ርህራሄ፣ የአሃዳዊነቱ ማስረጃ፣ የመልዕክተኛው ሙሓመድን ﷺ እውነተኝነት፣ በእነዚያ ወደተከበረው ቤቱ ደርሰው ማውደሙን የፈለጉት፤ ለዚህም የታጠቁት፤ ለማውደሙም የዝሆን መንጋ ከነሱው ጋ ይዘው የሄዱት፤ የመመለስ ተስፋ የሌላቸውን ከአቢሲኒያም ከየመንም ይዘው የመጡትን፤ የዝሆን ባለቤቶች ላይ ባደረገው አላየህምን? -ለዓረቦችም የዜያኔ መመከት በማይችሉበት ሆነው- ወደ መካ አቅራቢያ በደረሱና የመካ ሰዎችም በራሳቸው ላይ ከነሱ ሰግተው ከመካ በወጡ ጊዜ አሏህ በእነርሱ ላይ መንጎች የኾኑን ወፎችን ላከባቸው። ማለትም፡ የተለያየ የሁነ። ከሸክላ የሆኑ ድንጋዮችን ይወረውሩባቸዋል። በሷም መታቻቸው፤ ቅርቡንም ሩቁንም ተከታተለቻቸው፤ ሞቱም ተንኮታኮቱም፤ እነሱም ቅጠሉ እንደ ተበላ አዝመራ ሆኑ። አሏህም ከክፋታቸው ታደገ፤ ክፋታቸውንም በራሳቸው ላይ መለሰ። ታሪካቸው የታወቀና የተሰራጨ ነው። ይህች ነብዩ ﷺ የተወለዱባት አመት ከተልዕኮው ጠቋሚዎችና ከጥሪው አመላካቾች መካከል ሆነች። ለአሏህ ምስጋናና ሹክር ይገባው።

✪✪✪✪✪

### የሱረቱ ሊኢላፊ ቁረይሽ ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (ቁረይሽን ለማላመድ (ባለዝሆኖቹን አጠፋ)። 1. የብርድና የበጋን ወራት ጉዞ ሊያላምዳቸው ይህንን ሠራ። 2. ስለዚህ የዚህን ቤት (የከዕባን) ጌታ ይግገዙ። 3. ያንን ከረኃብ ያበላቸውን ከፍርሃትም ያረካቸውን (ጌታ ያምልኩ)። 4. ናት)።)**

---

(1-4) በርካታ የተፍሲር ሊቃውንት የዚህ ሱራ መጀመሪያው ከሱ በፊት ያለው ሱራ እንደሆነ ይገልፃሉ።(أي: إن الجار والمجرور متعلق بالسورة التي قبلها) ማለትም፡ ለቁረይሾች ሰላም፣ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ፣ በክረምት ለየመኖች በበጋውም ደሞ ለሻም የንግድና የሲሳይ ፍለጋ ጉዟቸውን ለማስተካከል ስንል ይህን በዝሆኑ ሰዎች ላይ ያደረግነውን አደረግን። እነሱን በክፋት የፈለጋቸውን አሏህ ﷺ የሓረምና የሰዎቹን ጉዳይ በዓረቦች ዘንድ እስኪያከብሯቸውና በየትኛውም የጉዞ ፍላጎታቸው እስከማያደናቅፏቸው ድረስ ከፍ አደረገ። ለዚህም ነው አሏህ ﷺ ሹክር እንዲያደርሱ ያዘዛቸው እንዲህም አለ ፡ "**ስለዚህ የዚህን ቤት (የከዕባን) ጌታ ይግገዙ።**" ማለትም፡ በብቸኝነት ሊነጥሉትና አምልኮም ለሱ ብቻ ሊያጠሩ።

“**ያንን ከረኃብ ያበላቸውን ከፍርሃትም ያረካቸውን (ጌታ ያምልኩ)። 4. ናት)።**” የሲሳይ ፍለጋ መግራቱና ከስጋት መዳን ከፍ ላለው አሏህ ሹክር ማድረስ ግድ ከሚያስብሉ ዱኒያዊ ጉዳዮች መካከል ናቸው። ጌታየ ሆይ! ለድብቁም ለግልሁም ፀጋህ ምስጋና ባጠቃላይ ላንተ የተገባ ነው። አሏህ በዝች ሱራ ላይ ጌትነቱን ከቤቱ ጋ ነጥሎ አቆራኝቶ ያመጣው ቤቱ(ካዕባ) ካለው ክብርና ደረጃ አንፃር እንጅ እሱ የሁሉም ጌታ ነው።

✪✪✪✪✪

## የሱረቱ አል-ማዑን ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (ያንን በምርመራው የሚያስተባብለውን አየህን? (ዐወቅከውን?) 1. ይህም ያ የቲምን በኀይል የሚገፈትረው፤ 2. ድኻንም በማብላት ላይ የማያግባባው ሰው ነው። 3. ወዮላቸው ለሰጋጆች። 4. ለእነዚያ እነርሱ ከስግደታቸው ዘንጊዎች ለኾኑት፤ (ሰጋጆች)። 5. ለእነዚያ እነርሱ ይዩልኝ ባዮች ለኾኑት። 6. የዕቃ ትውስትንም (ሰዎችን) የሚከለክሉ ለኾኑት (ወዮላቸው)። 7.)**

---

(1) አሏህ ﷻ የሱንና የባሮቹን ሓቅ የተውትን በመውቀስ መልኩ እንዲህ ይላል፡ “**ያንን በምርመራው የሚያስተባብለውን አየህን? (ዐወቅከውን?)**” ማለትም፡ ሞቶ በመቀስቀስና በምንዳው፤ መልዕክተኞች ይዘውት በመጡት አያምንም።

(2) “**ይህም ያ የቲምን በኀይል የሚገፈትረው፤...**” ማለትም፡ ብልቡ ድርቅና እና ተስፋ የሚያደርገው ምንዳም ሆነ የሚሰጋው ቅጣት ባለመኖሩ ምክንያት የማያዝን ብሎም በብርታትና ብድርቅና የሚገፈትር የሆነው፤

(3) “**. ድኻንም በማብላት ላይ የማያግባባው ሰው ነው።**” ማለትም፡ ሌላውን። እራሱም ሚስኪን የማያበላ ከሆነ ማ (ለዛቻው) ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።

(4-5) “**. ወዮላቸው ለሰጋጆች።**” ማለትም፡ እነዚያ ሰላታቸውን አጥብቀው ያዥ የሆኑት፤ ነገር ግን እነሱ “**ለእነዚያ እነርሱ ከስግደታቸው ዘንጊዎች ለኾኑት፤ (ሰጋጆች)።**” የሆኑት ናቸው። ማለትም፡ እሷኑ የሚጨፈልቋት፤ ጊዜዋን የሚተዋት፤ ማእዘኖቿን የሚያጓድሏት የሆኑት ናቸው፤ ይህም የሆነው የአሏህ ጉዳይ ስለማያሰስባቸው ነው። ከመታዘዞች ሁሉ እጅግ አሳሳቢዋን ነውና የተውት። ሰላትን መርሳት ባለቤቱ ሊወገዝበትና ሊወቀስበት የሚገባው የሆነ ጉዳይ ነው። በሰላት ውስጥ ሆኖ መርሳት ግን ከየትኛውም ሰው ከነብዩ ﷺም ሊከሰት የሚችል ነገር ነው።

(6-7) ለዚህም ነው አሏህ እነኝህን በእዩልኝ(ሪያእ)፣ በልብ ድርቀትና በርህራሄ ማጣት የገለፃቸው። እንዲህም አለ፡ “**ለእነዚያ እነርሱ ይዩልኝ ባዮች ለኾኑት።**” ማለትም፡ ሰዎች ስለሚያዋቸው ነው

"**የዕቃ ትውስትንም (ሰዎችን) የሚከለክሉ ለኾኑት (ወዮላቸው)።**" ማለትም፡ በትውስት ወይም ብስጦታ መስጠቱ የማይጎዳን ነገር ለመስጠት ንፉግ ናቸው። እንደ የቤት እቃ፣ ባልዲ፣ መቆፈሪያና መሰል መለዋወጡ እንደቀላልና እንደባህል የሆነበት ሁሉ። እነኝህ ከስስታቸው አንፃር የዕቃ ትውስትንም ይከለክላሉ። ታድያ ከዛ በላይ በሆነው እንዴት ሆነው ነው?!

ይህች ሱራ ሚስኪንና የቲምን በመመገብ ላይ ማነሳሳት፣ በዛው ላይ ማነቃቃት፣ ሶላትን ጠብቆ መያዝ፣ በሷው ላይ መጠባበቅ፣ በሷው እና በሌሎች ስራዎችም ላይ ኒያን ማጥራት ይዛለች። መልካም በመስራት፤ የቤት እቃ፣ ባልዲ ነገርም ሆነ ኪታብ ነገር መዋዋስንና ቀለል ያሉ ነገራቶችን መለጋገስንም አካትታለች። ምክንያቱም አሏህ ይህን ያያደረጉትን ወቅሷልና። አሏህ ይበልጡን ያውቃል።

۞۞۞۞۞

**የሱረቱ አል-ከውሠር ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች**

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (እኛ በጣም ብዙ በጎ ነገሮችን ሰጠንህ። 1. ስለዚህ ለጌታህ ስገድ፤ (በስሙ) ሰዋም። 2. ጠይህ (የሚጠላህ) እርሱ በእርግጥ (ዘሩ) የተቆረጠው ነው። 3.)**

---

(1) ከፍ ያለው አሏህ ለነብዩ ሙሓመድ ﷺ አደረግኩልህ በሚል (በመመፃደቅ) መልኩ እንዲህ ይላቸዋል: "**እኛ በጣም ብዙ በጎ ነገሮችን ሰጠንህ።**" ማለትም፡ በርካታ ኸይርና ታላላቅ ችሮታን፤ ከጥቅሉም አሏህ ለነብዩ ﷺ በዕለተ ትንሳኤ የሚለግሳቸው "አል-ከውሠር" የሚባል ጅረት፤ ርዝመቱ የአንድ ወር፣ ስፋቱ የአንድ ወር ያክል የሆነ፤ ውሃው ከወተት የነጣ፣ ከማር የጣፈጠ መጠጫው ያላቸው ብዛትም ድምቀትም እንደሰማይ ከዋክብቱ የሆነ፤ ከሱ አንድ ጊዜ የተጎነጨ ጥማት ለዘልአለሙ የማይነካው የሆነን ባህር ሰጠሁ እያላቸው ነው።

(2) የዋለለትን ፀጋ ባወሳለት ግዜ እንዲያመሰግንም አዘዘው። እንዲህም አለው፡ "**ስለዚህ ለጌታህ ስገድ፤ (በስሙ) ሰዋም።**" እነዚህን ሁለቱን የአምልኮ አይነቶች ለይቶ ያወሳቸው ከአምልኮ በላጮቹና የመቃረቢያ ቁንጮዎቹ በመሆናቸው ነው። እንዲሁም ሶላት በልቦና እና በአካል ለአሏህ መተናነስን ያካተተች፤ በአምልኮ አይነቶች መዘዋወርን የያዘች በመሆኗ እና በእርድ ደግሞ ባርያ ዘንድ ባለው ውድ የእርድ ነገር መቀራረብን፤ ነፍስ በስስትና በውዴታው ላይ ሁና የተፈጠረችበትን ገንዘብ ማውጣት ስላለበት ነው።

**(3) "ጠይህ (የሚጠላህ)... "** ማለትም፡ አንተን ጠይ፣ ወቃሽህና አንተ ዝቅዝቅ የሚያደርግ "... **እርሱ በእርግጥ (ዘሩ) የተቆረጠው ነው።"** ማለትም፡ ከመልካም ነገር ሁሉ የተቆራረጠው፤ ስራውም የተቆረጠ መወሳቱም የተቆረጠ ነው። ነብዩ ሙሓመድማ ﷺ በርግጥም በትክክል የተሟላው ነው። ለፍጡራን ሊኖራቸው ከሚችል ከፍ ያለ መወሳት፣ የረዳትና የተከታይ ብዛት በተሟላ መልኩ ያላቸው ናቸው።

☼☼☼☼☼

## የሱረቱ አል-ካፊሩን ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በላቸው «እናንተ ከሓዲዎች ሆይ! 1. «ያንን የምትግገዙትን (ጣዖት አሁን) አልግገዛም። 2. «እናንተም እኔ የምግገዛውን (አምላክም አሁን) ተገዢዎች አይደላችሁም። 3. «እኔም ያንን የተገዛችሁትን (ወደፊት) ተገዢ አይደለሁም። 4. «እናንተም እኔ የምግገዛውን (ወደፊት) ተገዢዎች አይደላችሁም። 5. «ለእናንተ ሃይማኖታችሁ አልላችሁ። ለእኔም ሃይማኖቴ አለኝ። 6.)**

---

(1-6) ማለትም፡ ለከሃዲያን ግልፅ አድርገህ በማሳወቅ እንዲህ በላቸው "**«ያንን የምትግገዙትን (ጣዖት አሁን) አልግገዛም።**" ማለትም፡ ከአሏህ ውጭ በድብቅም ሆነ በጉልህ ከሚያመልኩት መጥራራቱ ነው። "**«እናንተም እኔ የምግገዛውን (አምላክም አሁን) ተገዢዎች አይደላችሁም።**" አሏህን በመገዛት በኩል ኒያችሁ የጠራ ባለመሆኑ ይህ ከሽርክ ጋ የተቆራኘው አምልኳችሁ አምልኮ የሚባል አይደለም። ይህንንም ደጋግሞ ገለፀው፤ የመጀመሪያው ድርጊቱ እንደሌለ ለመጠቆም ሁለተኛው ደግሞ ጭራሽ የማይነጠል መገለጫ ባህርይ እንደሆነ ለመጠቆም ነው። ለዛም ነው በሁለቱ ጎራዎች መካከል ለያያቸውም ልዩነታቸውንም አስቀመጠ፤ እንዲህ በማለት፡ "**«ለእናንተ ሃይማኖታችሁ አልላችሁ። ለእኔም ሃይማኖቴ አለኝ።**" ልክ በሌላኛው አንቀፅ እንዲህ እንዳለው "«ሁሉም በሚመስለው መንገዱ ላይ ይሠራል። ጌታችሁም እርሱ መንገዱ ቀጥተኛ የኾነውን ሰው ዐዋቂ ነው በላቸው።" ስለዚህ እናንተም እኔ ከምሰራው የተጥራራችሁ ናችሁ እኔም እናንተ ከምትሰሩት የተጥራራሁኝ ነኝ።

☼☼☼☼☼

## የሱረቱ አል-ነስር ማብራሪያ፤ ሱራዋ መደንይ ነች

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (የአላህ እርዳታና (መካን) መክፈት በመጣ ጊዜ፤ 1. ሰዎችንም ጭፍሮች እየኾኑ፤ በአላህ ሃይማኖት ውስጥ ሲገቡ ባየህ ጊዜ፤ 2. ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው። ምሕረትንም ለምነው። እርሱ ጸጸትን በጣም ተቀባይ ነውና። 3.)**

---

(1-3) ይህች የተከበረች ሱራ የምስራች፣ በተከሰተም ጊዜ ለመልዕክተኛው ትእዛዝና ይህን ተከትሎ ለሚመጣው ጥቆማና ማመላከትን ይዛለች። የምስራቿ አሏህ መልዕክተኛውን እንደሚረዳ፣ የመካ መከፈት፣ ጠላት ከነበሩ በኋላ ከራሱ ሰዎች፣ ከረዳቶቹ ሆነው የሰዎች "**ጭፍሮች እየኾኑ፤ በአላህ ሃይማኖት ውስጥ ሲገቡ**" እንደሚያይ የምትጠቁመዋ የምስራች ነች። ይህ የምስራች በተጨባጭ የታየ ነው።

ከመካ መከፈት እና ከአሏህ እርዳታ በኋላ ያለው ትእዛዝ ደግሞ አሏህ መልዕክተኛው ﷺን በዚሁ ላይ እንዲያመሰግነው (ሹክር እንዲያደርስ)፣ እሱን በማመስገን እንዲያልቀውና መሃርታውንም እንዲጠይቀው ማዘዙ ነው።

ከጥቆማው በኩል ደሞ ሁለት ጥቆማዎች ይዟል። አሏህ ለዲኑ ያለው እርዳታ አሏህን (ከማይገባው ሁሉ)ማጥራት እና ከነብዩ ﷺ መሃርታን መጠየቅ በተገኘ ቁጥር ሁሉ ይዘልቃልም ይጨምራልም። ምክንያቱም ይህ ሹክር ከማድረግ በመሆኑ ነው። አሏህ ﷻ እንዲህ ይላል: "ብታመሰግኑ በእርግጥ እጨምርላችኋለሁ"። በርግጥም ይህ ነገር በዚህ ህዝብ በቅን ተተኪዎቹ (ኹለፋኡ ራሺዱን) ጊዜም ሆነ ከዛም በኋላ ባሉት የተገኘ ነገር ነው። ዲነል ኢስላም የትኛውም ሃይማኖት ባልዘለቀበትም በአሏህ እርዳታ ዘላቂ ከመሆን አልተወገደም። በሌላው ያልገባውም በሱ ገብቷል፤ ከህዝቡ ከራሱ የአሏህን ትእዛዝ ከመቃረን በኩል የተከሰተው እስከተከሰተበት ጊዜ ድረስ። የዚያኔ በንግግር መለያየት፣ በጉዳይ መበታተን ተፈተኑ፤ የተከሰተውም ተከሰተ፤ ይህ ከመሆኑም ጋ ለዚህ ኡማ እና ለዚህ ዲን በአእምሮ ውል የማይል በህሊና ዝር የማይል ልዩ የሆነ የአሏህ እዝነትና ርህራሄ አለው። ሁለተኛው ጥቆማ ደግሞ የነብዩ ﷺ የሞት ቀጠሮ መቃረቡን ጠቋሚ ነበር፤ ይህም የነብዩ ﷺ እድሜ ከሌላው እድሜ የተለየ በላጭነት ያለው በመሆኑ አሏህ የማለበት ነው። እንደሰላት፣ ሓጅን ሌሎችም በላጭ የሆኑ ነገራቶች ደግሞ መደምደሚያቸው መሃርታ መጠየቅን በመሰሉ መሆኑ የተለመደ ነው፤ ታድያ አሏህም መልዕክተኛውን ﷺ የእድሜው መቋጫ መቃረቡን ለመጠቆም በማመስገንና መሃርታን በመጠየቅ አዘዘው። የአሏህ ሰለዋትና ሰላም በሳቸው ላይ ይስፈንና በእድሜያቸው ከሚያገኙት በላጭ በሆነው ሁኔታ ጌታቸውን ለመገናኘት፣ ሊዘጋጁና ሊመቻቹ ዘንድ። እሳቸውም ﷺ እንደልማዳቸው የቁርአንን መልዕክት ወደ ተግባራዊነት ያዞሩትና በሰላታቸው ይሉት ነበር፤ በሱጁድም ሆነ በሩኩዓቸው *"ጌታየ ሆይ! ምስጋናም ጥራትም አሏህ ሆይ ላንተ የተገባ ነው፤ መሃርታህንም ለግሰኝ።"*

✪✪✪✪✪

**የሱረቱ አል-መሰድ(ተበት የዳ) ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች**

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (የአቡ ለሀብ ሁለት እጆች ከሰሩ (ጠፉ፤ እርሱ) ከሰረም። 1. ከእርሱ ገንዘቡና ያም ያፈራው ሁሉ ምንም አልጠቀመውም። 2. የመንቀልቀል ባለቤት የኾነችን እሳት በእርግጥ ይገባል። 3. ሚስቱም (ትገባለች)፤ እንጨት ተሸካሚ ስትኾን። 4. በአንገትዋ ላይ ከጭረት የኾነ ገመድ ያለባት ስትኾን። 5.)**

አቡ ለሃብ ማለት የነብዩ ﷺ አጎት ነው። እጅግ ጠላትነቱ የበረታና አስቸጋሪው ሰው ነበር፤ አሏህ ለጥፋት ይበለውና በዱኑም የለበትም ለዝምድናውም የማያሳስበው ነበር፤ አሏህም በእንዲህ አይነቱ እስከእለተ ትንሳኤ ድረስ በሚያዋርድ ከባድ ወቀሳ ወቀሰው፤ እንዲህም አለ
(1) "**የአቡ ለሀብ ሁለት እጆች ከሰሩ (ጠፉ፤**" ማለትም፡ እጁም ከሰረ እድለቢስ ሆነም፤ "... **(እርሱ) ከሰረም።**"
(2) "**ከእርሱ ገንዘቡ ...ምንም አልጠቀመውም።**" ያ የነበረውና ድንበር እንዲያልፍ ያደረገው "**... እና ያም ያፈራው ሁሉ**" የአሏህ ቅጣት በመጣበት ጊዜ አንዳችንም ነገር አልመከተለትም።
(3-5) "**የመንቀልቀል ባለቤት የኾነችን እሳት በእርግጥ ይገባል።**" ማለትም፡ እሳት ከየአቅጣጫው ታካብበዋለች፤ እሱም ሆነ "**ሚስቱም (ትገባለች)፤ እንጨት ተሸካሚ ስትኾን።**" እሷም በበኩሏ ለአሏህ መልዕክተኛ ﷺ እጅግ ብርቱ አስቸጋሪ ነበረች። እሷም ከባሏ ጋ በወንጀልና በጠላትነት ትተባበራለች፣ ክፋትን ትነዛለች፣ የአሏህ መልዕክተኛን ﷺ ለማስቸገር እስከችሎታዋ ጥግ ድረስ ትለፋለች። ልክ አንገቱ ላይ "... **ከጭረት የኾነ ...**" ገመድ ተቋጥሮለት እንጨት በሚሰበስብ ሰው አኳኋን እሷም በጫንቃዋ ወንጀልን ትሸከም ነበር። ማለትም፡ ከቃጫ በሆነ። ወይም ደግሞ እሷ አንገቷ ላይ ከጭረት የተገመደ ገመድ ተቋጥሮላት በእሳት ውስጥም በባሏ ላይ ማገዶ ትጭንበታለች።
ያም ሆነ ይህ፡ በዚህ አንቀፅ ላይ ከአሏህ አስደናቂ ምልክቶች መካከል ይገኝበታል። አሏህ ይህን ሱራ ያወረደው አቡ ለሃብና ባልተቤቱ ህያው ሳሉ ነበርና፤ እነሱም እሳት ውስጥ የሚቀጡ መሆናቸው የማይቀርለት ጉዳይ መሆኑንም አሳወቀን፤ ኢስላምን አለመቀበላቸውም ግድ የሚል ጉዳይ ነበር፤ ነገሩም ታድያ ግን የቅርቡንም የሩቁን የሚያውቀው ጌታ ባለው መልኩ ነበር የተከሰተው።

✪✪✪✪✪

**የሱረቱ አል-ኢኽላስ ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች**

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በል «እርሱ አላህ አንድ ነው። 1. «አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። 2. «አልወለደም፤ አልተወለደምም 3. «ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።፡» 4.)**

---

(1) ማለትም፡ "**በል**" ቁርጥ ባለ መልኩ ታምኖበት፤ ትርጉሙንም አምኖ በመቀበል፤ "**«እርሱ አላህ አንድ ነው።**" (በል)። ማለትም፡ አሃዳዊነት በሱ በቃ! በምሉእነት የተነጠለ አሃዳዊነት ያለው ነው። ያ መልካም ስሞችና የተሟላ ልእል ባህርያት እንዲሁም ፍፁም ድርጊቶች ያሉት፤ ያም ብጤም ሆነ አምሳያ የሌለው ነው።

(2) “**«አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው።**” ማለትም፡ በሚፈለገው ነገር ሁሉ ታሳቢው፤ የላይኛውም ሆነ የታችኛውም አለም ባለቤት ሁሉ ጥግ በደረሰ ትህትና የሚፈልጉት፤ በባህርያቱ የተሟላ በመሆኑ ጉዳያቸውን ይጠይቁታል፤ በሃሳባቸው ሁሉ ይከጅሉታል። ያ በእውቀቱ የተሟላ “አል-ዓሊም”፤ ያ ቻይነቱ የተሟላ የሆነ “አል-ሓሊም”፤ ያ በእዝነቱ የተሟላ የሆነ እንዲሁም ሁሉንም ነገር ያካበበች እዝነት ባለቤት የሆነ “አርረሒም” ነው፤ በሌሎች ባህርያቱም እንዲሁ (የተሟላ ባህርይ ባለቤት) ነው።

(3) ከምሉእነቱም አንፃር እሱ “**«አልወለደም፤ አልተወለደምም**” በራስ መብቃቃቱ የተሟላ ነውና።

(4) “**«ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።።»**” ከፍ ያለው የላቀው አሏህ በስያሜውም ይሁን፤ በባህርያቱም በድርጊቱም ቢሆን (አንድም ብጤ የለውም)።

ይህች ሱራ አሏህ ከስምና ባህርያቱ አንፃር ያለውን አሃዳዊነት በሙሉ አጠቃልላ ይዛለች።

✪✪✪✪✪

**የሱረቱ አል-ፈለቅ ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች**

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በል «በተፈልቃቂው ጎህ ጌታ እጠበቃለሁ። 1. «ከፈጠረው ፍጡር ሁሉ ክፋት። 2. «ከሌሊትም ክፋት ባጨለመ ጊዜ፤ 3. «በተቋጠሩ (ክሮች) ላይ ተፊዎች ከኾኑት (ደጋሚ) ሴቶችም ክፋት። 4. «ከምቀኛም ክፋት በተመቀኘ ጊዜ፤ (እጠበቃለሁ በል)።» 5.)**

---

(1) ማለትም፡ ጥበቃን በመሻት መልኩ “**«በተፈልቃቂው ጎህ ጌታ**” ማለትም፡ የፍሬውም የአዝርእቱም አስገኝ፤ የንጋቱም አስገኝ (በሆነው ጌታ) “**እጠበቃለሁ**” ማለትም፡ እጠጋለሁ፤ እከለላለሁ፤ አጥብቄ እይዛለሁ፤ “**በል**”።

(2) “**«ከፈጠረው ፍጡር ሁሉ ክፋት።**” ይህ የፈጠረውን ፍጡር ሰውንም ይሁን ጅኑንም፤ እንስሳቱንም፣ በሙሉ የሚያጠቃል ሲሆን እሷ ዘንድ ካለው ክፋት በፈጣሪዋ መጠበቅ ማለት ነው።

(3) ጥቅል አድርጎ ከገለፀ በኋላ ለይቶ አመጣ እንዲህም አለ፤ “**«ከሌሊትም ክፋት ባጨለመ ጊዜ፤**” ማለትም፡ ሌሊቱ ሰዎችን ባጨለመ ጊዜ፤ በርካታ ክፉ መናፍስትና አስቸጋሪ እንስሳት በሚሰራጭበት ጊዜ ከሚሆነው ሁሉ።

(4) “**«በተቋጠሩ (ክሮች) ላይ ተፊዎች ከኾኑት (ደጋሚ) ሴቶችም ክፋት።**” ማለትም፡ እነዚያ ድግምቱ ላይ በሚቋጥሩት የድግምታቸው ቋጠሮ ክሮች ላይ በመትፋት ለድግምታቸው ከሚታገዙት ሴት ደጋሚዎች ክፋት፤

(5) “**«ከምቀኛም ክፋት በተመቀኘ ጊዜ፤ (እጠበቃለሁ በል)።»**” ሓሲድ(ምቀኛ) ማለት ከተመቀኘው ሰው ያለን ፀጋ እንዲወገድ የሚመኝ ነው። ለዛም ፀጋው እንዲወገድ የሚችለውን ነገር ያደርጋል።ስለዚህም ከክፋቱ ለመዳንና ተንኮሉን ውድቅ ለማድረግ በአሏህ መጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ።

ቡዳ(የሰው አይን)ም በምቀኛ ስር የሚካተት ነው፤ ምክንያቱም የሰው አይን (አይቶ አሏህ በረካ ያድርግለት ከማይል) ከክፉ ፍጥረት የገማ ነፍስ ምቀኛ እንጅ አይመነጭምና።ይህች ሱራ ከጥቅሉም ይሁን ከዝርዝር የክፋት አይነቶች ሁሉ በአሏህ መጠበቅን አጠቃልላ ይዛለች። እንዲሁም ድግምት እውነትነት ያለው ክፋቱ የሚሰጋ በመሆኑ ከሱም ሆነ ከሰሪዎቹ የአሏህ ጥበቃ የሚያስፈልገው መሆኑንም ትጠቁማለች።

**የሱረቱ አል-ናስ ማብራሪያ፤ ሱራዋ መደንይ ነች**

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በል «በሰዎች ፈጣሪ እጠበቃለሁ። 1. «የሰዎች ሁሉ ንጉሥ በኾነው። 2. «የሰዎች አምላክ በኾነው። 3. «ብቅ እልም ባይ ከኾነው ጎትጓች (ሰይጣን) ክፋት። 4. «ከዚያ በሰዎች ልቦች ውስጥ የሚጎተጉት ከኾነው። 5. «ከጋኔኖችም ከሰዎችም (ሰይጣናት እጠበቃለሁ በል)።» 6.)**

---

(1-6) ይህች ሱራ ከሸይጧን በሰዎች ጌታ፣ በንጉሳቸውና በአምላካቸው (አሏህ) ጥበቃ መሻትን አካትታለች። ያ የክፋቶች ሁሉ መሰረትና መሳሪያም ጭምር የሆነው፤ ያም ካለው ፈትና እና ክፋት አንፃር "**«ከዚያ በሰዎች ልቦች ውስጥ የሚጎተጉት ከኾነው።**" ክፋትን ያስውብላቸዋል፤ እሱኑ መልካም እንደሆነ አስውቦ ያሳያቸዋል፤ እንዲያደርጉትም ፍላጎታቸውን ያነሳሳል። ከበጎ ነገርም ደግሞ ስነልቦናቸውን ይጎዳባቸዋል፤ ካለው ምንነት በተለየ መልኩ አድርጎ ያሳያቸዋል፤ እሱ ሁሌም እንዲሁ ነው ሁኔታው። ይወሰውስ ይወሰውስና መልሶ ደሞ ይደነዝዛል፤ ማለትም፡ አንድ ባርያ ጌታውን አስታውሶ ለመመከቱ በጌታው ከታገዘ ከመወስወስ ስራው ይስተጓጎላል። በመሆኑም በሰው ልጆች ሁሉ ጌታ በአሏህ ሊታገዝ፣ ጥበቃውን ሊጠይቅና ሊከለል ይገባዋል። ፍጡራን ሁሉ በጌትነቱና በንግስናው ስር ናቸው። በዛች ለሷው ሲባል በፈጠረበትም ምክንያት የሁሏንም ተንቀሳቃሽ አናት የያዘው እሱው ነው። እሷም ከሷው ማቆራረጥና በነሱና በሷ መካከል ግርዶሽ መሆን፤ አብረውት የእሳት ጓዶች ይሆኑ ዘንድ የሱ ጭፍሮች ማድረግም  የሚፈልገውን ጠላታቸውን በመገፍተር እንጅ የምትሟላ አይደለችም። ወስዋስ (መወትወት) ከሰው ልጅ እንደሚሆነው ሁሉ ከሰው ልጅም ይሆናል። ለዚህም ነው፡ "**«ከጋኔኖችም ከሰዎችም (ሰይጣናት እጠበቃለሁ በል)።»**" ያለው።

ከጅምሩ እስከ ከፍፃሜው፤ በጉልሁም ሆነ በድብቁም ሁሉ ምስጋና ለሱ የተገባ ነው። ፀጋውን ሙሉ ሊያደርግልን ዘንድ አሏህን እንጠይቀዋለን። ከሱ በርካታ ፀጋ ግርዶሽ የሆነችንን ወንጀላችንንም፤ አንቀፆቹን ከማስተንተን ልባችንን ያጠፋችውን ማንዳለጥና ስሜትንም መሃርታውን ይለግሰን ዘንድ እንጠይቀዋለን። እኛ ዘንድ ባለ ክፋት እሱ ዘንድ ያለን በጎ እንደማይነፍገን እንከጅለዋለን ከሱም ተስፋ እናደርጋለን። ምክንያቱም ከከሃድያን ህዝቦች በቀር ከአሏህ ርህራሄ ተስፋ የሚቆርጥ የለምና። ከጠማሞችም በቀር ከሱ እዝነት ተስፋ አይቆርጥምና። የአሏህ ሶለዋትና ሰላም በመልዕክተኛው ሙሐመድ፣ በተከታዮቹና በባልደረቦቹም ሁሉ ላይ ይስፈን፤ ዘላለሙን የተቀጣጠለ ዘላቂነት ያለው ሶለዋትና ሰላም። ምስጋናም ባጠቃላይ መልካም ነገር ሁሉ በፀጋው ሙሉ ለሚሆነው ይሁን።

## የመግቢያውና የተፍሲሩ ፈተና

1. የ "አሳሳቢ ትምህርቶች ለብዙሃኑ ህዝብ" ፀሃፊ ማን ነው?

O ሸይኽ ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ O ሸይኽ ሙሓመድ ቢን ዑሠይሚን O ሸይኽ ሀይሠም ሰርሓን

2. ለምንድን ነው ስለ "አሳሳቢ ትምህርቶች ለብዙሃኑ ህዝብ" የምንማማረው?

O አሳሳቢ ስለሆነች O ምክንያቱም ዑለሞች ትኩረት እንዲሰጣት አደራ ስላሉ

O ለአንድ ሙስሊም አስፈላጊ የሆኑ አሳሳቢ ነገራቶችን ስላካተተች

O ሁሉም መልስ ነው

3. ይህ ፅሁፍ የሚዳስሰው ስለ:

O አንድ ሙስሊም ከቁርአንና ከተውሒድ ጋ በተያያዘ ያለውን ሁኔታ

O የስርዓትና የስነምግባር ርእሶችን O ሙታንን ስለ መገነዝ O ስለሶላትና ዉዱእ

O ከወንጀል ስለማስጠንቀቅ O ሁሉም መልስ ነው

4. አንድ ሙስሊም ቁርአንን እንዴት እንደሚነበብ፣ እንዴት አስተካክሎ መቅራት እንዳለበት፣ እንዴት መሓፈዝ እንዳለበት መጀመር የሚገባው በ:

O ሱረቱ አል-ዓለቅ O በሱረቱ አል-ፋቲሓ O በሱረቱ አል-ኢኽላስ

5. ሰዎች ቁርአንን ከማስተንተንና በሱ ከመስራት ጋ በተያያዘ ባላቸው አቋም ወደ ሁለት ጠርዝ እና አንድ ሚዛናዊ ይከፈላሉ ( እውነት – ሃሰት )

6. አንድ ተማሪ መጀመር ያለበት በየትኛው የተፍሲር ኪታብ ነው?

O ኢብን ከሢር O አስ-ሰዕዲይ O አል-ቁርጡቢይ

7. አንድ ተማሪ መጀመር ያለበት በአጫጭሮች ሲሆን በሂደት ነው ወደ ረዣዥሞቹ መሄድ ያለበት ( እውነት – ሃሰት )

8. አንድ ተማሪ ከተፍሲር ኪታቦች መማርን መጀመር ያለበት በዘወትርና በመደጋገም እንዲያነብ በሚያነሳሳው በሱረቱል ቀሶስ፣ መርየምና አል-ከህፍ መሰል ሱራዎች ነው። ( እውነት - ሃሰት)

9. አንድ ተማሪ ራሱ ተፍሲርን ለማንበብ የሚያስቸግረው ከሆነ ለማዳመጥ በተዘጋጁ( تفسير السعدي من تفسير القران الصوتي አይነቱን ) የኪታብ ንባብ ቅጅዎች ማዳመጡ ይመከራል ( እውነት – ሃሰት )

10. ነብዩ ﷺ ቁርአን እየቀሩ ትርጉሙን አለማስተንተንን አስጠንቅቀዋል (እውነት – ሃሰት )

## ከሱረቱል ፋቲሓ ማብራሪያ የተውጣጡ ጥያቄዎች

11. ሱራዋ በዚህ ስያሜ የተጠራችው ከሷም እንዳይወጣም ወደሷ እንዳይገባም በሚገታ መልኩ የታጠረች በመሆኗ ነው። (እውነት – ሃሰት)

12. ሱረቱል ፋቲሓ የተባለችበት (ተጨማሪ) ምክንያት…

........................................................................................

13. ከሱረቱል ፋቲሓ ሌሎች ስያሜዎች መካከል:

O ኡሙል ቁርአን (የቁርአኑ እናት) O አስሰብዐል መሣኒ (ሰባቱ የሚደጋገሙ)

O አስ-ሶላት (ሶላቲቷ) O ሩቃ(ፈውስ) O ሁሉም መልስ ነው።

14. አሏህን በማመፅ ሳይሆን አሏህን በመታዘዝ ላይ እንኳ ቆይተን ቁርአን ከመቅራታችን በፊት የአሏህን ጥበቃ መሻት (“አዑዙ ቢላሂ” ማለትን ይመስል) ግዴታ ነው። ምንድን ነው ምክንያቱ?

........................................................................................

....................................................................................

15. *'አዑዙ'* የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው?

........................................................................................

16. *ለምንድን ነው ሸይጧን አር-ረጂም(ቅጥቅጡ የተረገመው)* የሚባለው…

O የተረገመ ማለትም ከአሏህ እዝነት የተባረረ ስለሆነ O . በተወንጫፊ ከዋክብት ስለሚቀጠቀጥ O የሰው ልጅን በስሜትና በውዥንብር ስለሚቀጠቅጥ(ስለሚመታ) O ሁሉም መልስ ነው

17. **አሏህ...**

O በውዴታና በማላቅ ተመላኪ አምላክ ነው

O ከሱ ውጭ በዚህ ስያሜ የተጠራ አንድም የለም

O ለአሏህ ስያሜዎች ሁሉ መንደርደሪያ ነው

O የአሏህ ታላቁ ስያሜው ነው።

O ሁሉም መልስ ነው።

18. ***አር-ራሕማን*** *እና* ***አር-ረሒም*** በሚሉት ሁለቱ የአሏህ መልካም ስያሜዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

.............................................................................

..........................................................................

19. ከፍ ያለው አሏህ ፍጡራኑን የሚንከባከበው በሁለት መልኩ ነው፤ በምን እና በምን?

O ጥቅል እና ልዩ O የተገደበ እና ያልተገደበ

20. አብዛኞቹ የነብያት ዱዓ __________ በሚል ነው።

O አሏህ ሆይ! O ያ ረብ (ጌታየ)!

21. የ *"ዲን"* እለት ማለት...

O የትንሳኤ እለት O. ሰዎች በስራቸው የሚመነዱበት እለት O ሁሉም መልስ ነው

22. **"ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።"** እጅግ ሰብሳቢውና ጠቃሚው ዱዓ ነው (እውነት –ሃሰት)

23. አድ-ዲን የሚለው የዓረብኛ ቃል የሚገልፀው

O ምንዳን O ስራን O . አንዳንዴ ስራውን አንዳንዴም ምንዳውን

24. (እንደ ዓረብኛ ሰዋሰው) ድርጊት ተቀባዩን ከድርጊት ፈፃሚው ማስቀደም ፋይዳው ...

O መገደብን (የተጠቀሰው ድርጊት በፈፃሚው ላይ ብቻ የተገደበ መሆኑን) O ምንም

25. **'አምልኮን'** ከ **'እገዛ መሻት በፊት'** መወሳቱ ______ከ ____ እንደማስቀደም ነው:

O ጥቅል የሆነውን ነጠላ ከሆነው O የራሱን መብት ከባርያው መብት O ሁሉም

26. **"አንተን ብቻ እንግገዛለን፤"** የሚለው አንቀፅ ለምንድን ነው ጥቅል በሆነ አገላለፅ የመጣው?

..........................................................................................

27. **ዒባዳ (አምልኮ)** ...

O ከጉልሁም፣ ከድብቁም፣ ውጫዊም ይሁን ውስጣዊ፣ ከንግግርም ይሁን ከተግባር አሏህ የሚወደውንና የሚደሰትበትን ሁሉ የሚያጠቃልል ስም ነው።

O በመውደድና በማላቅ መልኩ ትእዛዛትን በመፈፀምና ክልክላትን በመቆጠብ ለአሏህ መተናነስ ነው።

O አንዳንዴ ይህን ይፈለግበታል አንዳንዴ ደግሞ ሌላኛው ይፈለግበታል(ሀ እና ለ)

28. **"ምራን"** በሚለው የሃያሉ አሏህ ቃል የተፈለገበት ምራቻ ...

O መጠቆም እና ማመላከት O ተውፊቁን መግጠም O ሁሉም መልስ ነው

29. **"የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን "** በሚለው ቃል የተፈለገበት... O ከዚህ ህዝብ አማኝ የሆነው ሁሉ O ከነብያቶች፣ ከሲዲቆች፣ ከሸሂዶችና ከሷሊሑች የሆኑትን በጎ የዋለላቸውን

30. **"አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን።"** የሚለው አንቀፅ ሸሪዓንና ቀደርን መሰብሰብን አቅፏል ( እውነት – ሃሰት )

31. ከሚከተሉት መካከል የትኛዋ ነች ሌሎቹ ያላካተቱትን የቁርአን ክፍል በይበልጥ ያካተተች?

Oሱረቱል ፋቲሓ Oአየቱል ኩርሲይ Oሱረቱል ኢኽላስ

32. **"... መንገድ ምራን።"** የሚለው የአሏህ ቃል ከሚያካታቸው መካከል...

O ነብይነት የሚባለውን እውነታ ማፅደቅ O በመላ የቢድዓ እና የጥመት ባለቤት ላይ ምላሽ መስጠት O ሁሉም መልስ ይሆናል

33. **"የፍርዱ ቀን ባለቤት"** የሚለው የአሏህ ቃል ከሚያካታቸው መካከል...

O ምንዳ የሚሆነው በፍትህ እንደሆነ O አንድ ባርያ የሚሰራው ስራ በተጨባጭ የ/በራሱ እንደሆነ O ቀድመው የተጠቀሱት ሁሉ መልስ ናቸው O ምንዳ በስራ ብቻ እንደሆነ

## ፈተና ከአየተል ኩርሲይ አንቀፅ ማብራርያ

34. ለአየቱል ኩርሲይ አንቀፅ ይህ ስያሜ የተሰጣት ***ኩርሲይ*** የተጠቀሰበት አንቀፅ ስለሆነች ነው ( እውነት – ሃሰት )

35. በቁርአን ውስጥ ታላቋ አንቀፅ የትኛዋ ነች? O ስለእዳ የምትዳስሰዋ አንቀፅ O . አስሩ መብቶች የተወሳባት አንቀፅ Oአየተል ኩርሲይ

36. ቁርአን ከመልዕክት አንፃር ልዑል ነው ( እውነት – ሃሰት )

37. ከአሏህ መልካም ስያሜዎች መካከል በአየተል ኩርሲይ ላይ የተወሱት የአሏህ ስያሜዎች ስንት ናቸው?

O አምስት O ስድስት O ሰባት

38. "**ሕያው**" የሚለው የአሏህ ስም ከምን አንፃር ምሉእነትን ይዟል...

O አካላዊ O ስልጣናዊ

39. "**ራሱን ቻይ**" የሚለው የአሏህ ስም ከምን አንፃር ምሉእነትን ይዟል...

O አካላዊ O ስልጣናዊ

40. "**ሕያው**" እና "**ራሱን ቻይ**" የሚሉት ቃላት በሚቆራኙበት ጊዜ ስልጣናዊ እና አካላዊ ምሉእነትን ይጠቁማሉ። ( እውነት – ሃሰት )

41. "**ሕያው**" እና "**ራሱን ቻይ**" የሚሉት የአሏህ ስያሜዎች በቁርአን ላይ ተቆራኝተው የተደጋገሙበት ቦታ፡ ...

O በሶስት ቦታ O በአራት ቦታ O በሁለት ቦታ

42. የውግዘት ባህርያትን አሏህ ከራሱ መልዕክተኛውም ከሱ እንዳወገዙት እኛም ልናወግዛቸው ግድ ነው፤ ተቃራኒው የሆነውን ምሉእነት ከማፅደቅም ጋ፤ ምክንያቱም ማውገዝ ብቻውን ምሉእነት አይደለምና። ለምሳሌ፡ ካለው የተሟላ "**ሕያው**" እና "**ራሱን ቻይ**" ማንነት አንፃር ማንገላጀትንና እንቅልፍን ከሱ እናወግዛለን (እውነት – ሃሰት )

43. አሏህ ለተደሰተበት ካልሆነ በቀር ለማንም በሽፈዓ አይፈቅድም፤ የሚደሰትም አይደለም

ከ_____ ሰዎች ቢሆን እንጅ።

O ተውሒድ O . የነብዩﷺ ሱና ተከታይ. O የተጠቀሱት ሁሉ መልስ ናቸው

44. አሏህ ፍጡራኑን ያሳወቃቸው ሸሪዓዊም ይሁን አለማዊ እውነታ…

O ትንሽ ነው O .ብዙ ነው

45. **"ከፊታቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል" አሁን** ያለው እና የወደፊቱን ማለት ሲሆን **"ከኋላቸው ያለውም"** ማለት ያለፈ ማለት ነው። (እውነት - ሐሰት)

46. "**አል-ዓልይ** (**የሁሉ በላይ…"**)" የሚለው የአላህ ስም ትርጉም፡

O በአካሉ O በባህርያቱ O ፍጡራንን ሁሉ አሸናፊ የሆነ O ሁሉም

47. ከመተኛቱ በፊት የሚያነበው ሰው ከአላህ ዘንድ የጠበቀ መከላከያም አለው፤ እስኪነጋም ድረስ ሸይጧን አይቀርበውም። ምንድን ነው?

O የሱራ አል-በቀራህ መጨረሻ አንቀፆች O አየተል ኩርሲይ

48. አየተል ኩርሲይን መቅራቱ ይመከራል… O ከግዴታ ሶላቶች በኋላ

O ከምኝታ በፊት O ጧትና ማታ O ሁሉም መልስ ነው

## የሱረቱል ዘልዘላህ ማብራርያ ፈተና

49. ሱረቱል ዘልዘላ … O መከይ ነች O መደንይ ነች

50. ሱረቱል ዘልዘላ በውስጧ ከያዘችው መካከል…

O ማስጠንቀቅ O ማበረታታት O ሁሉም መልስ ነው

51. "**ምድር (በኀይል) መንቀጥቀጥዋን በተንቀጠቀጠች ጊዜ፤"** የሚለው የአሏህ ቃል **«ትክክል ሜዳም ትኾናለች። በርሷ ላይ ዝቅታና ከፍታ የሌለባት»** ከሚለው ቃሉ ጋ ተነፃፃሪ ነው: ( እውነት- ሃሰት )

52. "**ምድርም ሸክሟን ባወጣችም ጊዜ**" ማለት O ተራራና ኮረብታዋን O ሙታንና ድልቧን

53. ምድር በባርያዎች ላይ ከሚመሰክሩ የመስካሪዎች ጎራ መካከል አንዷ ነች። (እውነት – ሃሰት)

54. **"የተለያዩ ኾነው"** የሚለው የአሷህ ቃል የተፈለገበት…

O እያንዳንዱ ራሱን ችሎ O የሚበላለጡ ጎራዎች

55. **"የብናኘ ክብደት ያክልም መልካምን የሠራ ሰው ያገኘዋል።…"** የሚለው የአሷህ ቃል "የሰሩትንም ነገር ሁሉ ቀራቢ ኾኖ ያገኙታል።…" እንደሚለው የአሷህ ቃል ነው (እውነት – ሃሰት)

## ከሱረቱል ዓዲያት ማብራርያ ፈተና

56. ሱረቱል ዓዲያት … Oመደንይ ነች Oመክይ ነች

57. *"ዓዲያት"* የሚለው ቃል ትርጉም …

O ፈረሶች O ተንቀሳቃሽ ሁሉ Oሁሉም መልስ ነው

58. **ሱረቱል ዓዲያት** ግዴታ የሆኑ መብቶችን ያለመወጣትን ማስጠንቀቅን ይዛለች። (እውነት – ሃሰት)

59. የሚከተሉትን ቃላት ትርጉም ግለፅ:

*"ዶብሐን"*: ………………………………………………………………...

*"ቀድሐን"*: ………………………………………………………………...

*"ነቅዐን"*: ………………………………………………………………...

*"ለከኑድ"*: ……………………………………………………………...

## ከሱረቱ አል-ቃሪዓህ ማብራርያ ፈተና

60. ***ሱረቱል ቃሪዓህ*** … O መክይ ነች Oመደንይ ነች

61. ከሱረቱል ቃሪዓህ ተፈላጊ ነጥቦች መካከል ከ _____ ማስጠንቀቅን ይዛለች:

Oየእለተ ቂያማ አስደንጋጭ ሁኔታዎች O የዱንያ ፈተና

62. **አልቃሪዓህ** የተባለው ምኑን ነው O የዛቻ አንቀፆች O እለተ ትንሳኤ

63. የሚከተሉትን ቃላት ትርጉም አብራራ:

**"እንደ ተበታተነ ቢራቢሮ (ወይም ኩብኩባ)"** ……………………………………

"እንደ ተነደፈ ሱፍ " ..............................................................

64. በዝህች ሱራ የተወሳው **ሚዛን** ...O ትክክኛ ሚዛን. O የፍትህ ዘይቤአዊ ገለፃ

65. "በምትወደድ ኑሮ" ማለት O ዱንያ O ጀነት

66. "መኖሪያው ሃዊያህ ናት " ማለት:

O እንደማትለየው የሆነችው እናቱ ትሆናለች O መሃል አናቱ የእሳቱ ውስጥ ማገዶ ነች።

O ሁሉም መልስ ነው

67. "እርሷም ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ?!" የሚለው ቃሉ

O የጉዳዩዋን ከባድነት ለመጠቆም ነው O ጥያቄ ነው

68. አሏህ ይጠብቀንና ከእሳቲቱ ስያሜዎች መካከል:

| | | |
|---|---|---|
| Oአል ሃዊያህ | Oጀሃነም | Oአል ሑጦማህ |
| Oለዟ | O ሰዒር | Oሰቀር |
| Oሁሉም መልስ ነው | | |

69. "(እርሷ) በጣም ተኳሳ እሳት ናት።" –ከሷ በአሏህ እንጠበቃለንና- ቃጠሎዋ ከዱንያዋ እሳት ቃጠሎ በስንት እጥፍ ትበልጣለች?

O በሰባ O በዘጠና O በዘጠና ዘጠኝ

## ፈተና ከሱረት አት-ተካሡር ማብራርያ

70. ይህች ሱራ ... O መከይ ነች O መደንይ ነች

71. ይህች ሱራ በውስጧ ______ ይዛለች

O ስለሰዎች ሁኔታ መናገርን O የመፈጠራቸው አላማ ለመዘናጋታቸው ባርያዎቹን መውቀስን

72. ይህች ሱራ የተፈለገበት የአሏህ ፊት እንኳ ቢሆን መፎካከርን ትከለክላለች። (እውነት – ሃሰት)

73. ሰው ሲሞት "ወደ መጨረሻ መኖርያው ሄደ" የሚለው አገላለፅ:... O ከሞት በኋላ

መቀስቀስን ያወግዛል O ይቻላል

74. "እስከ ጎበኛችሁ ድረስ..." በሚለው ቃል ዘያሪዎች ብሎ ገለፃቸው እንጅ ነዋሪዎች ብሎ አይደለም የገለፃቸው። ለምን?

O የበርዘኽ(የቀብር) ህይወት ዋና እሳቤው ወደመጨረሻው ሃገር መሸጋገር የሆነ አገር በመሆኑ

O ከራሳቸው የሆነው የዱንያ መኖርያ ቤት የራሳቸው ወዳልሆነው የመቃብር ቤት ስለተሸጋገሩ

75. እውቀት ወደ ሶስት ይከፈላል፡ ተጨባጭ እውቀት፣ ተጨባጭ እይታ እና ተጨባጭ እውነታ (እውነት-ሃሰት)

## ከሱረቱ አል-ዓስር ማብራርያ ፈተና

76. ሱረቱል ዓስር... O መከይ ነች O መደንይ ነች

77. ሱረቱል ዓስር አራት ቁምነገሮችን ትጠቁማለች፡ እውቀት፣ ባወቁት መስራት፣ ጥሪ ማድግና ትዕግስት። ( እውነት – ሃሰት )

78. ከአሏህ ውጭ ባለ አካል መማልን በማስመልከት ትክክለኛው አገላለፅ የትኛው ነው?

O አሏህ ከፍጡራኑ በፈለገው መማል ይችላል O ፍጡራን ከአሏህ ውጭ ባለ አካል መማል አይችሉም O ፍጡራን ከአሏህ ውጭ ባለ አካል መማል ይችላሉ O የመጀምርያውና የሁለተኛው መልሶች ብቻ ትክክል ናቸው

79. **ትዕግስት** _____ ወደ ይከፈላል O ወደ ሁለት O ወደ ሶስት O ወደ አራት

80. ሱራዋ አራት ትዕዛዞች አሏት፤ ብሁለቱ ትዕዛዞች አንድ ባርያ ራሱን ሙሉ የሚያደርግበት ሲሆን በሌሎቹ ሁለቱ ደግሞ አንድ ባርያ ሌላውን ሙሉ የሚያደርግበት ነው። (እውነት – ሃሰት)

## የሱረቱል ሁመዛህ ማብራሪያ ፈተና

81. ይህች ሱራ... O መከይ ነች O መደንይ ነች

82. "ወይል" የሚለው ቃል ትርጉም...

O ጀሃነም ውስጥ ያለ ሸለቆ O ጀሃነም ውስጥ ያለን ሸለቆ እና ከዛም በላይ ያካተተ ዛቻ

83. አል-ሃምዝ የሚባለው በቃል የሚደረገውን ሲሆን አል-ለምዝ የሚባለው በድርጊት የሚደረገውን ትንኮሳ የሚመለከት ነው። (እውነት – ሃሰት)

84. "ገንዘቡ የሚያዘወትረው መኾኑን ያስባል።!" ከሚለው ቃሉ በጎነት በእድሜ የሚጨምር መሆኑን እንረዳለን። ( እውነት – ሃሰት )

85. "ምን አሳወቀህ?" ከሚለው ቃሉ የምንረዳው ነብዩ ﷺ... O ያውቋታል O አያውቋትም

86. ''የተነደደችው የአላህ እሳት ናት። '' በሚለው ከፍ ያለው አሏህ ቃሉ ላይ የእሳት ማገዶው... O ሰዎች O ድንጋይ O ሁለቱም መልስ ናቸው

87. "በልቦች ላይ የምትዘልቅ የኾነችው።" በሚለው ከፍ ያለው አሏህ ቃል የተፈለገው እሳቲቱ፡ O የሚታሰበው O ሰውነትና አልፋ ልቦና ድረስ ትዘልቃለች

## የሱረቱል ፊል ማብራሪያ ፈተና

88. ሱረቱል ፊል ሱራዋ ... O መካይ ነች O መደንይ ነች

89. በየብሱ ላይ ካሉት ፍጥረቶች ሁሉ ታላቋ ፍጥረት ከአሏህ ቤቶች መካከል በአንዱ እንኳ ድንበር እንዳታልፍ ትሰጋለች፤ የሰው ልጅ ደግሞ ለስጋቱ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። ( እውነት – ሃሰት )

90. ነብዩ ﷺ የተወለዱበት አመት በአረቦች የ_____ አመት ይባላል። O የዝሆን O የሃዘን O የድርቅ

91. ይህች ሱራ ከነብዩﷺ መላክ በፊት የነበረ ከተለምዶ ውጭ የሆነ ለሳቸው ሲባል የተገለፀ ነብያዊ ተአምሮች የሚካተት ነው። ( እውነት – ሃሰት)

92. የተከታዮቹን ሃረጎች ማብራሪያ ግለፅ:

"...መንጎች የኾኑን ዎፎች..."..............................................................

"... እንደ ተበላ አዝመራ..." .........................................................

## ከሱረቱል ቁረይሽ ማብራሪያ ፈተና

93. ***ሱረቱል ቁረይሽ***... O መከይ ነች O መደንይ ነች

94. ይህች ሱራ ከ____ ሱራ ጋ ቁርኝት አላት O አል-ካፊሩን O አል-ፊል O አን-ናስ

95. የቁረይሾች ጉዞ በክረምት ወደ ሻም በበጋ ደግሞ ወደ የመን ነበር። ( እውነት – ሃሰት )

96. አሏህ የመካን እና የሰዎቹን ክብር በሌሎች ዓረቦች ልቦና ዘንድ እስኪያከብሯቸውና እስከማይጋረጡባቸው ድረስ አልቋቸዋል። O በመካ ሳሉ O በመካም ጉዞም ላይ ሆነው

97. አሏህ ጌትነቱን ከካዕባ ጋ አቆራኝቶ ያመጣው ላለው ክብር እና በላጭነት እንጅ እሱ የሁሉም ጌታ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

98. **"ስለዚህ የዚህን ቤት (የከዕባን) ጌታ ይግገዙ፡፡"** የሚለው ቃል አገላለፅ ፍጡርን ከክብር አንፃር ወደ ፈጣሪ ማስጠጋት ነው። ( እውነት – ሃሰት )

## የሱረቱል ማዑን ማብራሪያ ፈተና

99. ሱረቱል ማዑን... O መከይ ነች O መደንይ ነች

100. "أَرَأَيْـتَ الَّـذِي يُـكَـذِّبُ بِـالـدِّيـنِ" በሚለው ከፍ ያለው አሏህ ቃል "ዲን" በሚለው የተፈለገበት... O ከሞት በኋላ መቀስቀስ እና መመንዳት O ግዴታንና መብቶችን ማውገዝ

101. "فَذَلِكَ الَّذِي يَدُعُّ الْيَتِيمَ" በሚለው የአሏህ ቃል 'يَدُعُّ' ማለት... O የሚተው O በጭካኔ የሚገፈትር

102. የቲም የሚባለው ________ የሞተበት ነው። O አባቱ O እናቱ

103. የቲም የሚባልበትም ... O ለአቅመ አዳም እስካልደረሰ O ቢያድግም

104. በሶላት ውስጥ መርሳት ባለቤቱ ሊወቀስበትና ሊወገዝበት የሚገባ የሆነው ሲሆን ሶላትን መርሳት ግን ከየትኛውም ሰው ሊከሰት የሚችል ጉዳይ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

105. ሪያእ(ይዩልኝ ይስሙልኝ) ኢስላማዊ ፍርዱ... O የተፈቀደ O የተወገዘ

O የተከለከለ(ሓራም) O ትንሹ ሽርክ O ትልቁ ሽርክ

106. በዚህ ሱራ ውስጥ ለሌሎች በጎ መዋልን የሚያበረታታ አለበት። ( እውነት – ሃሰት )

107. በአንቀፁ "الْمَاعُونَ" ("ትውስት")ተብሎ የተወሳው …

O መጣቀሚያ እቃ O መዋዋሱና መለጋገሱ ተለምዶ የሆነ ሁሉ

## የሱረቱ አል-ከውሠር ማብራሪያ ፈተና

108. ሱረቱ አል-ከውሠር... O መከይ ነች O መደንይ ነች

109. አል-ከውሠር የተባለው … O ጅረት ነው O ብዙ መልካም ነገርና ታላቅ ፀጋ ነው

110. አሏህ እነኝህን ሁለቱን የአምልኮ አይነቶች -ሶላትና እርድን- ለይቶ ያመጣቸው ከአምልኮ በላጮቹ እና ታላላቅ መቃረቢያዎች በመሆናቸው ነው። ( እውነት – ሃሰት )

111. "شَانِئَكَ" ማለት… O የሚጠላህ O የሚወቅስህ O የሚያሳንስህ O ሁሉም

112. "…እርሱ በእርግጥ (ዘሩ) የተቆረጠው ነው።" የሚለው የላቀው አሏህ ቃል የነብዩﷺ ወዳጅ የሆነ ሰው ትውስታ እና ውዳሴ እንደሚቀርለት ይጠቁማል። ( እውነት – ሃሰት )

113. ለነብዩﷺ በርካታ ረዳቶች እና ተከታዮች እንደሚኖሯቸው በሱራዋ ውስጥ ጥቆማ አለባት። ( እውነት – ሃሰት )

## የሱረቱል ካፊሩን ማብራሪያ ፈተና

114. ሱረቱል ካፊሩን ... O መከይ ነች O መደንይ ነች

115. ሱረቱ አል-ካፊሩን ከሱረቱል ፋቲሓ በኋላ በ______ ሶላት በመጀመሪያው ረከዓ መቅራቱ ይመከራል።

O ሱብሒ ሱና O በመግሪብ ሱና O በጡዋፍ ጊዜ በሚሰገድ ሱና

O በዊትር O ሁሉም መልስ ነው

116. ከሽርክ ጋ የተቆራኘ አምልኮ… O ያልተሟላ አምልኮ

O አምልኮ አይባልም

117. "በል" በሚለው የተፈለገው ለ_____ ነው። O ለነብዩ ﷺ

O ለነብዩም ﷺ በንንግሩ ሊፈለግበት ለሚያመቸውም ሁሉ

118. አልካፊሩን የተባሉት…

O የነብዩ ﷺ  ጥሪ ደርሷቸው ያላመኑት እንደ ክርስቲያንና አይሁድ መሰል ሁሉ

O የመካ ከሃዲያን

119. ይህች ሱራ ከሽርክ እና ጓዶቹ በልቦና፣ በአንደበትና በአካል በተጨባጭ መጥራራትን ይዛለች። ( እውነት – ሃሰት )

120. በሱራው ውስጥ (የአንዱ አንቀፅ) መደጋገሙ…

O ነገሩን ለማጠንከር ነው

O የመጀመሪያው የድርጊቱ አለመከሰትን የሚገልፅ ሲሆን የሁለተኛው ደግሞ መሰረታዊ መገለጫ ባህርይ እንደሆነ ለመጠቆም ነው።

## የሱረቱ አል-ነስር ማብራርያ ፈተና

121. ሱረቱ አል-ነስር …   O መካይ ነች   O መደንይ ነች

122. ይህች ሱራ በውስጧ የምስራች፣ መረጃ፣ ትእዛዝና ጥቆማ ይዛለች። (እውነት – ሃሰት)

123. አሏህ ለዚህ ህዝብ(ኡማ) እንዲሁም ለዚህ ዲን ከሚታሰበው በላይ እና በአእምሮ ውል ሊል በማይችልበት መልኩ እዝነትና ርህራሄ አለው። ( እውነት - ሃሰት )

124. በዝች ሱራ የነብዩﷺ የሞት ቀጠሮ እየተቃረበ እየተጠጋ መሆኑን ጥቆማ ይዛለች። (እውነት – ሃሰት)

125. የዚህን ሱራ ጭብጥ ተግባራዊ በማድረግ መልኩ ነብዩﷺ በሱጁዳቸው እና በሩኩዓቸው "ሱብሓነከሏሁመ ረበና ወቢሓምዲከ አሏሁመ ግፊርሊ( سبحانك اللهم ربنا وبحمدك اللهم اغفرلي)" ማለትን ያበዙ ነበር። ( እውነት – ሃሰት )

## የሱረቱ አል-መሰድ ማብራርያ ፈተና

126. ሱረቱ አል-መሰድ …   O መካይ ነች   O መደንይ ነች

127. አቡ ለሃብ …

O የነብዩ ﷺ አጎት ነው O ከነብዩ ﷺ ጋ ዝምድና የለውም

128. እስከ እለተ ትንሳኤ ድረስ ሲወቀስ ይኖራል…

O አቡ ለሃብ ብቻ O ከነብዩ ﷺ ጋ ጠላትነት የመሰረተ ሁሉ

129. የተከታዮቹን ቃላት ትርጉም ግለፅ:

"ተበት" ………………………………………………………… :تَبَّت

"ማከሰብ" ……………………………………………………… ما كسب

"ጂዲሃ"………………………………………………………… :جيدها

"መሰድ" ………………………………………………………… :مسد

130. ይህች ሱራ አቡ ለሃብንና ባልተቤቱ ከአሏህ ተአምራት መካከል ይዛለች፤ ሁለቱም አልሰለሙም!( እውነት –ሃሰት )

## የሱረቱ አል-ኢኽላስ ማብራርያ ፈተና

131. ሱረቱ አል-ኢኽላስ … O መኪይ ነች O መደንይ ነች

132. ሱረቱ አል-ኢኽላስ በዚህ ስያሜ የተጠራችበት ምክንያት …

O ጥርት ባለ መልኩ ስለአሏህ ብቻ ስለምትገልፅ O የሚቀራትን ከሽርክ ስለምታጠራው

Oሁለቱም

133. ይህች ሱራ ከምንዳ አንፃር ______ ትስተካከላለች

O የቁርአኑን ግማሽ O የቁርአኑን ሩብ O የቁርአኑን አንድ ሶስተኛ

134. ሱረቱ አል-ኢኽላስ ከሱረቱል ፋቲሓ በኋላ በ______ ሶላት በሁለተኛው ረከዓ መቅራቱ ይመከራል።

O ሱብሒ ሱና O በመግሪብ ሱና O በጡዋፍ ጊዜ በሚሰገድ ሱና

O በዊትር O ከግዴታ ሶላቶች በኋላ O በእንቅልፍ ሰአት O ሁሉም መልስ ነው

135. ሶስቱም የተውሒድ አይነቶች እስኪረጋገጡ ድረስ ሱረቱ አል-ካፊሩንና ሱረቱ አል-ኢኽላስን ቀንም ሌትም መቅራቱ ይመከራል። ( እውነት – ሃሰት )

136. ሱረቱ አል-ኢኽላስ በይበልጥ ይዘቷ…

O ተውሒድ አል-ኡሉሂያህ O ተውሒድ አል-ሩቡቢያ እና ተውሒድ አል-አስማእ ውሲፋት

137. "በል" ሲል ____ማለቱ ነው። O በቃል ብቻ O በቃል፣ በተግባርም በእምነትም

138. "በል «እርሱ አላህ አንድ ነው።" ሲል በጌትነት፣ በአምላክነት እና በስምና ባህርያት ያለውን ብቸኛ ነው ማለቱ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

139. "«አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው።" ሲል ____ ማለቱ ነው።

O ለሁሉም ነገር ተፈላጊው O ያ ለራሱ ሁኖ የሌላውም ሁሉ ብቸኛ መጠጊያ የሆነ

O በአለቃነቱ፣ በጌትነቱ፣ በአምላክነቱ፣ በስምና ባህርያቱ የተሟላ የሁሉ አሳዳሪ የሆነ Oሁሉም

140. ልጅ ወይም ወላጅ አለው ብሎ ወደ ኋያሉ አሏህ ማስጠጋት ትልቁ ክህደት ነው። ( እውነት – ሃሰት )

## የሱረቱ አልፈለቅ ማብራርያ ፈተና

141. ሱረቱ አልፈለቅ … O መክይ ነች O መደንይ ነች

142. ሱረቱ አልፈለቅን መቅራቱ ይመከራል በ…

O ከግዴታ ሶላቶች በኋላ O ልትተኛ ስትል O ሁሉም መልስ ነው

143. የተከታዮቹን ቃላት ግለፅ:

አዑዙ ............................................................................ :أعوذ
አልፈለቅ........................................................................... :الفلق
ጋሲቂን............................................................................ :غاسقٍ
ወቀብ............................................................................. :وقبَ
አን-ነፋሣት.......................................................................... :النَّفَّاثات
አልዑቀድ........................................................................... :العُقَد
ሓሲዲን............................................................................ :حاسدٍ

144. ይህች ሱራ በውስጧ … ይዛለች። O ጥቅል በሆነ መልኩም ይሁን በዝርዝር የአሏህ ጥበቃን መሻት O የሲሕርን እውነትነት O ሁሉም

## የሱረቱ አን-ናስ ማብራርያ ፈተና

145. ሱረቱ አን-ናስ ... O መኪይ ነች O መደንይ ነች

146. ሱረቱ አን-ናስ መቅራቱ ይመከራል...

O ከግዴታ ሶላቶች በኋላ O በእንቅልፍ ጊዜ O ሁሉም መልስ ነው

147. 'አል-ኸናስ' ማለት ምን ማለት ነው?

........................................................................................

# ሁለተኛው ትምህርት

**ሁለተኛው ትምህርት-የኢስላም ማእዘናት**

የአምስቱ ማዕዘናት ማብራርያ፡ የመጀመሪያውና ታላቁ ዓምድ - “ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው አምላክ የለም ፣ መሐመድም ﷺ የአላህ መልእክተኛ ነው”። የሚለው የምስክርነት ቃል ነው። ትርጉማቸውም ወደ ኋላ ከ“ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው አምላክ የለም” ቅድመ ሁኔታዎች ጋር ይብራራል ፡፡

ትርጉሙ-“ላ إِلَٰهَ” የሚለው ከአላህ ሌላ የሚመለኩትን ሁሉ የሚያወግዝ ነው። “إِلَّا الله” ማለት ደግሞ አምልኮን ለአላህ ብቻ የሚያፀድቅ ነው።

የ “ لا إله إلا الله” ቅድመ መስፈርቶች ደግሞ፡

1 -እውቀት፡ ድንቁርናን የሚጋፈጥ። 2 - እርግጠኛነት፡ ጥርጣሬን የሚጋፈጥ።

3- ኢኽላስ፡ ሽርክን የሚጋፈጥ 4- እውነተኝነት፡ ውሸትን የሚጋፈጥ

5- ጥላቻን በሚጋፈጥ ውዴታ 6- መንተት፡ መተውን የሚጋፈጥ

7 - መቀበል፡ ማፈግፈግን የሚጋፈጥ 8- ከአላህ ሌላ በሚመለኩ ነገሮች ሁሉ መካድ።

*ይህም በቀጣዮቹ ስንኞች ተጠቃልሎ እናገኘዋለን፡*

*እውቀት፣ እርግጠኝነት፣ እንዲሁም ኢኽላስህ*

*እውነተኝነት፣ ውዴታ፣ ለትእዛዙም መንተትህ*

*ተቀብሎ አፅድቆ በሌላው ተመላኪ መካድህ*

*ይህ ነው ተፈላጊው የእምነት መሰረትህ።*

*እንዲሁም በሙሐመድ መልዕክተኝነት መመስከር ግድ የሚያስብላቸው ግዴታዎች ደግሞ፡ የተናገሩትን እውነት ብሎ መቀበል፣ ባዘዙትም መታዘዝ፣ ካስጠነቀቁትና ከከለከሉትም መራቅ እና እሳቸው በደነገጉት እንጅ አሏህን አለማምለክ ናቸው። ከዚያም ለተማሪው ቀሪዎቹን የኢስላም ማዕዘናት ይብራራሉ። እነሱም፡ ሶላት፣ ዘካ፣ የረመዷንን ወር መፆም፣ መንገዱን ለቻለ በተከበረው የአሏህን ቤት ሓጅ ማድረግ ናቸው።*

## የሁለተኛው ትምህርት ማብራርያ

**የ "“لا إله إلا الله”" ማእዘናት**

**ማውገዝ: "በእውነት የሚመለክ የለም..."**

ከአሏህ ውጭ የሚመለከውን ሁሉ ያወግዛል

(በጣኦት መካድ)

**ማፅደቅ: "... ከአሏህ በቀር"**

አምልኮን ለአሏህ ብቻ ያፀድቃል

(በአሏህ ማመን)

**ይህች ከአሏህ ውጭ በእውነት ሊመለክ የሚገባው የለም የምትለው የኢኽላስ ቃል ሁለት ቅድመ መስፈርቶች አሏት፤ እነሱም ማፅደቅና ማውገዝ ናቸው።**

### የ “ላ ኢላሃ ኢላ አላህ” ቅድመ ሁኔታዎች ማብራርያ

የ “ላ ኢላህ ኢለሏህ” ሁኔታ እንደ ቁልፍ ጥርሶች ነው። “ላ ኢላሃ ኢለሏህ” ደግሞ በርግጥም የጀነት ቁልፍ ነች። ቁልፍም ጥርሶች ከሌለው በስተቀር አይከፈትም። በቁርአንና በሃዲስ ውስጥ የሚገኘውን “ላ ኢላሃ ኢላ አላህ” ለሚለው ማንኛውም እንዲህ እንዲህ አለው ተብሎ ምንዳ የተወሰበት ሁሉ እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎችን በተጨባጭ ማረጋገጡ ላይ የተመረኮዘ ነው። ቅድመ ሁኔታዎቹም ስምንት ናቸው፡

1- ትርጉሟን ማወቅ፡ ተቃራኒውም ትርጉሟን አለማወቅ ነው። ትርጉሟን የማያውቅን ሰው አትጠቅመውም። ስለሆነም እስልምናን ለመቀበል ለሚፈልግ ሰው ትርጉሙን ማወቅ ይጠበቅበታል። ነብዩﷺ “ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው አምላክ አለመኖሩን እያወቀ የሞተ ጀነት ገባ።” ብለዋል። (ሙስሊም ዘግበውታል)

2 - እርግጠኛነት - ማለትም መቶ በመቶ (ያለጥርጥር)። አንድ ሰው ከአላህ ሌላ ባሉ አማልክት መካድ እንዳለበት አንድ በመቶ እንኳ ቢጠራጠር ወይም ቢያምነታ እሱ/እሷ ሙስሊም አይደለም/ችም። አንድ ሰው ስለነዚያ የነብዩﷺ ጥሪ የደረሳቸው አይሁዶች እና ክርስቲያኖች ክህደት የሚጠራጠር ከሆነ ሙስሊም አይደለም። ነብዩﷺ እንዲህ ብለዋል-“እኔ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እና እኔም የአሏህ መልዕክተኛ መሆኔን እመሰክራለሁ። በእነዚህ ሁለት የምስክርነት ቃላት የማይወላዳ ሆኖ ጌታውን አሏህን የሚገናኝ አንድም ባርያ የለም ጀነት የገባ ቢህን እንጅ።” (ሙስሊም ዘግበውታል)

3- ኢኽላስ: መቶ በመቶ ለአሏህ ሊሆን፤ ምንም አይነት ይዩልኝ ወይም ይስሙልኝ ካለው ወይም ከአላህ ሌላ የሚያመልክን አይጠቅምውም ።

ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል-"በምልጃዬ በጣም እድለኛ የሆነው ሰው‹ ላ ኢላሃ ኢላ አላህ › ብሎ ከልቡ በኢኽላስ የሚመሰክር ሰው ነው ።" (ቡኻሪ)

4- እውነተኝነት-እንደ ሙናፊቆች አይነቱ ዋሸቶ የሚልን ሰው አትጠቅመውም። ነብዩﷺ እንዲህ ብለዋል-‹ላ ኢላሃ ኢለሏህ (ከአሏህ ውጭ በእውነት ሊመለክ የሚገባው የለም) መሐመድም የአሏህ ባርያ እና መልዕክተኛ ናቸው ብሎ ከልቡ የሚመሰክር የለም፤ አሏህ ከእሳት እርም የሚለው ቢሆን እንጅ።" (ቡኻሪ እና ሙስሊም)።

5- ውዴታ፡ አንድ ሰው አሏህን ሊወድ እና አንድንም እንደሱ ላይወድ ነው። በተጨማሪም አንድ ሰው አላህ እንዲወደድ ያዘዘውን ነገር ሁሉ መውደድ አለበት እና ተቃራኒውም ጥላቻ ነው። ለዚህም ነው ኢስላምን ከሚያፈርሱ ነገራቶች የሚመደበው። መልእክተኞች ይዘውት ከመጡት አንዳችንም ነገር መጥላት ቢሰራበትም እንኳ ከሃዲ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል-" ከሰዎችም ከአላህ ሌላ ባለንጣዎችን (ጣዖታትን) አላህን እንደሚወዱ የሚወዷቸው ኾነው የሚይዙ አልሉ። …" (አል-በቀራ 165)።

6- መነተት፡ ይህም ማለት በሷው መስራት ግዴታ ነው ማለት ነው። በሷው የማይሰራን ሰው አትጠቅመውም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል "በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም፤ (ምእመን አይኾኑም)።" (አን ኒሳእ 65)

7- መቀበል፡ አንድ ሰው በመልእክቱ፣ በተግባሩም ሆነ በእምነቱ መቀበል አለበት። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል "እነርሱ ከአላህ ሌላ አምላክ የለም በተባሉ ጊዜ ይኮሩ ነበሩ። እኛ ለዕብድ ባለቅኔ ብለን አማልክቶቻችንን የምንተው ነን? ይሉም ነበር። "(35-36)

8- መካድ: ማለትም ከአሏህ ውጭ የተመለከ ሁሉ አምልኮው ውድቅ ነው። ከአሏህ ውጭ ሊመለክ የሚገባው የለምና።

**ማሳሰቢያ፡**

የኢኽላስ የምስክርነት ቃል ማመኑ፣ መናገሩ እና በተግባር ማዋሉ የግድ ነው።

## የሁለተኛው ትምህርት ማብራርያ

### የመውደድ(ፍቅር) አይነቶቹ

**ተፈጥሯዊ ፍቅር**

አሏህን ከመውደድ በፊት እስካልተቀደመ ድረስ የሚፈቀድ ነው። ለምሳሌ: ልጅን እና ባለቤትን መውደድን ይመስል። የአሏህ መልዕክተኛﷺ እንዲህ ብለዋል፡ ''**እኔ እሱ ዘንድ ከልጅ፣ ከወላጁም ሆነ ከመላው የሰው ልጅ በላይ እሱ ዘንድ የተወደድኩ እስካልሆንኩ ድረስ አላመነም። ''**

**ለአሏህ ብሎ መውደድ**

ይህ ግዴታ ብሎም ታማኝ የኢማን ዘለበት ነው። አሏህ ﷻ እንዲህ ብሏል: "*የአላህ መልክተኛ ሙሐመድ እነዚያም ከእርሱ ጋር ያሉት (ወዳጆቹ) በከሓዲዎቹ ላይ ብርቱዎች በመካከላቸው አዛኞች ናቸው።* ..." (48:29).

ከስር ባሉት አራት ነገራቶች ይገለፃል:

**ከአሏህ ጋ (እኩል) ማፍቀር**

ይህ ከትልቁ ሽርክ ነው። ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ ይላል **"ከሰዎችም ከአላህ ሌላ ባለንጣዎችን (ጣዖታትን) አላህን እንደሚወዱ የሚወዷቸው ኾነው የሚይዙ አልሉ።"** (አል በቀራ :165).

<u>**አሏህ ዘንድ የተወደዱ ድርጊቶች ያም እንደ ተውሒድ ያለውን ሸሪዓ ይዞት የመጣውን ሁሉ ማለት ነው።**</u>

<u>**በሱ ሰሪዎች፡ እንደ ነቢያት ፣ ሩሱሎች፣ መላእክቶች ፣ ሱሓቦችና እና እያንዳንዱ የተውሒድ ሰው።**</u>

<u>**ለአላህ የተወደዱ ጊዜያት፡ እንደ ለይለቱል ቀድር እና የእያንዳንዱ ምሽት አንድ ሶስተኛ ክፍል ያሉትን ይመስል።**</u>

<u>**እንደ መካ እና መዲና ያሉ አላህ ዘንድ የተወደዱ በታዎች።**</u>

## የሁለተኛው ትምህርት ማብራርያ

**ሙሐመዱን ረሱሉሏህ በሚለው የምስክርነት ቃል "ዓብዱህ(ባርያው ናቸው)" ስንል ምን ማለታችን ነው?**

እርሱ ከፍጥረቱ ሁሉ እጅጉን በላጩ የአሏህ ባርያ ነው። ለአላህ የሚገባውን አምልኮ በፍጹም ያረጋገጠ ብቸኛ ነው።

እሱ በ ‹ጌትነት› ፣ በአምልኮም ሆነ በአላህ ስሞች እና ባህሪዎች ውስጥ ምንም ድርሻ ስለሌለው ﷺ ሊመለክ የሚገባው አይደለም ማለት ነው።

**ለአሏህ ተገቢ የሆነው ተገዥነት (ማጎብደድ) አይነቶቹ፡**

**የልዩ ልዩ የሆነው**

ይህ ደግሞ የመልዕክተኞች _ዓለይሂሙ ሰላት ወሰላም_ ለአሏህ ያላቸው ታዛዥነትን የሚጠቁም ነው። **"... እርሱ በብዙ አመስጋኝ ባሪያ ነበርና።"** (አል ኢስራእ 3) ይህች ወደ ባርያዎች የተጠጋችዋ የተገዥነት አይነት የልዩ ልዩ ነች። ምክንያቱም የነኝህን መልዕክተኞች ተገዥነት ጋ የሚፎካከር አንድም አካል የለምና።

**ልዩ የሆነው**

ይህ አጠቃላይ የታዛዥነት ማጎብደድ ነው: ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ ይላል " **የአልረሕማንም ባሮች እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚኼዱት... ናቸው"**(አል ፉርቃን 63). ይህ በድንጋጌዎቹ አሏህን የተገዛን ሁሉ ያጠቃልላል።

**ጥቅል የሆነው**

ይህ የአጠቃላይ ፍጥረት ለአሏህ ﷻ ጌትነት (አሸናፊነት) ያላቸው ማጎብደድ ነው። ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ ይላል፡ (**በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ (በትንሣኤ ቀን) ለአልራሕማን ባሪያ ኾነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም**) (መርየም 93). በዚህም አጠቃላይ ሙእሚኑም ከሃዲውም ይካተታል።

## የነብዩ ﷺ አጭር ታሪካዊ ዳሰሳ

**ዘራቸው**

እሳቸው-መሐመድ ኢብኑ ዓብዱላህ ኢብኑ ዓብዱል-ሙጦሊብ ኢብን ሀሺም ፣ ሃሺም ከቁርይሽ ሲሆን ፣ ቁረይሽም ደግሞ ከዓረቦች የመጣ እንዲሁም አረቦችም ደግሞ ከኢስማዒል ኢብኑ ኢብራሂም አል-ኸሊል (የአሏህ ተወዳጅ) ናቸው። ዓለይሂሙ ሰላት ወሰላም

## የሁለተኛው ትምህርት ማብራርያ

| | |
|---|---|
| እሳቸው የተወለዱት በመካ፤ በወርሃ ረቢዐል አወል ነው። በህይወት የኖሩት ለ63 አመት ሲሆን ከዚህም 40ውን ከነብይነት በፊት 23 አመቱ ደግሞ ነብይ እና ረሱል ሆነው ነው። እሳቸው ወላጅ አልባ ሆነው ነበር ያደጉት። ወላጅ አባታቸው ከመወለዳቸው በፊት የሞቱ ሲሆን በአያታቸው ዓብዱል ሙጦሊብ ሃላፊነት ስር ሆኑ። ከአያታቸው ሞት በኋላ ደግሞ አጎታቸው አቡ ጧሊብ ነው ያሳደጋቸው። | ውልደት |
| እሳቸው ﷺ ወደ ሁለቱም ከባባዶች የሰው ልጅና አጋንንት ነው የተላኩት። የሳቸው ተልዕኮ መልእክት ደርሶት በሳቸው ያላመነ ግን ማንም ይሁን ማን ከእስልምና የሚያወጣውን አይነት ትልቁ ክህደት ላይ ያረፈ ካፊር ነው። | መላካቸው |
| የአሏህ መልዕክተኛ ﷺ ወደ ተውሒድ፣ ወደ መልካም ባህሪ እና ወደ መልካም ስነምግባር ነው ጥሪ ያደረጉት። ከአላህ ሌላን ከማምለክ፣ ከመጥፎ ሥነምግባር እና ከመጥፎ ተግባራት አስጠንቅቀዋል። | ጥሪያቸው |
| እሳቸው ﷺ ከመካ ወደ በይተል መቅዲስ አርገዋል። ከዚያም ወደ ሰባተኛው ሰማይ አርገው አሏህም አናግሯቸው እዛው ባሉበትም አምስቱ የሶላት ወቅቶች ተደንግጎባቸዋል። | የኢስራእ እና ሚዕራጅ ጉዞ |
| እሳቸው ﷺ ከመካ ወደ መዲና ተሰደው እዚያው ሞተው በምእመናን እናት ዓኢሻ(ረዲየሏሁ ዓንሃ) ቤት ውስጥ ተቀበሩ። | ሂጅራ እና ሞት |
| አላህ ዲኑን በሳቸው አሟልቷል። ተልዕኳቸውን ግልጽ በሆነ መልእክት አስተላልፈዋል። አደራቸውን ተወጥተዋል። ህዝባቸውን መክረዋል፤ በየትኛውም የትግል አይነት በአሏህ መንገድ እውነተኛውን ትግል ታግለዋል። በመሆኑም ማንም ቢሆን በዚህ ሃይማኖት ውስጥ ማንኛውንም አይነት አዲስ ነገር ሊያክል አይመቸውም። | ተልዕኳቸው |

## የሁለተኛው ትምህርት ማብራርያ

| | |
|---|---|
| ሰባት ናቸው: በድር፣ ኡሑድ፣ አልኸንደቅ፣ ኸይበር፣ የመካ መከፈት፣ ተቡክና ሑነይን ናቸው። | **አሳሳቢ የሚባሉት ዘመቻዎቻቸው** |
| አል ቃሲም ፣ ኢብራሂም ፣ አብዱሏህ እሱም ነው ጦይቡ ጧሂር የሚባለው፣ ዘይነብ ፣ ሩቅያ፣ ኡም ኩልሡም፣ ፋጢማ ይባላሉ። ከፋጢማህ ውጭ ሌሎቹ ሁሉም እሳቸው በህይወት እያሉ የሞቱ ናቸው። ፋጢማም የሞተችው ከሳቸው ሞት ከስድስት ወር በኋላ ነው። አሏህ ሁሉንም መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና | ልጆቻቸው ሰባት ናቸው |
| ኸዲጃ ፣ ዓኢሻህ ፣ ሰውዳህ ፣ ሓፍሷ ፣ ዘይነብ አል ሂላሊያህ ፣ ኡሙ ሰላም ሂንድ ፣ ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ ፣ ጁወይሪያ ቢንት አል ሓሪሥ ፣ ሰፊያ ቢንት ሑየይ ፣ ኡሙ ሓቢባ ረምላ ፣ ረይሓናህ ቢንት ዘይድ እና መይሙናህ ቢንት አል ሓሪሥ። አሏህ ሁሉንም ስራቸውን ይውደድላቸውና። | 12ቱም ባልተቤቶቻቸው |
| እናታቸው አሚናህ ቢንት ወህብ፣ ሡወይባህ የአጎታቸው አቢ ለሃብ ነፃ የወጣች አገልጋይ፣ ሓሊማህ ቢንት አቢ ዙአይብ አስ-ሰዕድያህ (ረዲያሏሁ ዓንሃ)። | እሳቸውን ﷺ ያጠቡ |
| በሱረቱል ዓለቅ ላይ ያሉት ተከታዮቹ አንቀፆች: "**አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም።** 1. **ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)።** 2. **አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፤** 3. **ያ በብርዕ ያስተማረ።** 4. **ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲኾን።** 5." | መጀመርያ ወደ እሳቸው ﷺ የወረዱት የቁርአን አንቀፆች |
| ከወንዶች አቡበከር አስ-ሲዲቅ ሲሆኑ ከሴቶቹ ደግሞ የአማኞች እናት ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ እንዲሁም ከልጆች ዓልይ ኢብኑ አቢ ጧሊብ። ከአገልጋዮች ዘይድ ኢብኑ ሓሪሣህ እና ከባሪያዎ ደግሞ ቢላል ኢብን አቢ ረባሕ ናቸው። አሏህ ሁሉንም መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና። | መጀመርያ በሳቸው ﷺ ያመኑ |

## የሶስተኛው ትምህርት ማብራርያ

**የሳቸው ﷺ ሓጅና ዑምራቸው**

እሳቸው ﷺ 4 ጊዜ ሁሉንም በተለያየ አመት በወርሃ ዙል-ቀዒዳህ ሓጅ አድርገዋል። በአስረኛው አመተ ሂጅራ አንድ ጊዜ ያም የመሰናበቻውን ሓጅ ሓጅ አደረጉ።

**ስብእናቸው ﷺ**

ከፍ ያለው አሏህ ለመልዕክተኛው ﷺ እንዲህ ይላቸዋል: "አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ።"(አል ቀለም 4) አሏህ ስራዋን ይውደድላትና የምእመናን እናት ዓኢሻም እንዲህ ብላለች: "ስነምግባራቸው ቁርአን ነበር።"

**ታሪካቸውን የመማር አስፈላጊነቱ**

ኢብኑ አል ቀይም –አላህ ይዘንለትና እንዲህ ብሏል- በሁለቱም አገር ውስጥ የአንድ ሰው ደስታና ስኬት ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መመሪያ ጋር የተገናኘ ከሆነ እራሳቸውን ለሚመከሩ እና ስኬታማ ለመሆን እንዲሁም ደስተኛ ለመሆን ለሚወድ ሁሉ ከማያውቁት በማይሆንበትና በሚለይበት እንዲሁም በተከታዮቻቸው፣ በጭፍሮቻቸው እና በጓዶቻቸው ጎራ በሚሰለፍበት መልኩ ስለ መመርያቸው፣ ስለታሪካቸውና ስለጉዳያቸው ማወቁ የግዱ ነው። ሰዎችም በዚህ ረገድ ይለያያሉ፡ ትንሽ የሚያውቅ አለ፤ ብዙ የሚያውቅም አለ፤ የተነፈገም አለ፤ መበላለጡ አሏህ ለፈለገው የሚሰጠው የአሏህ ችሮታ ነው። አላህም የታላላቅ ችሮታዎች ባለቤት ነው።

# ሶስተኛው ትምህርት

## የኢማን ማእዘናት

የኢማን ማእዘናት ስድስት ናቸው: እነሱም- በአላህ ማመን፣ በመላእክቱ፣ በመፃህፍቱ፣ በመልዕክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀን ማመን እና በበጎውም ሆነ በክፉ ቀደር ከአሏህ መሆኑን ማመን ናቸው።

### ኢማን እንደ ሸሪዓህ ያለው ፍች

ኢማን በአንደበት የሚባል፣ በልቦና እምነት ተደርጎ የሚያዝ እና በአካልም በልቦናም የሚተገበር ነው። አሏህን በመታዘዝ የሚጨምር በማመፅም የሚቀንስ ነው። ማስረጃውም: -

- **በአንደበት የሚገለፅ ለመሆኑ:** የአሏህ ﷺመልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል: **"(የኢማን) ከፍተኛ ደረጃዋ ላ ኢላሃ የሚለው ቃል ነው።"**
- **በአካል የሚተገበር ለመሆኑ:** የአሏህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል **"(የኢማን) ዝቅተኛ ደረጃዋ አስቸጋሪን ነገር ከምንገድ ማስወገድ ነው።"**
- **በልቦናዊ ተግባር የሚገለፅ ለመሆኑ:** የአሏህ ﷺመልእክተኛ እንዲህ ብለዋል **"ሓያእም ከኢማን ነው"** (ሙስሊም)
- **ኢማን እንደሚጨምር ማስረጃው:** ተከታዩ የአሏህ ቃል ነው: **"ማንኛችሁ ነው= ይህች (ምዕራፍ) እምነትን የጨመረችለት?"**(አትተውባ 124)
- **እንደሚቀንስ ማስረጃው :** የአሏህ መልዕክተኛﷺ ቃል ነው **"ከአእምሮም ሆነ ከዲን ቅናሽ ... አላየሁም"** (ቡኻሪይና ሙስሊም)

## የሶስተኛው ትምህርት ማብራርያ

### ኢማን የሚጨምርባቸው ምክንያቶች

- ተውሒድን በተለይም የስምና ባህርያቱን አሃዳዊነት ማጥናት
- ለአሏህ ታዛዥነትን ማብዛት
- ከወንጀል መታቀብ
- ስለፍጥረታቱ ማስተንተን

### ኢማን የሚቀንስባቸው ምክንያቶች

- ተውሒድን በተለይም የስምና ባህርያቱን አሃዳዊነት ማጥናትን መተው
- አሏህን መታዘዝ መተው
- ወንጀልን መዳፈር
- ስለፍጥረታቱ ማስተንተንን መተው

### ስድስቱ የኢማን ማእዘናት

- በአሏህ ማመን
- በመላእክቶች ማመን
- ባወረዳቸው መፃህፍቶች ማመን
- በመልዕክተኞች ማመን
- በእለተ ፍፃሜ ማመን
- በቀደር በበጎውም በክፉውም ማመን

## የሶስተኛው ትምህርት ማብራርያ

### የመጀመርያው ማእዘን: በአሏህ ማመን

በስምና ባህርያቱ ማመን

በአሏህ ጌትነት ማመን

በአሏህ አምላክነት ማመን

በአሏህ ህልውና ማመን: ይህም በአራት መልኩ የሚሆን ነው:

**በተደነገገው**

ኢብን ቀይም አሏህ ይዘንላቸውና በቁርአን ውስጥ የትኛዋም አንቀፅ የለችም ወደ አሏህ ብቸኝነት የምትጠቁም ብትሆን እንጅ።

**በተፈጥሯዊ ማንነት**

የአሏህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል: **"ተወላጅ ሁሉ በተፈጥሯዊ ማንነቱ ላይ ሆኖ ይወለዳል ወላጆቹ አይሁድ ወይም ክርስትያን ወይም ደሞ መጁስይ ያደርጉታል እንጅ።"**(ቡኻርይ እና ሙስሊም)

**በተጨባጩ**

በችግርና መከራ ሆነህ እጆችህን ወደ ሰማይ ከፍ አድርገህ: "ያ ረብ!" ስትል ይህ ችግርና መከራ በአሏህ ፍቃድ ተወግዶ ታገኘዋለህ።

**እንደ አእምሮ**

እንደ አእምሯዊ አስተሳሰብ ምንም አይነት ግኝት ያለ አስገኝ ፍጥረትም ያለ ፈጣሪ ሊገኝ መቻሉን ሊቀበለው የሚችል አይደለም። **"ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን?"** (አጥ-ጡር 35)

### ሁለተኛው ማእዘን: በመላእክቶች ማመን

መላእክቶች: በማይዳሰሰው አለም ያለ ራሱን የቻለ አለም ነው። አሏህ ከብርሃን የፈጠራቸው፤ የማያምፁት ታዛዦች፤ መናፍስትም **"ቅዱሱ መንፈስ"** (አል በቀራ 87) አካልም **"መላእክትን ባለ ሁለት ሁለት፤...ክንፍ አድራጊ ለሆነው..."** (ፋጢር 1) አእምሮና ልቦናም **"ከልቦቻቸው ላይ ድንጋጤው በተገለጸም ጊዜ (ተማላጆቹ) «ጌታችሁ ምን አለ?» ይላሉ። ..."** (ሰባእ 23) እንዳላቸው እናምናለን። በነሱ ህልውናም ሆነ አሏህ ስለነሱ(እንደ ጅብሪል፣ ሚካኤልና ኢስራፊል ባለው) ከስያሜዎቻቸው ባሳወቀንም ስለ ባህሪዎቻቸውም **"አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጹም፡፡ የሚታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ።"** (ተሕሪም 6) ያለንን ስለስራዎቻቸውም ባሳወቀን እናምናለን።

### ስለመላኢኮች (ሃላፊነት) በግል ከተነገረን መካከል

ከነዚህም መካከል ስምንቱ የዓርሽ ተሸካሚዎች፣ ወሕይ የማድረስ ሃላፊነት ያለው ጅብሪል፣ በዝናብ በኩል ሃላፊነቱ ያለበት ሚካኤል፣ በአጠቃላይ በነሱ እና ስለነሱ በጥቅሉም ይሁን በዝርዝር በመጣው እናምናለን።

## ሶስተኛው ማእዘን፡ በመፃህፍቱ ማመን

ዘይቤያዊ ሳይሆን በትክክል የአሏህ ቃል መሆናቸውን፤ ከሱ የተወረዱ እንጅ የተፈጠሩ አለመሆናቸውን፤ አሏህ ከእያንዳንዱ ረሱል ጋ መፅሃፍ እንዳወረደ፤ በነሱ፣ ስለነሱ ስያሜ፣ መረጃ እና እስካተኻረ ድረስ ፍርድ ጥቅልም ይሁን በዝርዝር በመጣው እናምናለን። ቁርአንም ደሞ ከሱ በፊት የመጡትን (ተውራት/ኦሪት፣ ኢንጂል/ወንጌል፣ ዘቡር/መዝሙር፣ የኢብራሂምና የሙሳ ሱሑፎች) መፃህፍቶችን ሁሉ እንደሻረ እናምናለን።

## አራተኛው ማእዘን፡ በመልዕክተኞች ማመን

ከአምላክነት መለያ ማንነት ምንም ድርሻ የሌላቸው የሰው ልጆች መሆናቸውን፤ የሚያመልኩ እንጅ የማይመለኩ መሆናቸውን፤ አሏህ እንደላካቸው እና ወሕይም እንዳወረደላቸው፤ በተአምራትም እንዳጠናከራቸው፤ እነርሱም አደራቸውን እንደተወጡ፣ ኡማውንም እንደመከሩ እንዲሁም በአሏህም መንገድ ትክክለኛውን ትግል እንደታገሉ ማመናችን ግዴታ ነው።

በነሱ፤ አሏህ ስለነሱ በጥቅሉም በዝርዝርም ስለስማቸው፣ ስለባህርያቸውና ስለነሱ በነገረን ሁሉ እናምናለን። የነብያቶች መጀመርያ አደም፣ የረሱሎች መጀመርያም ኑሕ፣ የነብያቶችም የረሱሎችም መደምደምያ ደግሞ ሙሓመድ መሆናቸውን፤ ከሱ በፊት የነበሩ ድንጋጌዎች ሁሉ በሙሓመድ ሸሪዓ እንደተሻሩ፤ ከነሱም የቆራጥነት ባለቤት የተባሉትም በሁለት ሱራዎች (ሹራ እና አሕዛብ) የተጠቀሱት አምስቱ መሆናቸውን እናምናለን። ሶለዋቱሏሂ ወሰላሙሁ ዓለይሂም።

## አምስተኛው ማእዘን፡ በመጨረሻው ቀን ማመን

ነብዩﷺ ከሞት በኋላ ስለሚሆነው በነገሩን ሁሉ ማመንን የሚያጠቃልል ነው። የቀብር ፈተናን፤ በጥሩምባ መነፋቱ፤ የሰዎች ከቀብራቸው መነሳት፤ ሚዛን፤ የስራ መዝገብ፤ ሲራጥ፤ ሓውድ፤ ሸፋዓህ፤ ጀነት፤ ጀሃነም፤ የምእመናን ጌታቸውን በእለተ ትንሳኤ እና በጀነትማየታቸው፤ እና በሌሎችም በስሜት ህዋሳት ስለማይደረስባቸው የነገሩንን ሁሉ ይመስል።

## የሶስተኛው ትምህርት ማብራርያ

**ስድስተኛው የኢማን ማእዘን: በመጥፎውም በደጉም ቀደር ማመን**

ማወቅም መፃፉ መፍለግና መፍጠሩ እሱው ነው ክንውኑ ሂደት የፍጡሩ

**በሚለው ስንኝ አራቱም እርከኖች ይገኛሉ።**

**ማወቁ:**

ጥራት ይገባውና አላህ ሁሉንም ነገር በጥቅሉም በዝርዝርም እንደሚያውቅ ማመን: "... **(ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል።...**" (አልበቀራ 255).

**መፃፉ:**

አላህ ሁሉም ነገር እስከዕለተ ፍፃሜ ድረስ ያለውን ክንውን ሁሉ እንደፃፈው ማመን: ማስረጃውም ተከታዩ የአሏህ ቃል ነው: "**በሰማይና በምድር ውስጥ ምንም የተደበቀ ነገር የለም ገላጭ በኾነው መጽሐፍ ውስጥ ያለ ቢኾን እንጅ።**" (ነምል 75).

**መሻት:**

አላህ የሻው እንደሚሆን አላህ ያልሻው ደሞ እንደማይሆንና ባርያም የራሱ ነፃ ፍላጎት እንዳለው ነገር ግን ከአላህ መሻት ስር መሆኑን ማመን: "**አሏህ የሻውን እንጅ የምትሹ አይደላችሁም**" (አትተክዊር :29)

**መፍጠር:**

የሰው ልጆችም ሌላውም ከድርጊቶቹ ጋ አላህ የፈጠረው መሆኑ፤ ማስረጃውም

"**«አላህ እናንተንም የምትሠሩትንም የፈጠረ ሲኾን።»** **(አስ-ሷፋት 96)**"

# አራተኛው ትምህርት

## የተውሒድ አይነቶች እና የሽርክ አይነቶች

ተውሒድ ሶስት ክፍሎች አሉት: **የጌትነት አሃዳዊነቱ፣ አምላካዊ አሃዳዊነቱ እና በስምና ባህርያቱ ያለው አሃዳዊነቱ**

**የጌትነት አሃዳዊነቱ**: ጥራት ይገባውና አሏህ ሁሉንም ነገር የፈጠረ መሆኑን፣ የሁሉም ነገር አስተናባሪ መሆኑን እንዲሁም በዚህም ተጋሪ የሌለው መሆኑን ማመን ነው።

**የአምልኮ አሃዳዊነቱ**: ጥራት ይገባውና በእውነት ተመላኪው እርሱ መሆኑን፤ በዚህም ተጋሪ እንደሌለው ማመን ነው። ይህም ነው ደግሞ የ *"ላ ኢላሃ ኢላ ሏህ"* ትርጉም። ምክንያቱም ትርጉሟም ከአሏህ ውጭ በእውነት የሚመለክ የለም ነውና። በመሆኑም የአምልኮ አይነቶች ባጠቃላይ ከሶላት፣ ከፆም እና ሌሎችም ለአሏህ ብቻ ማጥራቱ ግዴታ ነው። አንዳቸንም ነገር ከሱ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ መስጠቱ የሚፈቀድ አይደለም።

**በስምና ባህርያቱ ያለው አሃዳዊነት**: ይህ ደግሞ በተከበረው ቁርአን፣ ሶሒሕ በሆኑ ሓዲሦች ስለአሏህ ስምና ባህርያት በወረደው ሁሉ ለአሏህ ብቻ ያለምንም ተጋሪ ጥራት ይገባውና ለሱ ልቅና በሚገባው መልኩ ማፅደቅና ማመን ነው። ይህም ያለማዛባት፣ ውድቅም ባለማድረግ፣ ዝርዝር ሁኔታም ውስጥ ባለመግባት እና ባለማመሳሰል ነው። በተከታዩ የአሏህ ቃል በመስራት መልኩ: **"በል «እርሱ አላህ አንድ ነው።(1) «አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። (2) «አልወለደም፤ አልተወለደምም (3) «ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።።»(4)** (አል ኢኽላስ 1-4) እንዲሁም ተከታዩ የአሏህ ቃል **"የሚመስለው ምንም ነገር የለም። እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው።"** (ሹራ 11)

አንዳንድ ዑለሞች ተውሒድን ወደ ሁለት ከፍለውታል፤ ይህም አሏህ በስምና ባህርያቱ ያለውን አሃዳዊነት በጌትነቱ ባለው አሃዳዊነት ስር በመክተት ሲሆን በዚህም ላይ መተቻቸት የለለበት ነው። ምክንያቱም ሁለቱም የፈለጉበት ነገር ግልፅ ነውና።

የሽርክ አይነቶችም ሶስት ናቸው: **ትልቁ ሽርክ፣ ትንሹ ሽርክ እና ድብቁ ሽርክ ናቸው።**

**ትልቁ ሽርክ**: የስራን መበላሸት እና በዛው ላይ ሆኖ ለሞተም ደግሞ እሳት ውስጥ መዘውተርን ግድ ያደርጋል። ልክ ከፍ ያለው አሏህ እንዳለው፡ **"ባጋሩም ኖሮ ይሠሩት የነበሩት ከነሱ በታበሰ ነበር።"** (አልአንዓም 88) እንዲሀም ብሏል: "**ለከሓዲዎች በነፍሶቻቸው ላይ በክህደት የሚመሰክሩ ሲኾኑ የአላህን መስጊዶች ሊሠሩ አይገባቸውም፡፡ እነዚያ ሥራዎቻቸው ተበላሹ፡፡ እነሱም በእሳት ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው።"** (አት-ተውበ17) በዛው ላይ ሆኖ ያለ ተውበ የሞተም አሏህ መሃርታ አያደርግለትም ጀነትም በርሱ ላይ እርም ነች። ልክ አሏህ እንዳለው፡ **"አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም፡፡ ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል፡፡"** (አን-ኒሳእ 48) ጥራት ይገባውና እንዲህም ብሏል: **"እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ፡፡ መኖሪያውም እሳት ናት፡፡ ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም።"** (አል ማኢዳህ 72)

ከአይነቶቹም: ሙታንንና ጣኦታትን መማፀን፣ በጭንቅ ጊዜም እነሱን ድረሱልኝ ማለት፣ ስለትን ወደነሱ ማቅረብ፣ እርድንም ለነሱ ማቅረብ እና ሌሎችም።

**ትንሹ ሽርክ**: ይህ ደግሞ በቁርአንና በሓዲሥ ጥቅስ ሽርክ በሚል ስያሜ የተጠራ ሆኖ ነገር ግን ከትልቁ ሽርክ ያልሆነ ነው። እንደ በአንዳንድ ድርጊቶች ላይ ይዩልኝ ይስሙልኝ ማለት፣ ከአሏህ ውጭ ባለ አካል እንደመማል፣ "የአሏህ እና የአንተ ፍላጎት ከታከለበት(እኩል በሚያደርግ ገለፃ)" ማለት እና ሌሎችም። ምክንያቱም ነብዩﷺ እንዲህ ስላሉ ነው " 'ከምፈራላችሁ ሁሉ እጅጉን የምፈራላችሁ ትንሹ ሽርክ ነው'፤ ስለዛም (ምንነት) ተጠየቁ፤ 'ሪያእ(እዩልኝ ስሙልኝ) ነው' አሉ። "

እንዲሁም የነብዩﷺ "ከአሏህ ውጪ ባለ የትኛውም አካል የማለ በርግጥም አጋርቷል" የሚለው ቃላቸው።

እንዲሁም የሳቸውﷺ "የአሏህ እና የእከሌ ፍላጎት ከሆነ አትበሉ፤ ነገርግን የአሏህ ፍላጎት ከሆነ ከዚያ የእከሌ በሉ" የሚለው ቃላቸው። አቡ ዳውድ ሶሒሕ በሆነ ዘገባ ከሑዘይፋ ኢብኑል የማን ዘግበውታል።

ይህ አይነቱ ከእስልምና ያስወጣል ወይም ደሞ በእሳት ውስጥ ዘውታሪ ያደርጋል ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ግዴታ የሆነውን የተውሒድ ምሉእነት ያናጋል።

ሶስተኛው አይነት ደግሞ: ድብቁ ሽርክ ነው። ይህም ነብዩ ﷺ ተከታዩን ያሉበት ነው: " **‘እኔ ዘንድ ከመሲሑ ደጃል በላይ እጅጉን የምፈራላችሁን አልነግራችሁምን?’** አሏቸው እነርሱም: ‘እንዴታ የአሏህ መልዕክተኛ ሆይ!’ አሉ እሳቸውም: **"ድብቁ ሽርክ፡ አንድ ሰው ለሶላት ይቆማል፤ ሶላቱንም ያሳምራል ግን እሱን የሚመለከተው ሰው ስላየ ነው።"**

ሽርክ ወደ ሁለት ብቻም ሊከፈል ይችላል፡ ትልቁ እና ትንሹ ተብሎ። ድብቁ ሽርክ ደግሞ ሁለቱንም ሊያጠቃልል የምችል ነውና።

ከትልቁ ሽርክ ሊይርፍ ይችላል፤ እንደሙናፊቆቹ ሽርክ፤ ምክንያቱም እነሱ ውዳቂ የሆነ እምነታቸውን ይደብቃሉና። ከዚያም ለሰው ሲታዩ ኢስላምን ያሳያሉ፤ ይዩልኝ ይስሙልኝ በሚል ስሜት ወይም ደሞ በራሳቸው ላይ ስለሚሰጉ።

በትንሹ ሽርክም ላይ ሊያርፍ ይችላል፤ እንደ ይዩልኝ ይስሙልኝ ያለው፤ ልክ ባሳለፍነው የማሕሙድ ኢብኑ ለቢድ አልአንሷርይ ሓዲሥ ላይ፤ እንዲሁም የአቢ ሰዒድ ሓዲሥም ላይ እንደተወሰው። አሏህ የተውፊቁ ባለቤት ይግጠመንና።

## የአራተኛው ትምህርት ማብራርያ

### የከልከላቶች አይነት፡

**ትልቁ ሽርክ፡**
ይህ ከፍተኛው ነው፡፡

**ትንሹ ሽርክ፡**
ከትልቁ ሽርክ ያነሰ ከከባባድ ወንጀሎች ግን የከፉ ነው፡፡

**ከባባድ ወንጀሎች፡**
መርገም፣ ከራሕመት መባረር፣ ወይም ከሰረው መጥራራትን የመሰለ መቀጣጫ የመጣበት ወይም ደግሞ “ከካፊሮች ነው” ወይም “ከሙሽሪኮች ነው” “ከሙእሚኖች አይደለም” የተባለበት ወይም ደሞ በአስቀያሚ እንስሳት የተመሳሰለበት ነው፡፡

**ትናንሽ ወንጀሎች፡**
ይህ ደንጋጊው (አሏህና መልዕክተኛው) ከልከሎት ልዩ የሆነ መቀጣጫ ያላስከተለበት ነው፡፡

### ከባባድ ወንጀሎች፡

**ፍርዱ**
ነብዩ ﷺ እንዲህ ስላሉ ተውባ ማድረጉ ግድ ነው፡ "ሙሽ አውራጅ ሴት ከሞሞቷ በፊት ተውባ አድርጋ ካልተመለሰች..." (ሙስሊም)

**ደረጃዎቹ**
ነብዩ እርስ በራሱ ይበላለጣል ነብዩ ﷺ እንዲህ ስላሉ፡ "ከከባዶቹ ከባዱን አልነገራችሁምን? ..." (ቡኻሪይ እና ሙስሊም ዘግበውታል)

**የድርጊቱ ፈፃሚ ፍርዱ**
-እምነቱ የቀነሰ ሙእሚን ነው፡፡ ወይም ደሞ በእምነቱ አማኝ በፈፀመው ከባድ ወንጀል አመፀኛ ነው፡፡
-እሱ ዘንድ ባለው መልካም ስራ ልክ ይወደዳል እሱ ዘንድ ባለው ከባድ ወንጀል ልክ ይጠላል፡፡
-ወንጀሉን በሚዳፈርበት ሁኔታ ላይ አብረውት አይቀማመጡም፡፡

**ብዛቷ?**
በቁጥር የተገደበ ባይሆንም ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መርህ የተገደበ ነው፡፡

## በትንሹ እና በትልቁ ሽርክ መካከል ያለው ልዩነት

### ትልቁ ሽርክ

1. ከኢስላም መንገድ ያስወጣል
2. ስራን ሁሉ ያበላሻል
3. ተውባ ሳያደርግ ለሞተ ለዘላለሙ እሳት ውስጥ ዘውታሪ ያደርገዋል
4. ለሚመለከተው ሙስሊም ባለስልጣን ደሙንና ገንዘቡን የተፈቀደ ያደርግበታል
5. በማስረጃ ከባዱ መሆኑ የተጠቆመበት
6. ሰበብ ለሆነ ነገር በፍጥረተ አለሙ ላይ ድብቅ የሆነ ማስተናበር አለው ተብሎ ከታመነ
7. በዛው ላይ ሆኖ ከሞተ መሃርታ አይደረግለትም
8. ተውባ ካደረገ አሏህ ተውባውን ይቀበለዋል፤ በሁለት አጋጣሚዎች ላይ ካልሆነ በቀር፤ የፀሃይ በስተምዕራብ በኩል መውጣትና ጣእረ ሞት / ሞት አፋፍ ላይ ሲሆን።

### ትንሹ ሽርክ

1. ከኢስላም መንገድ አያስወጣም
2. ስራን ሁሉ ባያበላሽም የተቀላቀለበትን ስራ ብቻ ለይቶ የሚያበላሽ ነው።
3. ዘላለሙን ጀሃነም ውስጥ ለመዘውተር ምክንያት አይሆንም
4. ባለስልጣን ደሙንና ገንዘቡን የተፈቀደ አያደርግበትም
5. በማስረጃ ትንሹ መሆኑ የተጠቆመበት
6. ሰበብ ያልሆነ ነገር ሰበብ ተደርጎ ሲያዝ
7. ወደ ትልቁ መዳረሻ የሆነ ሁሉ ከትንሹ ይመደባል
8. በሸሪዓህ ሽርክ መሆኑ ቢጠቆምም ነገር ግን ትልቁ መሆኑን በማይገልፅበት መልኩ የተገለፀ ከትንሹ ሽርክ ነው፤ ከትልቁ እንደሚመደብ የሚጠቁም ተጓዳኝ እስከሌለው ድረስ።

# አምስተኛው ትምህርት

## ኢሕሳን

የኢሕሳን ምሰሶው: አሏህን ልክ እንደምታየው ሆነህ ልታመልከው ነው፤ ምክንያቱም አንተ ባታየውም እሱ ያይሃልና።

### ኢሕሳን አንድ ምሰሶ እና ሁለት እርከኖች አሉት

**የእይታ አምልኮ(ዒባደቱል ሙሻሀዳህ)**

(አምልኮውን ከማጣጣም ጋ) አላህ ዘንድ ላለው ወዶ፣ ከጅሎና ናፍቆ የሚደረግ አምልኮ ነው፤ የነብያቶችና የመልእክተኞች ዓለይሂሙ ሰላም አምልኮ ነው: ልክ ነብዩﷺ **"...አመስጋኝ ባርያ መሆን የለብኝምን!"** እንዳሉት። ሌሎችም ሊደርሱበት የሚችሉት ደረጃ ነው

**የቁጥጥር አምልኮ (ዒባደቱል ሙራቀባህ)**

(የሚቆጣጠር እንዳለ አስቦ) በፍርሃትና በስጋት የሚደረግ አምልኮ ሲሆን የትኛውም ሙስሊም ከዚህ ደረጃ አይወጣም።

# ተውሒድ ነክ ፈተና

1. ዲነል ኢስላም በጥቅሉ ስንት እርከኖች አሉት? O ሶስት O አራት O አምስት

2. የኢስላም ማእዘናት ስንት ናቸው? O አምስት O ስድስት O ሰባት

3. ኢስላም ከኢማን ከፍ ብሎ ያለ እርከን ነው። ( እውነት - ሃሰት )

4. "**ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ**" የምትለዋ የኢኽላስ የምስክርነት ቃል ስንት ማእዘን ነው ያላት?

O ሰባት O ስምንት O ሁለት

5. የ "**ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ**" ቅድመ መስፈርቶች ስንት ናቸው?

O ስምንት O ሰባት O አምስት

6. እውቀት ከ "**ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ**" ቅድመ መስፈርቶች ሲሆን የሚፈለግበት ትርጉምም:

O አንድን ነገር ተጨባጭ ሁኔታውን ማግኘት O ከአሏህ ውጭ በእውነት የሚመለክ አለመኖሩ

7. የመልዕክተኛው ﷺ ጥሪ ደርሷቸው ያላመኑ ሰዎች ያላቸውን (የክህደት) ፍርድ የተጠራጠረ…

O ትልቁን ክህደት ፈፅሟል O ጥርጣሬው ከእርግጠኝነቱ የሚያመዝን ከሆነ ካፊር አይሆንም

8. በሙሉ ልብ መቀበል ከ "**ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ**" ቅድመ መስፈርቶች መካከል ነው ሲባል...

O ቃሉን O ድርጊት ነክ የሆነውን

O እምነቱን O ሁሉንም

9. ይዩልኝ ይስሙልኝ በ "**ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ**" ቢሆንም በምፅዋት ላይ እንዳለው ይዩልኝ ይስሙልኝ ከትንሹ ሽርክ የሚመደብ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

10. ልቡ ሳያምንበት በቃል ደረጃ "**ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ**" ያለ ሰው …

O የተውሒድ ሰው ነው O ያላመነ ሙስሊም ነው

O ትልቁ ክህደት ያለበት ከሃዲ ነው O ደካማ ኢማን ያለው ነው

11. አንድ ሰው አሏህን እንደሚወደው ወይም እኩል በሆነ መልኩ ነብዩንም ﷺ ቢወድ:

O ትልቁ ክህደት ውስጥ ገብቷል O ትንሹን ክህደት ከዷል O ከከባባድ ወንጀሎች አንዱን ፈፅሟል

12. መውደድ ስንት ክፍሎች አሉት? O አራት O ሶስት O ሁለት

13. ለአሏህ ብሎ መውደድ ለድርጊቱ፣ ለሰሪው፣ ለጊዜም ለቦታም የሚሆን ነው። (እውነት – ሃሰት)

14. ከአሏህ ጋ (እኩል) መውደድ ኢስላማዊ ፍርዱ…

O ትንሹ ሽርክ ነው O ግዴታ ነው O ትልቁ ሽርክ ነው

15. ለአሏህ ብሎ መውደድ ፍርዱ…

O የተፈቀደ ነው O ግዴታ ነው O ትልቁ ሽርክ ነው

16. የሰዎች አምላኪነት(ዑቡዲያ) ስንት ክፍሎች አሉት? O 2 O 3 O 4

17. ከሃድያንን ጨምሮ ፍጥረታት ሁሉ በአሏህ አሸናፊነት ስር ያሉ ባርያዎቹ ናቸው። (እውነት – ሃሰት)

18. **"ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ"** ብሎ ድርጊታዊ በሆነው በኩል ሙሉ በሙሉ ቢተወው፤ ባይሰግድ፣ ባይፆም ወይም የትኛውንም አይነት አምልኮ ባይፈፅም (ይህች የ 'ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ' ቃሉ)፡

O ትጠቅመዋለች O አትጠቅመውም

19. "ባርያውና መልዕክተኛው" የሚለው በሸሃዳ ላይ ያለው ቃል ባርያው ነው ስንል የማይመለክ፤ መልዕክተኛው ነው ስንል ደግሞ የማያስተባብሉት የሚለውን ጠቋሚ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

20. "ሙሓመድም ባርያውና መልዕክተኛው ናቸው" በሚለው የምስክርነት ቃል ተመርኩዘን ባዘዙት መታዘዝ እና የተናገሩትን አምኖ መቀበል … ነው ያልነው ይህ:

O ትርጉሟ ነው O ግድ የሚለው መልዕክቷ ነው

21. ከጌትነት መገለጫዎች መካከል አንዳች ነገርን ለነብዩ ﷺ የሚያደርግ ሰው የሳቸውን ባርያ የመሆን የምስክርነት ቃሉን አልሰጠም። ( እውነት – ሃሰት )

22. የነብዩ ﷺ ምጡቅ መገለጫ የሳቸው _______ መሆን ነው።

O የአሏህ መልዕክተኛ O ባርያውና መልዕክተኛው O የነብያቶች መደምደሚያ

23. "በኢስላም አዲስ መጤ(ቢድዓ)ን አምጥቶ መልካም እንደሆነች አድርጎ የሚያያት ሰው ነብዩ ሙሓመድ ﷺ በተልዕኳቸው ሸፍጥ ሰርተዋል እያለ ነው። ምክንያቱም አሏህ እንዲህ ብሏልና **"ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡**"(አልማኢዳህ 3) ስለዚህ የዚያኔ ዲን ያልሆነ ዛሬ ላይ ዲን አይሆንም።". ይህ የ _____ ቃል ነው?

O ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ O ኢብን ባዝ O ኢማም ማሊክ

24. ነብዩ ሙሓመድ ﷺ የነብዩ _____ ዝርያ ናቸው። O ኢስሓቅ O ኢስማዒል

25. ክፍት ቦታ ሙላ: ነብዩ ﷺ የተወለዱት በ ......................... አመት በ ............... ከተማ ነው። እድሚያቸውም ....... ነበር። ከዚህም ................. አመቱን ነብይ ከመሆናቸው በፊት ሲሆን ........... አመቱን ደግሞ ነብይ እና መልዕክተኛ ሆነው ነው። በ ............... ሱራ ነብይ ሆነው በ ................... ደግሞ ረሱልነትን ተጎናፀፉ።

26. ነብዩ ﷺ የተላኩት ወደ: O ህዝባቸው O ሰው ልጆች O ወደ ሰው ልጆችም ወደ ኢጋንንቱም

27. ሚዕራጅ ማለት የነብዩ ﷺ ከመካ ወደ በይቱል መቅዲስ ያደረጉት ጉዞ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

28. ነብዩ ﷺ በስደት የተጓዙት ወደ...

O ጧኢፍ O ኢትዮጵያ O መዲና O ሁሉም

29. የነብዩ ﷺ አሳሳቢ የሚባሉት ዘመቻዎቹ ስንት ናቸው?

O አንድ O ሁለት O ሶስት O አራት O አምስት

30. የነብዩ ﷺ ልጆች ስንት ናቸው?

O ሶስት O አራት O ሰባት

31. ነብዩ ﷺ የመሰናበቻ ሓጅ አድርገዋል፤ ይህም ከዛ በፊትም ሓጅ ማድረጋቸውን ይጠቁማል። ( እውነት – ሃሰት )

32. የነብዩን ﷺ ታሪክ መማር ...

O ግዴታ ነው O የተወደደ ነው O የተፈቀደ ነው

33. ክፍት ቦታዎቹን ሙላ: ኢማን እንደሸሪዓዊ ፍቹ በ ............. የሚባል፤ በ .............. እምነት ተደርጎ የሚያዝ፤ በ ................ የሚተገበር ነው። በ ............ የሚጨምር ሲሆን በ ............ የሚቀንስ ነው።

34. የኢማን ማእዘናት በቁጥር ስንት ናቸው?

O ስድስት O አምስት O አራት

35. በአሏህ ማመን እንድናምን ግድ የሚያስብላቸው ነገራቶች አሉ። ስንት ናቸው?

O አራት O ሶስት O ሁለት

36. የአሏህን ህልውና የሚጠቁሙ ማስረጃዎች በጥቅሉ ...

O አራት ናቸው O በቁጥር ሊገለፁ አይችሉም

37. ሚካኤል ዝናብ የማውረድ ኋላፊነት የተጣለበት መላኢካ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

38. ልቦና ያላቸው መላኢኮች ናቸው እንጅ መላኢኮች ልቦና የላቸውም። ( እውነት – ሃሰት )

39. አሏህ ስማቸውን ያሳወቀን መፃህፍቶች ብዛት ስንት ናቸው?

O ስድስት O አራት O ሰባት O ብዙ

40. በሁሉም ነብያቶች ላይ አሏህ መፅሃፍን አውርዷል። ( እውነት – ሃሰት )

41. የመጀመሪያው ረሱል አደም ነው። ( እውነት – ሃሰት )

42. ሙሓመድ ﷺ ረሱል እንጅ ነብይ አይደሉም። ( እውነት – ሃሰት )

43. ከመልዕክተኞች መካከል የቆራጥነት ባለቤት የተባሉት ስንት ናቸው?

O አምስት O አራት O ብዙ

44. በመጨረሻው ቀን ማመን ሰዎች ከቀብራቸው እስከመቀስቀስን ጨምሮ ከሞት በኋላ በሚሆነው ሁሉ ማመንን ያጠቃልላል። ( እውነት – ሃሰት )

45. በቅድና በቀደር ማመን የራሱ እርከኖች አሉት፤ ስንት ናቸው?

O አራት O አምስት O ሶስት

46. አሏህ ነገራቶች ከመከሰታቸው በፊት ያውቃልን? ( አዎ – አይ )

47. አሏህ ሰዎች የሚያደርጉትን ሁሉ ያውቃልን? ( አዎ – አይ )

48. አሏህ ሰዎች የሚያደርጉትን ሁሉ በፅሁፍ አስፍሮታልን? ( አዎ – አይ )

49. ባርያ የፈለገውን የሚያደርግበት ነፃ ፍላጎትና መሻት አለው። ( እውነት – ሃሰት )

50. የባርያዎች ስራቸው ፍጡር ነውን? ( አዎ – አይ )

51. ተውሒድ ወደ ______ ይከፈላል።

O ወደ ሁለት O ወደ ሶስት O ወደ አለመግባባት የሚያመራ አይደለም

52. በትልቁ ሽርክ እና በትንሹ ሽርክ መካከል ካሉ ልዩነቶች መካከል አምስቱን ጥቀስ።

1- ……………………………………………………………………………..

2-………………………………………………………………………………...

3-……………………………………………………………………………...

4-……………………………………………………………………………...

5-……………………………………………………………………………...

53. ከትልቁም ከትንሹም ሽርክ አምስት ምሳሌዎችን ጥቀስ

| ትልቁ ሽርክ | ትንሹ ሽርክ |
|---|---|
| ........................................ | .................................. |
| ........................................ | .................................. |
| ........................................ | .................................. |
| ........................................ | .................................. |
| ........................................ | .................................. |

54. የእምነት ኒፋቅ ከመንገዱ የማያስወጣ ትንሹ ሽርክ ላይ የሚመደብ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

55. ኢሕሳን የሚያጠቃልለው

O አንድ ማእዘን O ሁለት ማእዘናት

# ስድስተኛው ትምህርት

## የሶላት ቅድመ መስፈርቶች

**ሶላት ዘጠኝ ቅድመ መስፈርቶች አሉት:**

1. ኢስላም 2. (የአእምሮ) ጤንነት 3. ተምይዝ (ክፉውን ከደጉ መለየት መቻል)

4. ርክሰትን ማስወገድ 5. ነጃሳን ማስወገድ 6. ሃፍረተ ገላን መሸፈን

7. የሶላት ጊዜው መግባቱ 8. ወደ ካዕባ መቅጣጨት 9. ኒያ

## የመጀመርያው ቅድመ መስፈርት: ኢስላም

ተቃራኒው ክህደት ነው፡ አላህን የሚሰድብ ወይም አምልኮን ከአሏህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ የሚሰጥ ቢሰግድ ተውባ አድርጎ ወደ አሏህ እስካልተመለሰ ድረስ ሶላቱ ውድቅ ነው።

## ሁለተኛው መስፈርት: የአእምሮ ጤንነት

ተቃራኒው እብደት ሲሆን ስካርም እዚሁ ለመካተት ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።

## ሶስተኛው ቅድመ መስፈርት: መለየት መቻል

ይህ ሲባል ለአቅመ ተቃራኒ ፆታ መድረስ ማለት አይደለም። ይልቅ ትርጉሙ በነገሮች መካከል መለየት መቻል ማለት ነው፤ በሌላ አገላለፅ ጥያቄ እና መልስን ያውቃል። የተወሰነ ዕድሜ ገደብ የለውም። ብዙውን ጊዜ ግን ዕድሜ 7 ዓመት ሲኮን ነው ነገራቶችን መለየት የሚቻለው። የህፃን ልጅ ሶላት ትክክለኛ የሚሆነው መቼ ነው? ነገራቶችን መለየት ከቻለ ነው። ማለትም እንደምሳሌ ጥያቄ እና መልስን ማወቅ ከቻለ፤ እሳትና ውሃን መለየት ከቻለ ማለት ነው። ካልሆነ ግን ሶላቱ ውድቅ ነው።

## አራተኛ ቅድመ መስፈርት: ርክሰትን ማስወገድ

የሚከተሉትን ያጠቃልላል:

### ትልቁ ርክሰት

ገላን በመታጠብ የሚወገድ ነው።

### ትንሹ ርክሰት

ዉዱእ በማድረግ የሚወገድ ነው።

## አምስተኛ ቅድመ መስፈርት: ነጃሳን ማስወገድ

ሲባል ከሰውነት ፣ ከቦታ እና ከልብስ ማስወገድ ነው። አንድ ሰው እሱ ላይ ነጃሳ ኖሮበት እያወቀ፣ እሱን ማስወገድ የሚችል እና የሚያስታውስ ሆኖ ሳለ ከሰገደ ሶላቱ ውድቅ ነው።

ነጃሳን ማስወገድ በሦስት ምድቦች ይከፈላል:

**ከባድ:**
ይህ የውሻ ነጃሳ ነው። ነብዩ ﷺ የውሻ ለሃጭ ያረፈበትን እቃ ሰባት ጊዜ የመጀመርያውን በአሸዋ እንዲታጠብ አዘዋል። ሙስሊም ዘግበውታል

**ቀላል:**
መጭመቅ ሳይጠበቅበት ውሃ በማፍሰስ ያውም በማርከፍከፍ ይወገዳል። ይህ ምግብ ያልጀመረ ህፃን ልጅ ሽንት፣ መዝይንና መንይን የሚመለከት ነው። ምንም እንኳ ጡሃራ ቢሆንም ነብዩ ﷺ እርጥብ ሲሆን ውሃ ያርከፈክፉበታል ደረቅ ከሆነ ደግሞ ይፈገፍጉት ነበር።

**መካከለኛ:**
በማጠብ የሚወገድ ሲሆን ያም ውሃን ከማፍሰሱ ጋ በመጭመቅ ነው። ይህ መካከለኛና ከባድ ላልሆነው የሚሆን ነው። የወንድም ሆነ የሴት ሽንት እና ሌሎች ነጃሳዎችን የሚመለከት ነው።

## የስድስተኛው ትምህርት ማብራሪያ

**ነጃሳ ነገራቶች**

የሰዎች ሽንት እና አይነምድር፤ እንዲሁም ስጋቸው የማይበሉ እንስሳት ሽንትና ኩሬያቸውም ነጃሳ ነው። እንደ ድመቶች ፣ በቅሎ እና አህያ የመሳሰሉትን ለመጠንቀቅ አስቸጋሪ ከሆኑት እንስሶች በቀር የአውሬዎች ሁሉ ኩሬ እና ሽንትም ነጃሳ ነው። የእርድ ደም / ማለትም: እንስሶች ሲታረዱ የሚፈሳቸው ደም፣ ከሁለቱ የመፀዳጃ ሽለቆዎች የሚወጣ ደምም እንዲሁ ነጃሳ ነው። ከሰው ልጅ ሬሳ እና ነፍስ (የሚፈስ ደም) የሌላቸው፣ እንዲሁም የባህር ሙታኖችና አንበጣ ሲቀሩ ሌሎቹ ሙታኖችም ነጃሳ ናቸው።

### ስድስተኛው ቅድመ ሁኔታ: ሃፍረተ ገላን መሸፈን

ሃፍረተ ገላ ሲባል ሶስት አይነት ነው:

**ከባዱ:**

የጉርምስና ዕድሜ ላይ የደረሱ ሴቶች ሃፍረተ ገላ፣ ከፊቷ በስተቀር መላውን ሰውነት መሸፈን ትሸፍነው፤ በባዕድ ሰዎች ፊት ከሆነች ደግሞ እሱንም መሸፈን ይኖርባታል።

**ቀላሉ:**

እድሜያቸው እንደ ከሰባት እስከ አስር ዓመት ያሉ ወንድ ልጆች ሃፍረተ ገላ፤ ቢያንስ ሁለቱ ብልቶች መሸፈን አለባቸው።

**መካከለኛ:**

በሁለቱ ከተጠቀሱት በስተቀር፤ ከእምብርት እስከ ጉልበት ድረስ መሸፈን ተገቢ ነው። ትከሻዎችን መሸፈን እና ሙሉ በሙሉ ለመልበስ የበለጠ ከመሆኑም ጋ።

### ሰባተኛው ቅድመ መስፈርት: የሶላት ሰአት መግባቱ

ሶላት ጊዜው ከመግባቱ በፊትም ሆነ ካለፈም በኋላ ትክክል አይሆንም። ለበቂ ምክንያት ሲባል ከሌላኛው የሶላት ወቅት ጋ አቆራኝቶ ለመስገድ ካልታሰበ በቀር። ሆን ብሎ ማዘግየቱን ካሰበ ግን ወንጀለኛ ይሆናል።

## ስምንተኛው ቅድመ መስፈርት፡ ወደ ቂብላ መቅጣጨት

ከነዚህም በጉዞ ወቅት የሚሰገዱ የሱና ሶላቶች ልዩ ናቸው፤ በሚጓዝበት ጊዜ ሲሰግድ መጓጓዣው በዞረችበት አቅጣጫ ሁሉ ነውና የሚሰግደው። ለምሳሌ- በጊዜያችን በአውሮፕላን ውስጥ ሲሰገድ። በተጨማሪም ፣ መቅጣጨት የተሳነውና ጠላትን የሚሰጋ ሰውም እንዲሁ ፍርዱ የተለየ ነው።

## ዘጠነኛው ቅድመ ሁኔታ፡ ኒያ

ቦታዋ ልብ ውስጥ ነው። በቃላት መግለጹ መጤ(ቢድዓ) ነው። አንድ ሰው ከሶላቱ ከተወሰነ ጊዜ በፊት (እንደሚሰግድ) ቢያስብ ወይም የጊዜውን ግዴታ ለመስገድ በሚል (ጥቅል በሆነ) መልኩ ቢያስብ እንኳ ሶላቱ ተቀባይነት ያለው ነው።

## አሳሳቢ ጥቆማዎች

1- ሆን ብሎ፣ ባለማወቅ አሊያም በመርሳት ቅድመ ሁኔታን መተው ተቀባይነት የለውም ፤ አንድ ሰው ባለማወቅ ወይም ረስቶ ነጃሳ እያለበት ቢሰግድ ግንሶላቱ ትክክል ነው፤ ምክንያቱም ይህ ከመተው አይነቶች እንጅ ከማድረግ አይነቶች አይደለምና።

2- ቅድመ ሁኔታዎች ከአምልኮው ውጭም በፊትም ይሆናሉ። የአምልኮው ተግባር እስኪጠናቀቅ ድረስ መገኘታቸው ግን የግድ አስፈላጊ ነው።

# ሰባተኛው ትምህርት

## የሶላት ማእዘናት

የሶላት ማእዘናት አስራ አራት ናቸው:

1- ከተቻለ መቆም 2- ተክቢረተል ኢሕራም (በሶላቱ መጀመርያ "አሏሁ አክበር" ማለት)

3- ሱረቱል ፋቲሓ(አልሓምዱ)ን መቅራት 4- ሩኩዕ መውረድ 5- ከሩኩዕ በኋላ መልሶ መቆም 6- በሰባቱ የሰውነት አካላት ሱጁድ ማድረግ 7- ከሱጁድ በኋላ መልሶ መነሳት

8- በሁለቱ ሱጁዶች መካከል መቀመጥ 9- በእያንዳንዱ ክንዋኔ ላይ ሁሉ መረጋጋት

10- እያንዳንዱን ማእዘን በተራው ማድረግ 11- የመጨረሻው ተሸሁድ

12- ለተሸሁድ(አተሕያቱ) መቀመጥ 13- በነብዩﷺ ላይ ሶለዋት ማውረድ

14- በሁለቱም በኩል ማሰላመት

## የመጀመርያው ማእዘን: ከተቻለ መቆም

### ተጨማሪ ሶላቶች:

አንድ ሰው ቁጭ ብሎ የሚሰግድ ከሆነ ሶላቱ ትክክለኛ ነው። ሆኖም አጅሩ ግን ቆሞ ከሚሰግደው ሰው ግማሽ ነው። አንድ ሰው ተኝቶ ቢሰግድ ደግሞ ተቀምጦ ከሚሰግደው ግማሹን አጅር ያገኛል።

### የግዴታ ሶላቶች:

በግዴታ ሶላቶች ደግሞ መቆሙ ምሰሶ ነው። አንድ ሰው በጭራሽ መቆም ካልቻለ ወይም መቆም ቢችልም ነገር ግን ትኩረት ማድረግ የማይችል ከሆነ ግዴታነቱ ይቀርለታል። አንድ ሰው ከሶላቱ የተወሰነውን ክፍል እንኳ መቆም ከቻለ መቆም ይኖርበታል።

## ሁለተኛው ማእዘን፡ ተክቢረተል ኢሕራም

“አሏሁ አክበር” ከሚለው ቃል ውጭ አያብቃቃም።

## ሶስተኛው ማእዘን፡ ፋቲሓ(አልሓምዱ) መቅራት

በእያንዳንዱ ረከዓ ውስጥ በዝምታም ሆነ ጮክ ብሎ በሚሰገደው ሁሉ አንቀፆቿን፣ አናባቢዎቿን፣ ቃላቶቿን እና ፊደላቶቿን አሟልቶ በቅደም ተከተል መቅራቱ የግድ ነው። አንድ ሰው ኢማሙን ያገኛቸው ሩኩዕ ላይ ሆኖ ከሆነ ብቻ ትቀራለች።

## ዘጠነኛው ማእዘን፡ በእያንዳንዱ ክንዋኔ ላይ ሁሉ መረጋጋት

መረጋጋቱ በእያንዳንዱ ማእዘን ላይ በሚባለው ዚክር ነው የሚረጋገጠው።

## አሳሳቢ ጥቆማዎች

ማእዘኖቹ በአምልኮ ውስጥ ያሉ ናቸው። ከማእዘናቶቹ መካከል አንዳቸውንም ሆን ተብሎ፣ ባለማወቅ ወይም ደግሞ በመርሳት ከተተወ ሶላቱ ተቀባይነት የለውም። በሱጁደ ሰህው (የመርሳት ሱጁድም) የሚጠገን አይደለም። በሰአቱ ማእዘን የተወበትን ሶላት እንዲደግም ይታዘዛል። አንድ ሰው ሁሉንም ማእዘናትን እያጓደለ ለሰገደባቸው ቀደም ያሉ ሶላቶች ግን ባለማወቁ (ከተጠያቂነት ነፃ በሆነ መልኩ) ውዝር ይኖረዋል። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ሶላቱን ያበላሸውን ሰውየ ሰውየው የተወው ከሶላት ማእዘናት አንዱ የሆነችውን መረጋጋት ከመሆኑም ጋ በወቅቱ የያዘውን ሶላት እንጅ ሁሉንም ሶላት እንዲደግም አላዘዙምና። ። አላህ ይበልጡን ዐዋቂ ነው።

# ስምንተኛው ትምህርት

## የሶላት ዋጅቦች(ግዴታዎች): የሶላት ግዴታዎች ስምንት ናቸው

1- ከተክቢረተል ኢሕራም(የመጀመርያው "አሏሁ አክበር") ውጭ ያሉት ተክቢራዎች (አሏሁ አክበር) ሁሉ

2- ለኢማሙም ይሁን ለተከታዮቹ *"ሰሚዐሏሁ ሊመን ሓሚዳህ"* ማለታቸው።

3. እያንዳንዳቸው *"ረበና ወለከል ሓምድ"* ማለታቸው

4. በሩኩዕ ጊዜ *"ሱብሓነ ረብየል ዓዚም"* ማለት

5. በሱጁድ ጊዜ *"ሱብሓነ ረቢየል አዕላ"* ማለት

6. በሁለቱ ሱጁዶች መካከል *"ረቢ ግፊርሊ"* ማለት

7. የመጀመርያው ተሸሁድ

8. ለተሸሁድ መቀመጥ

## <u>አሳሳቢ ጥቆማዎች</u>

ሩኩዕ ላይ "ሱብሓነ ረብየል ዓዚም" በሚለው ቃል ማለቱ ግዴታ ነው። ከዚያም ከነብዩﷺ በመጡ ሌሎች አባባሎች ማለቱ ይመከራል። እንደዚሁም በተመሳሳይ ሱጁድ ላይ እያለ "ሱብሓነ ረቢየል አዕላ" በማለት ከዚያም በሌላ ከነብዩﷺ በመጡ መጨመሩ አስፈላጊ ነው።

# ዘጠነኛው ትምህርት

## ተሸሁድ (አት-ተሒያቱ)

የተሸሁድ ፍቹ - “ምስጋና፣ ሶለዋት እና መልካም ሁሉ ለአሏህ የተገባ ነው። አንተ ነብይ ሆይ! ሰላም በአንተ ላይ ይሁን የአላህ እዝነት እና በረከቱም እንዲሁ በአንተው ላይ ይሁን፤ ሰላም በእኛ ላይ፣ በደጋግ የአላህ ባሪያዎችም ላይ ይሁን። ከአላህ ውጭ በእውነት ሊመለክ የሚገባው እንደሌለ ሙሓመድም የአሏህ ባርያና መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።”

ከዚያም ለነቢዩﷺ ሶለዋት በማውረድ ለሳቸው በረካን በመሻት መልኩ ዱዓ የሚያደርግ ሲሆን እንዲህ ይላል፤ ‹አላህ ሆይ በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ ሶለዋትህን እንዳወረድከው በሙሓመድና በቤተሰቦቹም ላይ ሶለዋትህን አውርድ። አንተ በእርግጥ የላቀ ምስጋና የሚገባህ ነህና። አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ እንደባረክከው በመሐመድ እና በመሐመድም ቤተሰቦች ላይ በረካህን አውርድ። በርግጥ አንተ የላቀ ምስጋና የሚገባህ ነህና።"

ከዛም በመጨረሻው ተሸሁድ ላይ ከጀሃነም ቅጣት፣ ከቀብር ቅጣት፣ ከህይወት እና ሞት ፈተና እና ከመሲሑ ደጃል ፈተና የአሏህን ጥበቃ ይለምናል: - “አሏህ ሆይ! ከጀሃነም ሥቃይ በአንተው እጠበቃለሁ ፣ ከመቃብር ቅጣት በአንተው እጠበቃለሁ፣ ከሕይወት እና ከሞት ፈተናዎች በአንተው እጠበቃለሁ፣ ከደጃልም ፈተና በአንተው እጠበቃለሁ።” (ቡኻሪ እና ሙስሊም)።

ከዚያም ከዱዓዎች አማርጦ በሻው በተለይም ከነብዩ ﷺ ማስረጃ ባላቸው ይማፀናል። ከነዚህም: “አሏህ ሆይ! አንተን በማስታወስ፣ በማመስገንና ባማረ መልኩ እንድገዛህ አግዘኝ። አሏህ ሆይ! እኔ ራሴ በእጅጉ በድያለሁ፤ ወንጀልን ደግሞ ከአንተው ውጭ የሚምር የለም፤ በመሆኑም ከአንተው ዘንድ የሆነ መሃርታህን ለግሰኝ፤ መሃሪው እና አዛኙ አንተው ነህና።”

በዙህር፣ ዓሱር፣ መግሪብ እና ዒሻእ ሶላቶች ላይ ግን ከመጀመሪያው ተሸሁድ ካለ በኋላ ለሦስተኛው ረከዓህ ይቆማል። በዚህ በኩል የመጡ ሓዲሦች ካላቸው ጥቅል መልዕክት ከተሸሁዱ ጋ በነብዩﷺ ላይ ሶለዋት ማውረድን ካከለበት በላጭ ይሆንለታል።

# አስረኛው ትምህርት

## የሶላት ተጨማሪ ሱናዎች

1- የመክፈቻ ዱዓእ

2- ቆሞ ሳለ፣ ከሩኩዕ በፊት እና ከዛም በኋላ የቀኝ እጅን መዳፍ በግራ እጅ ላይ አሳርፎ ደረት ላይ ማድረግ

3- በመጀመርያው ተሸሁድ፣ ወደ ሩኩዕ ሲወረድ፣ ከሩኩዕ ቀና በሚባልበት ጊዜ እና ከመጀመርያው ተሸሁድ ወደ ሁለተኛው ተሸሁድ በሚሸጋገሩበት ጊዜ ጣቶችን ዘርግቶ በትከሻ ወይም በጆሮ ትይዩ እኩል አድርጎ ሁለቱን እጆች ማንሳት

4. በሩኩዕ እና በሱጁድ ጊዜ የሚባለውን ከአንድ ጊዜ በላይ ማለቱ

5. ከሩኩዕ ቀና ካሉ በኋላ *"ረበና ወለከል ሓምድ"* ከሚለው በላይ መጨመሩ፤ በሁለቱ ሱጁዶች መካከል *"ረቢግፊርሊ"* ከሚለው በኋላ ያለ የድግግሞሽ ጭማሪ

6- በሩኩዕ ጊዜ ጭንቅላትን ከጀርባ ጋ እኩል ለጥ ማድረጉ

7- በሱጁድ ጊዜ ክርናችንን ከጎናችን ማራቅ፤ ሆድን ከታፋ ማራቅ እና ታፋን ደግሞ ከባት ማራቅ

8- በሱጁድ ጊዜ ክርንን ከመሬት ማንሳት

9- በመጀመርያው ተሸሁድ እና በሁለቱ ሱጁዶች መካከል መቀመጫን የግራ እግር ውስጠኛው ክፍል ላይ አሳርፎ የቀኝ እግርን ተረከዝ ተክሎ መቀመጥ።

10- ሶስትና አራት ረከዓ በሚሰገድባቸው ሶላቶች በመጨረሻ ተሸሁድ ጊዜ ተወሩክ በሚባለው አቀማመጥ መቀመጥ፤ ያም፡ መቀመጫን መስገጃው ላይ አሳርፎ የግራ እግርን በተከልነው የቀኝ እግር ተረከዝ ስር ማሾሎክ

11- በመጀመርያውና በሁለተኛው ተሸሁድ ጊዜ ከሚቀመጥበት ጊዜ አንስቶ እስከ ተሸሁድ መጨረሻ ድረስ ባለው ጠቋሚ ጣትን መጠቆም እና በዱዓም ጊዜ ማንቀሳቀስ።

12- ለነብዩና ለቤተሰቦቻቸው፤ ለነብዩ ኢብራሂምና ለቤተሰቦቻቸውም ﷺ በመጀመርያው ተሸሁድ ጊዜ ሶለዋትና በረካን ከአሏህ እንዲወርድላቸው አሏህን መማፀን።

13- በመጨረሻው ተሸሁድ ጊዜ ዱዓእ ማድረግ

14- በፈጅር ሶላት፣ በጁሙዓህ ሶላት፣ በሁለቱ ዒዶች ሶላት፣ በሶላተ ኢስቲስቃእ(ዝናብ እንዲመጣ የሚሰገድ ሶላት) በዒሻእ እና በመግሪብ የመጀመርያዎቹ ሁለት ረከዓዎች ላይ ጮክ ብሎ መቅራት

15- በዙህር እና በዓሱር እንዲሁም በመግሪብ ሶላት ደግሞ በሶስተኛው ረከዓ በዒሻእ ሶላትም በመጨረሻዎቹ ሁለት ረከዓዎች በዝግታ መቅራት

16- ከፋቲሓ በኋላ ጨምሮ መቅራት

ከጠቀስናቸው ውጭ ያሉ ሌሎች በሶላት ውስጥ የሚደረጉ ሱናዎችንም ከመጠባበቅ ጋ፤ ከነዚህም: ሰጋጁ ኢማም ይሁን ተከታይ አልያም ብቻውን የሚሰግድም ቢሆን “ረበና ወለከል ሓምድ” ካለ በኋላ የሚጨምረው ሱና ነው። እንዲሁም: በሩኩዕ ጊዜ ጣቶችን ለያይቶ ታፋዎቹ ላይ ማስቀመጡ ይገኝበታል።

## የመክፈቻ ዱዓእ

*“አሏሁመ ባዒድ በይኒ ወበይነ ኸጧያየ ከማ ባዐድተ በይነል መሽሪቂ ወል መግሪብ አሏሁመ ነቂኒ ሚነል ኸጧያ ከማዩነቀ ሠውቡል አብየዱ ሚነ ደነስ አሏሁመግሲልኒ ሚን ኸጧያየ ቢልማኢ ወሠልጂ ወልበረድ”*

*“አላህ ሆይ ፣ በምስራቅና በምእራብ መካከል እንዳደረግከው ርቀት በእኔና በኃጢያቶቼ መካከል ያለውንም ርቀት እንዲሁ አድርግ። ከኃጢአቶቼም በውሃ ፣ በበረዶ እና በብርድ እጠበኝ።”* (ቡኻሪ እና ሙስሊም) ወይም ደግሞ *"ሱብሓነከሏሁመ ወቢሓምዲከ ወተባረከ ኢስሙከ ወተዓላ ጀዱከ ወላኢላሃ ገይሩክ”* ትርጉሙ “አሏህ ሆይ! ምስጋና ይገባህና ጥራት የተገባህ ፍፁም ነህ፤ ስምህ ልቅና የተገባው ነው፤ ማንነትህ ከፍ ያለ ነው፤ ከአንተም ውጭ በእውነት የሚመለክ የሌለ ጌታ ነህ።"

# አስራ አንደኛው ትምህርት

**ሶላትን ውድቅ የሚያደርጉ ነገራቶች**

ሶላትን ውድቅ የሚያደርጉ ነገራቶች ስምንት ናቸው:

1- ከማስታወስ እና ከማወቅም ጋ መናገር - የረሳ ወይም የማያውቅ ግን ሶላቱ ውድቅ አትሆንበትም።

2- ሳቅ። 3- መብላት። 4- መጠጣት 5- የሃፍረተ ገላ መገለጥ 6- ከቂብላ አቅጣጫ በብዙ መንሻፈፍ።

7- እየሰገደ እያለ ተከታታይ የሆነ አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎች ማድረግ 8- ዉዱእ ማፍረስ

**የመጀመርያው አፍራሽ:** ከማስታወስ እና ከማወቅም ጋ መናገር

ኢማሙ ሲረሳ ወይም በቁርዓን ሲሳሳት ለመርዳት ካልሆነ በስተቀር ::

በሶላት ጊዜ ሊኖሩ የሚችሉ እንቅስቃሴዎች ሁኔታ

| የተከለከሉ እንቅስቃሴዎች: | የተወገዙ እንቅስቃሴዎች: | የተፈቀዱ እንቅስቃሴዎች: | የሚፈለጉ እንቅስቃሴዎች: | ግዴታ የሆኑ እንቅስቃሴዎች: |
|---|---|---|---|---|
| እንደ መብላት ያሉ ብዙ አላስፈላጊ ተከታታይ እንቅስቃሴዎች። | ትንሽ እንደ መዞር ያሉ አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን። | ፂምን እንደ ማከክ ያሉ አስፈላጊ እንቅስቃሴዎች። | የሰፍ ክፍተቶች መዝጋትን የመሰሉ ሶላትን ሙሉ ለማድረግ አሰፈላጊ የሆኑ እንቅስቃሴዎች:: | የሶላቱ ትክክለኛነትን የሚወስኑ ነጃሳን እንደ ማስወገድ የመሰሉ እንቅስቃሴዎች። |

## የአስራ አንደኛው ትምህርት ማብራርያ

### አስፈላጊ ጥቆማዎች

የሶላት ቅድመ ሁኔታዎች፣ ማእዘናት፣ ግዴታዎቹንና ሱናዎቹን አሳልፈናል። ልዩነታቸውስ ምንድን ነው?

| ሱና | ግዴታ | ማእዘን | ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|
| በአምልኮው ምንነት ውስጥ የሚካተት ነው | | | ከአምልኮው ምንነት ውጭ ነው |
| ከአምልኮው ክፍሎች በሆነው ክፍል ብቻ የተገደበ ነው | | | በመላ አምልኮው ዘላቂ ነው |
| አለማወቁ፣ መርሳቱም ሆነ ሆን ብሎ መተው ዑዝር ይሆንለታል | ሆን ብሎ እስካልሆነ ድረስ አለማወቁ ወይም መርሳቱ ዑዝር ይሆነዋል | አለማወቁ፣ መርሳቱም ሆነ ሆን ብሎ መሆኑ ለመቅረቱ (ዑዝር) በቂ ምክንያት አይሆንም | |
| | በሱጁደ ሰህው የሚጠገን ነው | በሱጁደ ሰህው አይጠገንም | የመርሳት ሱጁድ (ሱጁደ ሰህው) አይደረግለትም |

## የአስራ አንደኛው ትምህርት ማብራርያ

**ሱጁደ ሰህው (የመርሳት ሱጁድ)**

የሱጁደ ሰህው ምክንያቶች ሶስት ናቸው:

**ጥርጣሬ:**

ለምሳሌ አንድ ሰው የሰገደው ሁለት ወይንስ ሶስት መሆኑን ከተጠራጠረ፤ ይህ ሁለት አይነት ነው:

**መቀነስ:**

ለምሳሌ ከሶላቱ ግዴታዎች መካከል አንዳች ነገር አልፎበት ቢቀንስ

**መጨመር:**

አንድ ሰው ሩኩዕ ወይም ሱጁድ ወይም መቆምን ወይም መቀመጥን ቢጨምር

**በአምልኮው ውስጥ የሆነ ጥርጣሬ:**

ጥርጣሬው ብዙ ከነበረ ዞርም አይልለትም፤ ትንሽ ከሆነ ግን እሱ ዘንድ አመዛኝ ብሎ በሚያስበው ላይ ተንተርሶ ቀሪውን ይገነባል። እሱ ዘንድ አማካኝ ሆኖ ከታየው ደግሞ ቢያንስ በሚለው ላይ ተንተርሶ ቀሪውን ይገነባል።

**አምልኮውን ካጠናቀቀና ከቋጨ በኋላ መጠራጠር:**

እንዲህ አይነቱን እርግጠኛ እስካለሆነ ድረስ ቦታም የሚሰጠው አይሆንም።

**ጥቆማ:**

- አንድ ሰው በሱጁደ ሰህው ከረሳ አንዳችም ነገር ሳይጠበቅበት ሶላቱ ትክክለኛ ነው።
- አንድ ሰው ማእዘን የሆነን ነገር ከረሳ እሷኑ እስኪያመጣት እና ኋላም ሱጁደ እህው እስኪሰግድ ድረስ ሶላቱ ትክክል አትሆንም።
- አንድ ሰው ግዴታ የሆነን ነገር ረስቶ ትቶ ቦታውንም ካለፈው የመርሳትን ሱጁድ (ሱጁደ ሰህው) ይወርዳል።

## የሶላት አሰጋገድ ሁኔታ ስእላዊ ማጠቃለያ

- በመጀመርያ አንድ ሙስሊም በቤቱ ሆኖ (ዉዱእ በማድረግ) ንፅህናውን ጠብቆ ጥሩውን መልበስ አለበት
- በእግሩም ይሁን በመጓጓዣ በእንቅስቃሴው እርጋታንና ስርዓትን ተላብሶ፤ ማለትም፡ ሳይጣደፍ፣ ግራ ቀኝ ሳይውረገረግ እንዲሁም ድምፁን ከፍ ሳያደርግ መሄድ ይኖርበታል
- (የለበሰውን ልብስ ሰብስቦት ከነበረ የልብሱን እጅጌ መዘርጋት ይኖርበታል)




- አንዴ መስጅድ ከደረሰ ጫማዎቹን አውልቆ በተመደበላቸው ቦታ ያስቀምጣል፤ ዱንያ ነክ ነገሩንም እዛው ይጥላል፤ በመስጅድ ውስጥ መሸጥ፣ መለወጥና የጠፋን እቃ አፋልጉኝ ብሎ ማወጅ ሓራም ነው።
- በሚገባበት ጊዜ ቀኝ እግሩን በማስቀደም እንዲህ ይላል: ***"ቢስሚላሂ ወሶላቱ ወሰላሙ ዓላ ረሱሊላሂ አሏሁመፍተሕሊ አብዋበ ራሕመቲክ"*** እንዲሁም ሲወጣ ደግሞ የግራ እግሩን አስቀድሞ እንዲህ ይላል: ***"ቢስሚላሂ ወሶላቱ ወሰላሙ ዓላ ረሱሊላሂ አሏሁመ ኢኒ አስአሉክ ሚን ፈድሊክ"***
- ወደ ውስጥ ከገቡ በኋላ ወንዶች በፊት ለፊት ካሉት ሶፎች ይሆናሉ ሴቶች ደግሞ ከኋለኞቹ ሶፎች ይሆናሉ
- ሶላቱ ተጀምሮ ከነበረ አንድ ሰው ‹ አላሁ አክባር › በማለት ኢማሙ በማንኛውም ሁኔታ ላይም ቢሆን መቀላቀል አለበት። ኢማሙን ያገኛቸው ቆሞ ወይም ሩኩዕ ላይ ከሆነ እንደሙሉ ረከዓ ይቆጠርለታል። ኢማሙ ሶላቱን ሲያጠናቅቅ ዘግይቶ ኢማሙን የተቀላቀለው ሰው ይነሳና ያመለጠውን ያጠናቅቃል።


- አንድ ሰው ወደ መስጊድ ሲገባ እና ሶላቱ ገና ካልተጀመረ ከሶላቱ በፊት የሶላቱን ተያያዥ ሱና መስገድ አለበት። ሶላቱ ከፊት የተቆራኘ ሱና ከሌለው ግን አንድ ሰው መስጊድ ውስጥ ከመቀመጡ በፊት (የገባው ወደ መስጅድ በመሆኑ) እንዲሁ ሁለት ረከዓ መስገድ አለበት።
- አንድ ሰው ሲገባ ሶላቱ ካልተጀመረ እንዲጀመር በሚል ሰአቱን መመልከት አልያም ጉሮሮውን በማፅዳት የመስጅዱን ክብር መዳፈር የለበትም።
- ኢማምም ሆነ ብቻውን የሚሰግድ ሰው ሲሰግድ ከለላ(ሱትራ) ነገር ከፊት ለፊቱ ማድረጉ ይመከራል። ኢማሙ ከፊት ለፊቱ ሱትራ ካደረገ ግን ከኋላው ለሚሰግዱት ሰዎች በቂያቸው ነው።




- በቆመበት ጊዜ በእግሮቹ መካከል ያለው ርቀት ሳይበልጥም ሳያንስም በትከሻዎቹ መካከል እንዳለው ርቀት መሆን አለበት። የእግሮቹን ጫፍ ደግሞ ቀጥ አድርጎ ወደቂብላ አቅጣጭቶ መቆም አለበት።



- አንድ ጊዜ የሶላቱን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ከፈጸመ በኋላ እጆቹን በጆሮዎቹ ወይም በትከሻዎቹ ትይዩ ወደ ላይ ከፍ በማድረግ “አሏሁ አክባር” ይላል። የመዳፎቹን ውስጠኛ ክፍል ወደ ቂብላ ያቅጣጫል።



- ከዚያም የቀኝ እጁን መዳፍ በግራ እጁ ጀርባ እና አንጓ ውጫዊ ክፍል ላይ ያሳርፈዋል፤ ወይም በቀኝ እጁ የግራ እጁን አንጓ ይይዛል።



- አይኑንም ወደ ሱጁድ ማረፊያ ቦታ ላይ ያሳርፋል፤ ወደ ሌላ ቦታም አይዟዟርም።



- ከዚያም በአንደኛው ረከዓ ላይ ብቻ “የመክፈቻ ዱዓእ” ማድረጉ ይመከራል፤ ከነብዩﷺ በመጡ የተለያዩ ሶላቶች “የመክፈቻ ዱዓዎችን” በመለዋወጥ ማለቱ የተሻለ ይሆንለታል።

- ከዚያም ከነብዩﷺ በመጡ “አዑዙ ቢላሂ ሚነ -ሽ -ሸይጧኒ -ር- ሯጂም" ን በመሰሉ መጠበቂያ ቃላት በአሏህ ይጠበቃል።

- ከዚያም ‹ቢስሚላሂ -ር- ሯሕማኒ -ር- ሯሒም› ይላል።


- ከዚያም ፋቲሓን ከአናባቢዎቿ፣ ቃላቶቿ፣ ፊደላቶቿ እና አናቅፆቿ ጋ አሟልቶ በትክክል ይቀራል።

- ከዚያም እንደገና የመጠበቂያ ቃላትን(አዑዙ ቢላህን) ሳይጨምር ከቁርአን የገራለትን መቅራቱ ይመከራል። የሱራው መጀመርያ ላይ ከሆነ የሚቀራው ብቻ ቢስሚላህ ይበል።

- ከዚያም ከሶላቱ መጀመርያ ጋር በተመሳሳይ መልኩ እጆቹን ከፍ አድርጎ “አሏሁ አክበር” ብሎ ሩኩዕ ይወርዳል።

- የእጆቹን ክርን ሳያጥፍ ጉልበቶቹን በመዳፉ ይዞ፤ ጀርባውን ከጭንቅላቱ በስትክክል አድርጎ ያጎበድዳል።

- በግዴታ አንድ ጊዜ “ሱብሓነ ረቢየል ዓዚም” ይላል። ከነብዩﷺ ከመጡ ሌሎች ዱዓዎችም መጨመሩ ይመከራል።



- ከዚያም ካጎበደደበት እጆቹን በጆሮዎቹ ወይም በትከሻዎቹ ትይዩ አድርጎ ከፍ እያለ ተስተካክሎ ከመቆሙ በፊት “ሰሚዐሏሁ ሊመን ሓሚዳህ” ይላል።

- ተስተካክሎ ሲቆም ደግሞ “ረበና ወለከል ሓምድ” ይላል።

- ከዚያም እጆቹን ከፍ ሳያደርግ በሰባቱ የሰውነት ክፍሎቹ [በግንባሩ ከአፍንጫው ጋ፣ ሁለት የእጅ መዳፎቹ፣ ሁለት ጉልበቶቹ፣ የሁለት እግር ጣቶቹ ውስጠኛው ክፍሉ] ሱጁድ ያደርጋል።

- እጅና ብብቱ እንዳይገናኙ፤ ብብቱ እና ታፋውም፤ ታፋውና ባቱም እንዳይገናኙ ከፈትፈት ያደርገዋል፤ የእጆቹን ክርንም ከመሬት ያነሳል።



- አንድ ጊዜ “ሱብሓነ ረቢየል አዕላ” ማለት የግድ ነው። ሌሎች ከነብዩﷺ በመጡ ዱዓዎች መጨመሩ ይወደድለታል፤ በፈለገው ዱዓ መማፀንም የሚፈቀድለት ቢሆንም ከነብዩﷺ በመጡ ዱዓዎች ማለቱ በላጭ ይሆንለታል።
- ከዚያም ‹አላሁ አክባር› በማለት መቀመጫን የግራ እግር ውስጠኛው ክፍል ላይ አሳርፎ የቀኝ እግርን ጣቶች ወደ ቂብላ በማቅጣጨት ተረከዝን በመትከል “ኢፍቲራሽ” የሚባለውን አይነት አቀማመጥ ይቀመጣል። የእጆቹን መዳፍ በታፋዎቹ ላይ ያደርጋል። ይህ አቀማመጥ ከባለ ሶስት እና አራት ረከዓ ሶላቶች የሁለተኛው ተሸሁድ ውጭ ባሉ አቀማመጦች ላይ ሁሉ የሚቀመጠው አቀማመጥ ነው። በዚህ በተጠቀሰው የሁለተኛ ተሸሁድ ላይ ግን የግራ እግሩን በቀኝ እግሩ ስር በማሸሎክ “ተወሩክ” የሚባለውን አይነት አቀማመጥ ነው የሚቀመጠው።



- ከዚያም አንድ ሰው "አላሁ አክባር" በማለት እንደመጀመርያው ሱጁድ ይወርዳል።

- ከዚያም "አሏሁ አክባር" በማለት ለሁለተኛው ረከዓ በመነሳት ከተክቢረተል ኢሕራም እና ከመክፈቻው ዱዓእ ውጭ በመጀመርያው ረከዓ ያደረገውን ሁሉ ያደርጋል።

- ሁለተኛውን ረከዓ ካጠናቀቀ በኋላ ለተሸሁድ ይቀመጣል።

- ጠቋሚ ጣቱን በመዘርጋት የመካከለኛውን ጣቱን ደግሞ ከአውራ ጣቱ ጋ አያይዞ ክብ አድርጎ ጠቋሚ ጣቱን እያንቀሳቀሰ ዱዓውን ያደርጋል።

- አት-ተሕያቱን ማለቱ የግድ ነው።

- የሁለት ረከዓ ሶላት ከሆነ ደግሞ ከተሸሁዱ በኋላ የሚባለውን በኢብራሂም ላይ የሚደረገውን ሶለዋት ይላል፤ ከአራቱም ደግሞ የአሏህን ጥበቃ ይለምናል፡ **"አሏሁመ ኢኒ አዑዙበከ ሚን ዓዛቢ ጀሃነም፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ዓዛቢል ቀብር ወአዑዙቢከ ሚን ፊትነቲ ደጃል፤ ወአዑዙቢከ ሚን ፊትነቲል መሕያ ወልመማት"** ይላል ትርጉሙም፡ "አሏህ ሆይ! ከእሳት ቅጣት በአንተው እጠበቃለሁ፤ ከመቃብር ቅጣት በአንተው እጠበቃለሁ፤ ከዳጃልም ቅጣት በአንተው እጠበቃለሁ፤ ከሕይወትና ሞት ሙከራዎች በአንተው እጠበቃለሁ"።

ከዚያም በፈለገው መልኩ ዱዓ ያደርጋል፤ በላጭ የሚሆንለት ግን **"አሏሁመ አዒኒ ዓላ ዚክሪከ ወሹክሪከ ወሑስኒ ዒባደቲክ"** ትርጉሙም "አሏህ ሆይ! አንተን በማስታወስ፣ በማመስገንና አምልኮየን ለአንተው በማሳመር ላይ አግዘኝ።" በመሰሉ ከነብዩ ﷺ በመጡ ዱዓዎች ማለቱ ነው።



- ከዚያም ጭንቅላቱን ብቻ በማንቀሳቀስ በትከሻው ሳይዞር፤ ጭንቅላቱንም ወደ ላይም ወደ ታች ሳያደርግ በእጁም ጥቆማ መስጠት ሳይጠበቅበት ወደ ቀኝና ግራ ያሰላምታል።



- ሶላቱ ባለ 3 ወይም 4 ረከዓ ሶላት ከሆነ የመጀመሪያውን ተሸሁድ ካለ እና እንደተጨማሪ ደግሞ ኢብራሂምይ ሶለዋት ካለ በኋላ ይነሳል ።

- "አላሁ አክባር" ብሎ 3ኛውንም ረከዓ ይሰግዳል፤ ባለ ሶስት ረከዓ ሶላት ከሆነ ለመጨረሻው ተሸሁድ ይቀመጣል። ባለ አራት ረከዓ ከሆነ ደግሞ አንዷቷንም ይጨምራትና ለመጨረሻው ተሸሁድ ይቀመጣል።

- ኢብራሂምይ የሆነውን ሶለዋትም ይልና፡ "አሏሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚን ዓዛቢ ጀሃነም፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ዓዛቢል ቀብር፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ፊትነቲ ደጃል፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ፊትነቲል መሕያ ወልመማት" በማለት ከአራቱ የአሏህን ጥበቃ ይማፀናል። ከዚያም በመረጠው ሁሉ መማፀን ይችላል፤ በላጩ የሚሆንለት ግን "አሏሁመ አዒኒ ዓላ ዚክሪከ ወሹክሪከ ወሑስኒ ዒባደቲክ" ቢል ነው።

- የግዴታ ሶላት ከሆነ ከሶላት በኋላ የሚባሉትን ከነብዩﷺ የመጡ ዚክሮችን ማለቱ የተወደ ይሆንለታል።

- **"አስታግፊሩሏህ! አስታግፊሩሏህ! አስታግፊሩሏህ! አሏሁመ አንተ ሰላም ወሚንከ ሰላም፤ ተባረክተ ያዘል ጀላሊ ወልኢክራም"**

- ከዚያም እንዲህ ይላል ‹ሱብሐነሏህ፤ አል ሓምዱላላህ፤ አላሁ አክባር" እያንዳንዳቸውን 33 ጊዜ ካለ በኋላ ሁሉም በድምር 99 ጊዜያት ይሆናሉ። ከዚያም በ "ላ ኢላሃ ኢለሏሁ ዋሕደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሓምዱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር" 100 ኛውን ይሞላል። ትርጉሙም "ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው ምንም ነገር የለም ፤ ተጋሪ የሌለው ብቸኛ ነው ፣ ግዛቱ የእርሱ ነው፤ ምስጋናም ለእርሱ ነው፤ እሱም በነገሩ ላይ ሁሉ ቻይ ነው።»

- ከዚያም አያተል-ኩርሲይ **"አሏሁ ላ ኢላሃ ኢላ ሁወል ሓዩል ቀዩም…"** (ገጽ 11) ፣ ሱራ አል ኢኽላስ/ **"ቁል ሁወሏሁ አሓድ… "** (ገጽ.33) ፣ ሱረቱል ፈለቅ **"ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ…"** (ገጽ.34) ፣ እና ሱረቱን-ናስ **"ቁል አዑዙ ቢረቢናስ…"** (ገጽ 36) ያነባል ። (**ል.በ.** ገጽ 11,33 ፣ 34 እና 36 ማለት በዚህ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡበት ነው)።

## አስፈላጊ ጥቆማ -

- ከሶላት ትክክለኛነት ቅድመ ሁኔታዎች መካከል በሶላቱ ውስጥ መሸፈን ያለባቸውን የሰውነት ክፍሎች መሸፈን አንዱ ነው። በሶላቱ ወቅት እነዚህ ክፍሎች እንዳልተገለጡ ማረጋገጥ አለበት፤ ካልተሸፈኑ ሶላቱ ተቀባይነት የለውም ፡፡





- ከኢማሙ ጋር የሚሰግደው አንድ ሰው ብቻ ከሆነ ያ ሰው በቀኝ ጎኑ መቆም አለበት። አንድ ሰው ከሌላው ጎን ሆኖ ሲሰግድ እንደሚቆመው ወደፊትም ወደኋላም ሳይል አብሮት መቆም አለበት።



## ሶላቶች በጥቅሉ

| ስም | ኢስላማዊ ፍርዱ | ጊዜው | ረከዓዎቹ | ማብራርያ |
|---|---|---|---|---|
| የጁሙዓ ሶላት | ግዴታ | በዙህር ሰአት | 2 | ጁሙዓ ጮክ ተብሎ በሚቀራ የሚሰገድ፤ በሦስት ወይም ከዚያም በላይ በሆኑ ወንዶች ሊከናወን የሚችል ነው። |
| የፀሃይ ግርዶሽ ሶላት | ማህበሰባዊ ግዴታ (ፈርዱን ኪፋያ) | ግርዶሹ ሲከሰት | 2 | በእያንዳንዱ ረከዓ ላይ ሁለት ሩኩዕ በማድረግ ጮክ ብሎ በሚቀራ ሶላት የሚከናወን ነው። |
| የዊትር ሶላት | እጅግ ጠንካራ ሱና | ከዒሻእ ሶላት በኋላ እስከ ፈጅር ድረስ | ከ 1-11 | ያም የሚከናወነው ወይ:<br>- አንዷት ረከዓ ብቻ፤<br>- ለመጨረሻ ተሸሁድ ብቻ የሚቀመጥበት ሶስት ተከታታይ ረከዓዎች፤ ወይም ደግሞ ሁለት ረከዓዎችን ይሰግድና ካሰላመተ በኋላ አንድ ረከዓ ይጨምራል፤<br>- ለመጨረሻ ተሸሁድ ብቻ በመቀመጥ አምስት ተከታታይ ረከዓዎች፤<br>- ለመጨረሻ ተሸሁድ ብቻ በመቀመጥ ሰባት ተከታታይ ረከዓዎች፤<br>- በስምንተኛው ለተሸሁድ በመቀመጥ ሳያሰላምት ለዘጠነኛው ተነስቶ የሚጨምርበት እናም ተሸሁድ ካለም በኋላ የሚያሰላምትበት፤<br>- ሁለት ሁለት እያደረገ በመስገድ አንዷት ረከዓ ብቻዋን በመስገድ ዊትር የሚያደርግበት ነው። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የፈጅር ሱና | እጅግ በጣም ጠንካራ ሱና | ከሱብሒ ሶላት በፊት | 2 | በ 1 ኛው ረከዓ ሱረቱል ካፊሩንን ይቀራል እና በ 2 ኛው ረከዓ ደግሞ ሱረቱል ኢኽላስን ይቀራል። |
| የዝሁር ሱና | ተወዳጅ ሱና | ከዝሁር በፊት አራት እና ከዝሁር በኋላ ሁለት ረከዓ | 4 እና 2 | ሁለት ሁለት ረከዓ በመክፈል |
| የመግሪብ ሱና | ተወዳጅ ሱና | ከመግሪብ በኋላ | 2 | በ 1 ኛው ረከዓ ሱረቱል ካፊሩንን ይቀራል እና በ 2 ኛው ረከዓ ደግሞ ሱረቱል ኢኽላስን ይቀራል። |
| የዒሻ ሱና | ተወዳጅ ሱና | ከዒሻ በኋላ | 2 | |
| ተራዊሕ | ተወዳጅ ሱና | ከዒሻ በኋላ እስከ ፈጅር ድረስ | ከ 2 - 10 | |
| ተሕየተል መስጅድ (መስጅድ ስለገባህ የሚሰገድ) | ግዴታ | መስጅድ በገባህ እና ከመቀመጥህ በፊት | 2 | |
| ሶላተ ዱሓ | ተወዳጅ ሱና | ፀሃይ ከፍ ካለችበት ጀምሮ እስከ ዙህር ድረስ | 2-8 | |
| ሶላተል ኢስቲኻራ (አሏህ የማማከር ሶላት) | ተወዳጅ ሱና | በየትኛውም ጊዜ | 2 | ከማሰላመቱ በፊት የኢስቲኻራ ዱዓውን ያደርጋል |

## የአስራ አንደኛው ትምህርት ማብራርያ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሶላተል ኢስቲስቃእ (ዝናብ እንዲመጣ የሚሰገድ ሶላት) | አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተወዳጅ ሱና ነው | ፀሃይ የዘንግን ያህል ከፍ ካለችበት ጊዜ ጀምሮ | 2 | በአንደኛው ረከዓ ልክ እንደ ዒድ ተክቢራ ተክቢረተል ኢሕራምን ጨምሮ ሰባት ጊዜ "አሏሁ አክበር" ይላል፤ በሁለተኛው ረከዓ ደግሞ አምስት ጊዜ "አሏሁ አክበር" ይላል። ይህ ግን የመሸጋገሪያን ተክቢራ አይጨምርም። |
| የዒድ ሶላት | ተወዳጅ ሱና | ፀሃይ የዘንግን ያህል ከፍ ካለችበት ጊዜ ጀምሮ | 2 ረከዓ እና 2 ኹጥባ | በአንደኛው ረከዓ ተክቢረተል ኢሕራምን ጨምሮ ሰባት ጊዜ "አሏሁ አክበር" ይላል፤ በሁለተኛው ረከዓ ደግሞ አምስት ጊዜ "አሏሁ አክበር" ይላል። ይህ ግን የመሸጋገሪያን ተክቢራ አይጨምርም። |

**ልቅ የሆነ የሱና ሶላት መስገድ የሚከለከልባቸው ጊዜያት**

1 .ጎህ ከቀደደ ጀምሮ ፀሃይ የዘንግን ያህል ከፍ እስከምትልበት ጊዜ ድረስ

2 .ከዓሱር ሶላት ጀምሮ ፀሃይዋ እስከትጠልቅ ድረስ

3 .የፀሃይ ከመሃል አናት መሆን ጀምሮ ዘንበል እስከትል ድረስ

## ስለሶላት ፈተና

1. ሶላት ስንት ቅድመ ሁኔታዎች አሉት? O 9 O 11 O 8
2. ሙስሊም ካልሆነ በስተቀር ማንም ስለማይሰግድ ‹እስልምናን› እንደሶላት ቅድመ ሁኔታ መቁጠር ስህተት ነው ( እውነት – ሃሰት )
3. 'የመለየት ዕድሜ' ማለት የጉልምስና ዕድሜ ማለት ነው። ( እውነት – ሃሰት )
4. 'ነጃሳ ነገሮችን ማስወገድ' አካልን ፣ ልብሶችን እና ቦታውን ሁሉ ይመለከታል (እውነት – ሃሰት)
5. የአሳማ ነጃሳነት: O ከባድ O መካከለኛ
6. ከፈሰሰ ገላን መታጠብ ግዴታ ስለሚያደርግ የዘር ፈሳሽ(መንይ) ርኩስ ነው። ( እውነት – ሃሰት)
7. ውሃን በመርጨት እና በማጠብ መካከል ምንም አይነት ልዩነት የለም ( እውነት – ሃሰት )
8. ከመታረዱ በፊት የሞተ እንስሳ ሁሉ ነጃሳ ነው ( እውነት – ሃሰት )
9. የውሻን ነጃሳ ለማስወገድ አፈርን በዘመናዊ ( እንደሳሙና) ባሉ ማፅጃዎች መጠቀም በቂ ነው። ( እውነት – ሃሰት )
10. መግባት መውጣት የሚያበዙ ለመጠባበቁ አስቸጋሪ የሆኑ እንስሳት ሲሆን ነው፤ ለምሳሌ: ድመት ለአንዳንዶቹ ጡሃራ ሁና ለሌሎች ግን ነጃሳ ልትሆን ትችላለች። ( እውነት – ሃሰት )
11. 'እስትንፋስ' የሌለው ነገር' ስንል "እስትንፋስ" የተባለው "ነፍስ" ለማለት ነው። ( እውነት – ሃሰት )
12. በደም ሥሮች ውስጥ የሚቆይ ደም… O ነጃሳ O ጡሃራ
13. የሶላት ማእዘናት ስንት ናቸው O 14 O 9 O 8
14. የመጀመሪያ ተክቢር ማለት እጆችን ከፍ ማድረግ ማለት ነው ( እውነት – ሃሰት )
15. አንድ ሰው ማእዘንን ረስቶ ከዘነጋ ፣ የመርሳት ሱጁድ መስገድ ብቻ ነው የሚጠበቅበት ( እውነት – ሃሰት )
16. ሶላት ስንት ግዴታዎች አሉት? O 8 O 14 O 9

17. አንድ ሰው "ሱብሓነ ረቢየል አዕላ" የሚለውን ቢያንስ አንድ ጊዜ ማለቱ ግዴታ መሆኑን ከማወቁም ጋ “ሱቡሕ ቁዱስ ረቡል መላኢከቲ ወሩሕ” ብሎ ቢናገር ሶላቱ ውድቅ ነው። (እውነት–ሃሰት)

18. የቀኝ እጅን መዳፍ በግራ እጅ ጀርባ እና አንጓው ላይ ማድረጉ የተደነገገ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

19. በለሊቱ ክፍለ ጊዜ በሚሰገዱ እና የዒድ ሶላቶችን በመሰሉ መሰብሰብ የተደነገገባቸው ሶላቶች ቁርአንን ጮክ ብሎ መቅራቱ የተደነገገ ነው። (እውነት – ሃሰት)

20. ሶላትን ውድቅ የሚያደርጉ ስንት ናቸው? O 8 O 9 O 14

21. ተወሩክ የሚባለውን አይነት አቀማመጥ የምንቀመጠው በ _______ *ተሸሁድ* ነው።

O1ኛው O መጨረሻው O ሁሉም

22. "ረበና ወለከል ሓምድ" ካልን በኋላ “ወሹክር” ጨምሮ *"ረበና ወለከል ሓምዱ ወሹክር"* ማለት…

O የተከለከለ O የተወደደ O የተፈቀደ

23. በሁለቱ ሱጁዶች መካከል: "ረቢግፊርሊ ወሊዋሊደየ" ማለት the 2 prostrations is…

O የተፈቀደ O የተከለከለ O የተወገዘ

24. በሱጁድ ጊዜ ክርንን ምድር ላይ ማድረግ …

O የተከለከለ O የተወደደ O የተወገዘ

25. የሱጁደ ሰህው(የመርሳት ሱጁድ) ምክንያቶቹ ብዛት ስንት ናቸው? O 2 O 3 O 4

26. ድርጊቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ጥርጣሬ ተፅእኖ የለውም፤ ጥርጣሬ የሚበዛበት ሲሆንም እንዲሁ ( እውነት – ሃሰት )

27. የፈጅር ሶላት ሱና በሌላው የግዴታ ሶላት ጋ ተቆራኝተው ከሚመጡ የሱና ሶላት አምሳዮቿ የምትለየው፡ በበላጭነቷ፣ በቀላልነቷ፣ ባሏት ልዩ ተመርጠው የሚቀሩ ሱራዎች፣ በጉዞም ላይ

ለመስገድ ያላት ተጠባቂነት፣ በቤት በሚሰገድበት አጋጣሚ ደግሞ ከተሰገደች በኋላ ጋደም ማለት የሚበረታታ በመሆኗ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

28. የተከታዮቹን ቁምነገሮች ኢስላማዊ ፍርድ አብራራ:

| ጉዳዩ | ፍርዱ |
|---|---|
| ዲኑን የሰደበ ሰው ሶላት | |
| በስካር ላይ ያለ ሰው ሶላት | |
| በአልዝሃይመር በሽታ የተጠቃ ሰው ሶላት | |
| የህፃን ልጅ ሶላት | |
| ረስቶ ዉዱእ ሳያደርግ ሰገደ | |
| ረስቶ በተነጀሰው ልብሱ ሰገደ | |
| የላም ሽንት | |
| የአሞራ ሽንት | |
| ተፋዎቹ ሳይሸፈኑ ሰገደ | |
| ረስቶ ጊዜው ሳይደርስ ሰገደ | |
| በፕሌን ውስጥ ሰገደ | |
| በጥቅሉ የጊዜውን ግዴታ በሚል ኒያ(ሃሳብ) ሰገደ | |
| ተቀምጦ ሰገደ | |
| ፋቲሓን መቅራት ዘነጋ | |
| (ዘግይቶ በመምጣቱ) ኢማሙን ያገኛቸው ሩኩዕ ላይ ነው | |
| ሶላት ላይ መጣደፍ | |
| ከሰገደ በኋላ ብዙ ጥርጣሬን ተጠራጠረ | |
| ተክቢረተል ኢሕራም ካደረገ በኋላ ስለውዱኡ ተጠራጠረ | |

## የአስራ አንደኛው ትምህርት ማብራርያ

| | |
|---|---|
| ረስቶ ሩኩዕ ጨመረ | |
| ተክቢረተል ኢሕራምን ተወው | |
| የመጀመርያውን ተሸሁድ ተወው | |
| የመጨረሻውን ተሸሁድ ተወው | |
| የሰገደው ሶስት ወይንስ አራት የሚለውን ተጠራጠረ | |
| ከሰገደ በኋላ ተጠራጠረ | |
| በሚሰግድበት ጊዜ ተጠራጠረ | |
| ሱጁደ ሰህው(የመርሳት ሱጁድ) ላይ ሳለ ተጠራጠረ | |
| በሚሰግድበት ጊዜ ረስቶ ተናገረ | |
| ሰግዶ ከጨረሰ በኋላ እንጅ ልብ ሳይለው ሃፍረተ ገላው ተገልጦ ሰገደ | |
| ወደ ሶላት ከመሄድ በፊት ገና ቤት ውስጥ ሳሉ ንፅህናን መጠበቅ | |
| መስጅድ ውስጥ መሻሻጥ | |
| መስጅድ ውስጥ የገንዘብ ምንዛሬ ማድረግ | |
| ኢማሙን የመጨረሻው ተሸሁድ ላይ አገኛቸው | |
| በሶላት ጊዜ በፊትለፊትህ ሱትራ(ከለላ ነገር) ማድረግ | |
| ቀላል እንቅስቃሴ ማድረግ | |
| ብዙ የሆነ እንቅስቃሴ ማድረግ | |
| ሶላትን በተጣደፈ መልኩ መስገድ | |
| በተሸሁድ ጊዜ ኢብራሂምይ የሆነውን ሶለዋት ማድረግ | |
| ሶላት ላይ ሳሉ መናገር | |
| ሶላት ላይ ሳሉ መንቀሳቀስ | |
| ፋቲሓን(አልሓምዱ ሊላህን) መቅራት ረሳ | |

| | |
|---|---|
| የጁሙዓህ ሶላት | |
| የዊትር ሶላት | |
| [መስጅድ ስለገባህ] ተሕየተል መስጅድ መስገድ | |

29. የቅድመ ሁኔታ(ሸርጥ)፣ ማእዘን(ሩክን)፣ ግዴታ(ዋጅብ) እና ሱና ልዩነቱን ጥቀስ፡

| ቅድመ ሁኔታ | ማእዘን | ግዴታ | ሱና |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

# አስራ ሁለተኛው ትምህርት

## የውዱእ ቅድመ ሁኔታዎች

**የውዱእ ቅድመ ሁኔታዎች አስር ናቸው:**

1- ኢስላም 2- የአእምሮ ጤነኛ መሆን 3- መለየት የሚችልበት እድሜ ላይ መሆን 4- ኒያ (ትክክለኛ የሆነ ሃሳብ) 5- ፍርዱን ይዞ መዝለቅ፤ እስኪጨርስ ድረስ ማቋረጧን ላያስብ 6- ውዱእን የሚያፈርሱ ነገራቶች መሃል ላይ አለማቋረጣቸው 7- ከዛ በፊት ኢስተንጃእ(ሃፍረተ ገላን በውሃ ማፅዳት) ወይም ኢስቲጅማር(ሃፍረተ ገላን በደረቅ ነገር ማፅዳት) ማድረግ 8- የውሃው ጡሃራ እና ሓላል መሆን 9- የውሃ ወደ ቆዳ ተደራሽ መሆን ሊያቅብ የሚችልን ነገር ማስወገድ 10- በየጊዜው ውዱእ የማፍረስ ችግር ላለበት ሰው የጊዜው መግባቱ

<u>የአንዳንዶቹ ቅድመ ሁኔታዎች ማብራርያ</u>

- “ፍርዱን ይዞ መዝለቅ፤ እስኪጨርስ ድረስ ማቋረጧን ላያስብ" ሲባል ዉዱእ የማድረግ ሃሳቡ እስከመጨረሻው ድረስ ዘላቂ ይሁን ማለት ነው።
- "ውዱእን የሚያፈርሱ ነገራቶች መሃል ላይ አለማቋረጣቸው" ሲባል እንደምሳሌ የግመል ስጋ እየበላ ውዱእ ማድረግ የለበትም፤ ወይም እየሸና፤ ይልቅ ውዱእ ማድረጉን ከመጀመሩ በፊት ውዱእን የሚያፈርሱ ነገራቶች አቋርጦ ሊሆን ይገባዋል።
- "ከዛ በፊት ኢስተንጃእ(ሃፍረተ ገላን በውሃ ማፅዳት) ወይም ኢስቲጅማር(ሃፍረተ ገላን በደረቅ ነገር ማፅዳት) ማድረግ" ሲባል ከዚህ ተነጥሎ የሚወጣው ውዱእ የሚያድረግበት ምክንያት በአየር ምክንያት(ፈስቶ) ከሆነ፣ በእንቅልፍ ምክንያት ከሆነ፣ የግመል ስጋ በልቶ ከሆነ ብቻ የተለየ ህግ ይኖረዋል።

- "የውሃው ጡሃራ እና ሓላል መሆን" ሲባል ነጃሳ በሆነ ወይም በተዘረፈ ውሃ መሆን የለበትም ለማለት ነው።
- "የውሃ ወደ ቆዳ ተደራሽ መሆን ሊያቅብ የሚችልን ነገር ማስወገድ" ሲባል እንደቡሆ እና የጠፍር ቀለም ያሉ ነገራቶችን ማስወገድ ለማለት ነው። ምክንያቱም እነኝህ ውሃ ወደሰውነት እንዳይደርስ ያግዳሉና።

## ሱነኑል ፊጥራ (ተፈጥሯዊ ሱናዎች)

ከተፈጥሯዊ ሱናዎች መካከል

1- **ግርዛት**: ለወንድ ልጅ ግዴታ ሲሆን ለሴት ልጅ ደግሞ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተወደደ ነው።

2-5- **ቀድሞ ቀመስን**(በአፍንጫና በላይኛው ከንፈር መካከል ያለውን የፂም ክፍል) **ማሳጠር፣ ጥፍር መቁረጥ፣ የብብትን ፀጉር መንቀል፣ በሃፍረተ ገላ ያለውን ፀጉር መላጨት፡** ከአነስ –ረድየሏሁ ዓንሁ- በተላለፈ ሓዲሥ እንዲህ ይላል: "ነብዩﷺ **ቀድሞ ቀመስን ለማሳጠር፣ ጥፍርን ለመቁረጥ፣ የብብትን ፀጉር ለመንቀል እና በሃፍረተ ገላ ያለውን ፀጉር ለመላጨት ከአርባ ለሊቶች በላይ እንዳንተወው የጊዜ ገደብ አደረጉልን።"**

6- **ፂምን ማፋፋት**: It ፂምን ማሳደግ ፍርዱ ግዴታ ሲሆን፤ መላጨቱ ከከባባድ ወንጀሎች መካከል አንዱ ነው።

7- **ሲዋክ:** ልዩ የሆነ አትክልት ዛፍ ተጠቅሞ ጥርስን ማፅዳት ነው። መሰረታዊ ፍርዱ የተወደደ በተለይም ደግሞ በተከታዮቹ አጋጣሚዎች፡ በውዱእ ጊዜ፣ በሶላት ጊዜ፣ ቤት በሚገባበት ጊዜ፣ ቁርአን በሚቀራበት ጊዜ፣ ከምኝታ በሚነሱበት ጊዜ፣ ለሞተ ሰው(ሌሎች ሊያፀዱለት) እና የአፍ ጠረን በሚቀይርበት ጊዜ ይበልጥ ጠንካራ ሱና ነው።

# አስራ ሶስተኛው ትምህርት

## የውዱእ ግዴታዎች

**የውዱእ ግዴታዎች ስድስት ናቸው:**

1- ፊትን ማጠብ፣ መጉመጥመጥንና መሰርነቅን(አፍንጫን በውሃ ማፅዳት) ያቀፈ ነው።

2- ክርንን ጨምሮ ሁለቱንም እጆች ማጠብ

3- ጆሮን ጨምሮ መላ ራስን ማበስ

4- ቁርጭምጭሚትን ጨምሮ ሁለቱንም እግሮችን ማጠብ

5- ቅደም ተከተላቸውን መጠበቅ

6- ማከታተል

ፊትን፣ ሁለት እጆችን፣ ሁለቱንም እግሮችን እንዲሁም መጉመጥመጥንና መሰርነቅም ሶስት ሶስት ጊዜ ማጠቡ የተወደደ ነው። የነኝህ ግዴታቸው ግን አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ነበር። ራስን ማበስ ግን ከነብዩﷺ የመጡ ሶሒሕ ሓዲሦች እንደሚጠቁሙን መደጋገሙ የተወደደ አይደለም።

### የተረጋገጠው ማከታትል

ውዱእ የሚያደርግ ሰው አንድን አካል ሲያጥብ ከበፊቱ ያጠበው አካል እስኪደርቅ ድረስ ባለማዘግየቱ የሚሆን ነው።

# አስራ አራተኛው ትምህርት

## ውዱእ የሚያፈርሱ ነገራቶች

**ውዱእ የሚያፈርሱ ነገራቶች ስድስት ናቸው:**

1- ከሁለቱ መፀዳጃዎች የወጣ ነገር ሁሉ

2- ከሌላ የሰውነት አካልም ቢሆን የወጣ ፀያፍ ነጃሳ ነገር ሁሉ

3- በእንቅልፍም ይሁን በሌላ ህሊናን መሳት

4- የፊትም ይሁን የኋላ ሃፍረተ ገላን ያለግርዶሽ መንካት

5- የግመል ስጋ መብላት 6- (አሏህ ይጠብቀንና) ከኢስላም መቀልበስ

**አሳሳቢ ጥቆማ:**

**ጀናዛን(ሟችን) ማጠብን በማስመልከት**: ትክክል የሚሆነው ውዱእን አይፈርስም የሚለው ነው። ይህን የሚያመላክት ማስረጃ የሌለ በመሆኑ የበርካቶቹ ዑለሞች ቃል ነው። ነገር ግን የአጣቢ እጅ ያለ ግርዶሽ የሟችን ብልት ከነካች ግን ውዱእ ማድረግ ግዴታ ይሆንበታል። ማድረግ የሚጠበቅበት ግን በግርዶሽ ተጠቅሞ ካልሆነ በቀር የሟችን ብልት አለመንካት ነው።

እንዲሁም **ሴትን ልጅ መንካት**[1] ከዑለሞች ጠንከር ያለውን ቃል በመመርኮዝ በስሜትም ይሁን ከስሜት ውጭ መሆኑ ልዩነትና ገደብ ሳይኖረው አንዳች ነገር እስካልወጣው ድረስ ውዱእ የሚያፈርስ አይደለም። ምክንያቱም ነብዩﷺ ባለቤታቸውን ስመው ውዱእ ሳያደርጉ ሰግደዋልና። "...ሴትንም የነካችሁ ብትኾኑ..." (አልማኢዳህ 6) የሚለው ደግሞ የተፈለገበት ይበልጥ ለእውነት ቅርብ በሆነው የዑለሞች ቃል መሰረት ፆታዊ ግንኙነት ነው። ይህም የነኢብኑ ዓባስ እንዲሁም ሌሎች ቀደምትም ኋላ ከመጡ ታላላቅ ተተኪዎችም የመረጡት ቃል ነው።

[1] ልብ በል፡ ከሴት ልጅ ጋ ወይም ከተቃራኒ ፆታ ጋ ያለ መስተጋብር **መገደቡ**ም ሆነ ተቃራኒ ፆታን ሰላም ማለት **የማይቻለው** ተቃራኒ ፆታን ሰላም ማለት ዉዱእን ስለሚያፈርስ አይደለም። [ተርጓሚው]

## ውዱእ ከሚያፈርሱት የከፊሎቹ ማብራርያ

"ከሁለቱ መፀዳጃዎች የወጣ ነገር ሁሉ" ሲባል በልቁ ነው፤ እንደ ሽንት፣ ሰገራ፣ መንይ (የዘር ፈሳሽ)፣ መዝይ(ጠረን የለሹ ነጭ ፈሳሽ)፣ ወድይ(ከሽንት በኋላ የሚወጣው ፈሳሽ አይነት)፣ ፈስ፣ ጠጠርም ቢሆን፣ ደም፣ ትል ነገር፣ የወር አበባ ደም እና የወሊድ ደም ሁሉ ማለት ነው።

"ከሌላ የሰውነት አካልም ቢሆን የወጣ ፀያፍ ነጃሳ ነገር ሁሉ" ያለውን በማስመልከት ይበልጥ ሚዛን የሚደፋው የዑለሞች ቃል ሽንትና ሰገራ ነክ ነገር ካልሆነ በቀር ውዱእ አያፈርስም የሚለው ነው።

"በእንቅልፍም ይሁን በሌላ ህሊናን መሳት" ሲባል እንቅልፍ በመሰረቱ ውዱእ የሚያፈርስ ሆኖ አይደለም። ይሁን እንጅ አየር(ፈስ) ለማውጣ አመች ነው። በመሆኑም ከሱ አንዳች ነገር እንዳልወጣ እርግጠኛ መሆን የሚችልበት ሁኔታ ላይ ከነበረ ውዱእ አፍርሷል ሊባል አይችልም።

"የፊትም ይሁን የኋላ ሃፍረተ ገላን ያለግርዶሽ መንካት": የሚለውን በማስመልከት አሏህ ይዘንለትና ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ በመንካት ብቻ ውዱእ ማድረጉ የተወደደ እንጅ ግዴታ እንዳልሆነ ሚዛን የሚደፋ አቋም መሆኑን አብራርተዋል።

## የውዱእ አደራረግ ሁኔታ ስእላዊ ማጠቃለያ

-ውዱእ ለማድረግ ሲፈልግ “ቢስሚላህ” ይበል።

- ከዚያም በውሃ አድርጎ ሁለት እጆቹን ሶስቴ ያጥባል

- ከዚያም በቀኝ እጁ ውሃ ዘግኖ ለመጉመጥመጥ ወደ አፉ በማስገባት በኮሽኮሸው ደግሞ ወደ አፍንጫው በመሳብ ከዚያም ደግሞ የግራ እጅ ጠቋሚ ጣቱን ከአውራ ጣቱ ጋ አድርጎ ከአፍንጫው እንዲወጣ ያደርገዋል፤ ይህንንም ሶስት ጊዜ ይደጋግመው።

- ከዚያም ፊቱን ሶስቴ ያጥበዋል፤ ፊት ሲባል ገደቡ ቁመቱ ከተለምዶው የራስ ፀጉር መብቀያ ወደታች እስከ አገጭና ፂም ጫፍና ጠርዝ ድረስ ሲሆን ወደ ጎን ደግሞ በሁለቱ ጆሮዎች መካከል ነው።

- ከዚያም ከቀኝ እጁ ጀምሮ ግራ እጁን በማስከተል ሁለት እጆቹን ክርኑንም ጨምሮ ሶስቴ ያጠባቸዋል።

- ከዚያም ከግንባሩ ጀምሮ ማጅራቱ ድረስ አብሶ ድጋሚ በመመለስ አኳኋን ራሱን ያብሳል።

- ከዚያም ሁለቱን ጠቋሚ ጣቶቹን ጆሮው ውስጥ በመከተት ጆሮውን ያብሳል።

- ከዚያም እግሮቹን ከቁርጭምጭሚቱ ጋ ሶስቴ ያጥባል።








-ውዱእ ማደረጉን ሲያጠናቅቅ እንዲህ ይላል *"አሽሃዱ አን ላ ኢላሃ ኢለሏህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለሁ ወአሽሃዱ አነ ሙሓመደን ዓብዱሁ ወረሱሉህ"* [2] በቲርሚዝይ ዘገባ ደግሞ እንዲህ የሚል ጭማሪ ይገኛል *"አሏሁመ ጅዓልኒ ሚነተዋቢነ ወጅዓልኒ ሚነል ሙተጠሂሪን"*[3]

## ከተደነገገው ልክ በላይ መጨመር ያለው ፍርድ

በውዱእ ጊዜ ከተደነገገው በላይ መጨመር አይፈቀድም። ከሶስት ጊዜ በላይ ማጠብን ይመስል፣ ከክርን በላይ ትከሻ ድረስ ማጠብን ይመስል፣ ወይም ከቁርጭምጭሚት በላይ ባትን ማጠብ ይመስል፣ወይም ራስን ሲያብሱ ማጅራትን ጨምሮ ማበስ ይመስል።





[2] ትርጉሙም "ከአሏህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አለመኖሩን እና ተጋሪ የሌለው ብቸኛ መሆኑን እመሰክራለሁ፤ እንዲሁም ሙሓመድም ባርያውና መልዕክተኛው መሆናቸውንም እመሰክራለሁ"

[3] ትርጉሙም፡ አሏህ ሆይ! ወዳንተ ከሚመለሱት አድርገኝ፤ ከሚጥራሩትም አድርገኝ።

## ከንፅህና ጋ ተያያዥ የሆኑ አንዳንድ ነጥቦች

### የመጀመርያው: ጡሃራ (መጥራራት)

### 'ተየሙም'

አካልን ወይም ከፊሉን ለመታጠብ የሚያስፈልገው ሊገኝ ባለመቻሉ ወይንም ቢኖርም እንኳ መጠቀሙ የሚያሰጋ በመሆኑ ውሃን መተካት ነው። በመሆኑም አፈር ውሃን የሚተካ ይሆናል ማለት ነው።

#### የተየሙም ምንነት

ተየሙምን በማሰብ "ቢስሚላህ" ይላል። ከዚያም ንፁህ የሆነው ምድር ላይ እጁን ያሳርፍና በዚያው በመዳፎቹ የእያንዳንዱን መዳፍ ጀርባ እና ፊቱን ያብሳል።



እጁን መሬት ላይ ሲያሳርፍ ጣቶቹን ከፊትፊት ማድረጉ የተደነገገ አይደለም፤ የመዳፎቹን ጀርባ ሲያብስም ጣቶቹን መፈልፈል አይጠበቅበትም።





**ግዴታ የሆነው ገላን መታጠብ ሁኔታው**

መታጠብንና ከጀናባ መጥራትን በልቡ ሊያስብ ይገባዋል፤ ከዚያም "ቢስሚላህ" ይበልና በስስም ይሁን በብዙም ፀጉር ስር ያለን ሁሉ በማዳረስ በመጉመጥመጥ እንዲሁም በመሰርነቅ መላ ሰውነቱን ይታጠብ።

**በትጥበት ጊዜ ተወዳጅ የሆኑ ነገሮች**

በመጀመርያ ሃፍረተ ገላውን መታጠብ፤ ከዚያም ሁለት እጆቹን፤ ከዚያም ለሶላት እንደሚያደርገው ውዱእ ያድርግ፤ የፀጉሮቹን ስሮች ማዳረስ፤ ከዚያም በቀኝ በኩል አጥቦ በግራ በኩል ይታጠብና ከዚያም ሁለት እግሮቹን ይታጠባል።

**ትጥበትን ግድ የሚያደርጉ ነገሮች**

1- ጀናባ: ወይ በግንኙነትም ይሁን በሌላ ምክንያት የዘር ፈሳሽ በመፍሰሱ አልያም ደግሞ የሁለቱ ጥንዶች ብልት ስለተነካኩ ብቻም ይሆናል።

2- የወር አበባ ደም ወይም የወሊድ ደም ስለፈሰሰ

3- ሸሂድ (ለዲነል ኢስላም ልቅና የተሰዋ) ካልሆነ በቀር በሌላ ከሞተ

4- ካፊር እስልምናን ከተቀበለ

## በሁለት ካልሲዎች(ኹፎች) ላይ የማበስ ቅድመ ሁኔታዎች

ኹፎቹ ወይም ካልሲዎቹ ጡሃራ መሆን አለባቸው።

ኹፎቹን ሲያጠልቃቸው በጡሃራ (እግሮቹ) መሆን አለበት፤ ማለትም፡ ውዱእ ሲያደርግ ሁለት እግሮቹን ካጠባቸው በኋላ (ያጠለቃቸው) መሆን አለበት።

በካልሲዎቹ ላይ ማበሱ ለትንንሽ ርክሰት (ለውዱእ ማፍረስ) እንጅ በጀናባ ወይም ገላን መታጠብ ግድ ለሚያስብል ነገር መሆን የለበትም።

ካልሲዎቹ አብዛኛውን የእግሩን ክፍል የሚሸፍኑ መሆን አለባቸው።

ማበሱ በሸሪዓው በተገደበው የጊዜ ልኬት ገደብ ውስጥ መሆን ይኖርበታል። ይህም መንገደኛ ላልሆነ አንድ ቀን ከለሊት (24 ሰዓት) ሲሆን፤ ለመንገደኛ ደግሞ ሶስት ቀን ከለሊቱ (72 ሰአታት) ያህል ነው። ሰአት ቆጠራው የሚጀምረው ውዱእን አድርጎ ካጠለቃቸው በኋላ ውዱእን አፍርሶ ለአዲሱ ውዱእ መጀመርያ ካበሰበት ሰአት ነው።

## በኹፎቹ(ካልሲዎቹ) ላይ የሚታበስበት አኳኋን?

እጁን ከእግሩ ጣርዞች ጀምሮ እስከባቱ ድረስ ማሳለፍ ነው። ማለትም የሚታበሰው ክፍል የኹፉ (የካልሲው) የላይኛው ክፍል ነው ለማለት ነው። ስለዚህም እጆቹን ከእግሮቹ ጣቶች እስከ ባቱ ድረስ ብቻ ያንሸራትታል። ይህ ማበስ በሁለቱም እጆቹ አንድ ላይ ከሁለቱም እግሮቹ ላይ ነው የሚሆነው። ማለትም ቀኝ እጁ እግራ እግሩን የምታብስ ስትሆን በዛው ቅፅበት የግራ እጁም የግራ እግሩን የምታብስ ትሆናለች ማለት ነው። ልክ ሁለቱን ጆሮዎቻችንን በምናብስበት መልኩ ማለት ነው። ምክንያቱም ከሱና የምንረዳው ጉልሁ መልዕክት ይህንኑ ነውና።

### ከማበስ ጋ ተያያዥነት ያላቸው ቁምነገሮች

1- የማበስ ጊዜው ከተቋጨ አልያም የታበሰበት ከወለቀ ጡሃራው እንዳለ ነው፤ ውዱኡ አልፈረሰም።

2- በቀዳዳ ኹፍ (ካልሲም) ላይ ማበስ ይቻላል፤ እንዲሁም ባለው ቀዳዳ ምክንያትም ይሁን በስስነቱ ቆዳን የሚያሳይም (እንዲሁ ለማበስ መጠቀም ይቻላል)።

## የመፀዳዳት ስነ-ስርዓቶች

**ተወዳጅ የሆኑ:**

-ወደ መፀዳጃ ቤቱ ሲገባ ግራ እግሩን በማስቀደም እንዲህ ማለቱ "***ቢስሚላሂ አሏሁመ ኢኒ አዑዙቢከ ሚነል ኹቡሢ ወልኸባኢሥ***". (ትርጉም፡ በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፤ አሏህ ሆይ! ከወንድም ሆነ ከሴት አጋንንት ባንተው እጠበቃለሁ።)

-ሲወጣ ደግሞ ቀኝ እግሩን በማስቀደም "***ቁፍራነከ***" ማለቱ (ትርጉም፡ መሃርታህን ጌታየ)

**ግዴታው**፡ በአጥር ነገር አልያም በሌላ መከለል፤ ገላጣ መሬት ላይ ከሆነ ደግሞ ከሰው ራቅ ማለቱ

**የማይፈቀድለት:**

-በመንገድ ላይ፣ ሰዎች በሚቀማመጡበት ቦታ፣ በምታመርት ዛፍ ስር፣ ወይም ሰዎችን ሊያስቸግር በሚችል ቦታ እንዲሁም በረጋ ውኋ ላይ መፀዳዳት፤

-በሚፀዳዳበት ጊዜ ጀርባውን አልያም ፊቱን ለቂብላ መስጠት፤

- ብልቱን በቀኝ እጁ መንካት፤

-አሏህን ማውሳት፤

ተፀዳድቶ እንዳጠናቀቀ ወይ በውኋ ያጥበዋል ወይም ደግሞ በደረቅ ነገር ያፀዳዋል(ኢስቲጅማር)፤

**የኢስቲጅማር (በደረቅ ነገር የማፅዳት) ቅድመ መስፈርቶች:**

- ሶስት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ መጥረግ፤ ይህ ሲባል ግን በአንድ ማፅጃ ተመሳሳይ ቦታ (ደጋግሞ) መጥረግ የለበትም።

- ማፅጃው በራሱ ፅዱ መሆን አለበት። ይህም ድንጋዩ ወይም መሃረቡ መልሶ ደረቅ በመሆኑ ሊታወቅ ይችላል።

- ኢስቲጃምር የሚደረገው በነጃሳ ነገር፣ እንደምግብ ባለ ክብር ነገር፣ ወይም በአጥንት እንዲሁም በእንስሳ ኩስ መሆን የለበትም።

የሽንቱ ፍንጣሪ በልብሱ ላይ አልያም በሰውነቱ ላይ እንደማያርፍ እንዲሁም ሃፍረተ ገላው ለእይታ እንደማይጋለጥ ለተማመነ ቆሞ መሽናት ይፈቀድለታል፤ “… **ነብዩ ﷺ ወደ ሰዎች መፀዳጃ ቦታ መጥተው ቆመው (ሽንታቸውን) ሲፀዳዱ አይቻቸዋለሁ።**” (ቡኻሪይ እና ሙስሊም)

## ከንፅህና ጋ የተያያዙ ጥያቄዎች

1. ውዱእ ስንት ቅድመ መስፈርቶች አሉት? O 9 O 10 O 8

2. ውዱእ የማድረግ ግዴታዎች: Oአራቱ የሰውነት ክፍሎች O ከቅደም ተከተልና ማከታተልን በተመለከተ ያስቀደምነው።

3. ውዱእን የሚያፈርሱት ነገራቶች ብዛት ስንት ነው? O 6 O 5 O 8

4. ከሚከተሉት ውዱእን የሚያፈርሰው የትኛው ነው:

O የግመል ስጋ O የሚዳቋ ስጋ O የሆድ ድምፅ O አየር(ፈስ)

O እንቅልፍ O ሬሳ ማጠብ O ሴትን መንካት

5. የተየሙምን ሁኔታ አብራራ:

………………………………………………………………………

………………………………………………………………………

………………………………………………………………………

6. የትጥበትን አኳኋን አብራራ:

………………………………………………………………………

………………………………………………………………………

………………………………………………………………………

7. የተከታዮቹን ነጥቦች ኢስላመዊ ፍርድ አብራራ:

| ነጥቡ / ጉዳዩ | ኢስላማዊ ፍርዱ |
|---|---|
| ኒያን በቃል ማለት | |
| ውዱኡን ሲያደርግ ኒያው(ሃሳቡ) ለአንድ ሶላት ብቻ ነበር፤ ነገር ግን በዚያው ከዛ(ከአንዱ) በላይ ሶላቶችን ሰገደበት | |
| ውዱኡን ሲያደርግ ኒያው ቁርአን ለመቅራት ነበር፤ ግን ሰገደበት | |
| ውዱኡን በሚያደርግበት ሰአት ውዱእ የማድረጉ ኒያው (ሃሳቡ) ተቋረጠ | |
| ውዱኡን ካደረገ በኋላ ውዱእ የማድረጉ ኒያው (ሃሳቡ) ተቋረጠ | |
| ውዱእ አደረገና በባቱ ላይ ሊጥ ተመለከተ | |
| የግመል ስጋ እየበላ ውዱእ አደረገ | |
| በተሰረቀ ዉኋ ውዱእ አደረገ | |
| ኢስቲንጃእ ወይም ኢስቲጅማር ከማድረጉ በፊት ውዱእ አደረገ | |
| ለጆሮዎቹ እንደአዲስ ዉኋ ዘገነ | |
| ጭንቅላትን ሶስት ጊዜ ማበስ | |
| አንዳድ ጊዜ ብቻ እያጠቡ ውዱእ ማድረግ | |
| ዉዱእ በሚያደርጉበት ጊዜ ሶስት ሶስት ጊዜ ማድረግ | |
| ውዱእ በሚያደርጉበት ጊዜ ሁለት መዳፎችን መታጠብ | |
| ፂምን እየፈለፈሉ ማጠብ | |
| በውዱእ ጊዜ እያሹ መታጠብ | |
| መታጠብ ያለበትን በማበስ ብቻ መብቃቃት | |
| ፀጉርን መታጠብ | |
| መዳፎችን በውኋ ቋቱ ውስጥ ማስገባት | |

## የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

| | |
|---|---|
| በውዱእ ጊዜ ቀኝን ማስቀደም | |
| የውዱእ አካላትን ከሶስት ጊዜ በላይ ማጠብ | |
| ባትን ማጠብ | |
| ከዋና በኋላ ቀጥታ ሰገደ | |
| ገላውን ከታጠበ በኋላ ውዱእ ሳያደርግ ሰገደ | |

## የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

### ሁለተኛው : ዘካ

ሁለት አይነት ነው:

#### ዘካቱል በደን

ይህ ዘካተል ፊጥር የምንለው ነው። በእያንዳንዱ ሙስሊም ትልቅም ይሁን ትንሽ፤ ወንድም ይሁን ሴት፤ ጨዋም ይሁን ባርያ ላይ ሁሉ ግዴታ ነች።

#### ዘካቱል ማል

ይህች ከእስልምና ማእዘናት ሶስተኛዋ የሆነችዋ የዘካ አይነት ነች። ይህች በእያንዳንዱ ጨዋ ሆኖ የሃብት መጠኑ በሸሪዓ የተወሰነውን የኒሷብ ልኬት የደረሰ ሁሉ ላይ ግዴታ ነች። ከምድሪቱ ለወጣ፤ እንዲሁም ኒሷቡ እንደሚፋፉ እና እንደ የንግድ ትርፍ ላለው መሰረቱን ይዞ ለሚያድግ አይነቱ አመት ለመሙላቱ ጊዜው የሚቆጠርለት በመሰረቱ ላይ ተንተርሶ ለሆነው ካልሆነ በቀር፤ ይህ የኒሷብ ልኬት መጠኑ ደርሶም ሙሉ አንድ አመት እስካልሞላው ድረስ በሃብቱ ላይ የዘካ ግዴታ የለበትም።

ይህም አራት አይነት ነው:

##### የንግድ ቁስ:

ለሽያጭና ለግዥ የተጋለጠ ሁሉ

##### ከመሬት የሚወጣ

ፍራፍሬና ቡቃያ

##### የደለበች የቤት እንስሳ

ለሙሉ አመት ወይም አመት ሊባል በሚችል በነፃነት የሚንከባከቧት፤ የቤት እንስሳ (በሂሙቱል አንዓም) ሲባል ግመል፣ ከብት እንዲሁም በግና ፍየልን ማለታችን ነው።

##### ወርቅና ብር

ወርቅና ብር(ሲልቨር) እንዲሁም ሌላም እንደነሱ ሆኖ የግብይት መሳርያ የሆነ፤ የወርቅ ኒሷብ 20 ሚሥቃል[85 ግራም] ሲሆን የ(ሲልቨር)ብር ኒሷብ 200 ዲርሃም [595 ግራም] ነው።

## የዘካ ገንዘብ ባለቤቶች:

1. **ድሆች /ፋቃራእ:** እነኝህ ማለት አንዳችም ነገር የሌላቸው፤ ቢያገኙም ከሚያስፈልጋቸው ጥቂቱን እንጅ የማያገኙ ችግረኞች ናቸው።

2. **ሚስኪኖች** : እነኝህ ማለት ከሚያስፈልጋቸው አብዛኛውን ወይም ግማሹን የሚያገኙ ናቸው። ለምሳሌ፡ አጠቃላይ አመታዊ ፍጆታ (ተደምሮ ለግለሰብ) 12000 ነው ብለን ብናስብ ድሃ ማለት እሱ ዘንድ ሊኖር የሚችለው (ቢደመር) 6000 ወይንም ከዚያ በታች የሆነ ማለት ሲሆን ሚስኪን ማለት ደግሞ እሱ ዘንድ ሊኖር የሚችለው 6000 ወይንም ከዚያ በላይ ነገር ግን 12000 የማይሞላ ማለት ነው። ይህም (አመት ያልነው) ሚስኪንንም ሆነ ድሃን የምንሰጠው በአመት አንድጊዜ ስለሆነ ነው፤ ዘካም ግዴታ የሚሆነው በአመት አንዴ ነውና።

3. **የዘካ ሰራተኞች:** እነዚህም ሰብሳቢዎቹ፣ ጥበቃዎቹ፣ በማከፋፈሉ የተመደቡት፣ የሙስሊሞቹ መሪ በሾመላቸው ሹም ይከናወናል። እነኝህ ስለድህነታቸው መገለፅ እንደቅድመ መስፈርት አይሆንም ይልቅ ሃብታሞች እንኳ ቢሆኑም የራሳቸው ድርሻ አላቸው።

4. **ልቦናቸው የተዘነበሉትን:** እስልምና እንደሚቀበሉ ተስፋ የተጣለባቸው ወይም ሸራቸውን ለማቀብ ወይም ደግሞ ኢማንን ለማጠናከር።

5. **ጫንቃዎችን ለማስለቀቅ:** እነኝህም:

ሀ. ራሱን ከአለቃው በገንዘቡ ነፃ የሚያወጣ ሙስሊም

ለ. ሙስሊም ባርያን ነፃ ለማውጣት

ሐ. ሙስሊም እስረኛን ነፃ ለማውጣት

የባርያው አለቃ አንድን ባርያ ነፃ ቢለቀውና ዘካ ነው ብሎ ቢያስብ አይፈቀድለትም።

6. **እዳ ላይ ያሉ:**

ሀ. በሰዎች መካከል ለማሸማገል ብሎ እዳ ውስጥ የገባን

ለ. ለራሱ ሲል እዳ ውስጥ የገባ

አንድ ድሃን ያበደረ ሰው ዘካን አስቦ እዳውን ቢምረው የዘካ ግዴታውን ተወጣ ማለት አይደለም።

7. **<u>በአሏህ መንገድ ለሚታገል:</u>** ለዘማቾችም ይሁን ለሚያስፈልጋቸው ትጥቅ ማሟላትንም ያካትታል።

8. ***<u>ለመንገደኛም</u>***: ስንቁ የተቋረጠበት ለሆነ መንገደኛ ወደ ሃገሩ ሊያደርሰው የሚያስችለውን ያክል ይሰጠዋል።

ከነኚህ ከተዘረዘሩት ለአንዳቸው ብቻ በመስጠት መብቃቃትም ይቻላል። ዘካ ለሃብታምም ሆነ መስራት ለሚችል ብርቱ አይፈቀድም፤ እንዲሁም ለነብዩﷺ ቤተሰቦች ማለትም ለሃሺም ዘር እና ለነርሱው ባርያዎችም የተፈቀደች አይደለችም፤ የዘካ ገንዘቡን በሚያወጣበት ጊዜ በሱ ስር ለሆኑትና ጣጣቸውን ሊሸፍንላቸው ግዴታ የተጣለበትን ሰዎች ቢሰጥም አይፈቀድለትም፤ ለካፊርም የተፈቀደች አይደለችም። ተጨማሪ በሆነ ሶደቃ ግን ለነኚህም ሆነ ለሌሎችም መስጠት ይፈቀዳል፤ ነገር ግን ይበልጥ ጠቀሜታዋ ዘርፈ ብዙ በግ=ሆነ ቁጥር ይበልጥ የተሟላች ነች።

## አስፈላጊ ገለፃዎች

-***ቢንት መኻድ*** እድሜዋ ከአንድ አመት በላይ የሆናት ግመል ነች፤ በዚህ ስያሜ ልተራ የቻለችበትም ምክንያትም ከእናቷ ጫና አንፃር ነው።

- ***ቢንት ለቡን*** ሁለት አመቷ የሞላት ግመል ነች፤ በዚህ ስያሜ የተሰየመችውም እናቷ ባለወተት ስለሆነች ነው።

- ***አል-ሒቃህ*** ሶስት አመት የሞላት ግመል ነች፤ በዚህ የተሰየመችውም የግመል ኮረዳ ስለሆነች ነው።

-***አል-ጀዘዓህ*** እድሜዋ ከአራት አመት በላይ የሆናት ነች፤ በዚህም የተሰየመችው የፊት ጥርሷ የምትሰበረውና የምትወድቀው በዚህ እድሜዋ ስለሆነ ነው።

-***አት-ተቢዕ*** ወይንም ***አት -ተቢዓህ*** እድሜዋ አንድ አመት የሞላት ጥጃ ነች።

- ***አል-ሙሲንናህ*** እድሜዋ ሁለት አመት የሞላት ጊደር ነች።

## የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

**የዘካ መጠን**

| የገንዘቡ አይነት | (ዘካ እንዲወጣበት) አመት መሙላቱ | ኒሷብ (የገንዘቡ ለዘካ ብቁነት ሸሪዓዊ ልኬት) | የዘካው መጠን |
|---|---|---|---|
| የደለበች የቤት እንስሳ (በሂመቱል አንዓም) [ግመል፣ ከብት፣ በግና ፍየል] | ቅድመ መስፈርት ነው | ቀጣዩን ሰንጠረዥ ተመልከት | ቀጣዩን ሰንጠረዥ ተመልከት |
| ከመሬት ከሚወጣ | ቅድመ መስፈርት አይደለም | 300 ሷዕ (≈900 ኪሎ ግራም ገደማ) | ከዝናብ ወይም ከተፈጥሮ ምንጭ በተገኘ ውኋ አሊያም መሬቱ እርጥበታማ በመሆኑ ከበለፀገ 1/10 |
| | | | በመስኖ ውኃ ከበለፀገ 1/20 |
| | | | በሁለቱም መንገድ ከበለፀገ ሩብ ቀረሽ ለአንድ አስረኛ ይለግሳል |
| ከመገበያያ ገንዘብ | ቅድመ መስፈርት ይሆናል | 85ግራም ወርቅ ወይም 595 ግራም ሲልቨር/ብር | የአንድ አስረኛ ሩብ |
| ከግብይት እቃዎች | ቅድመ መስፈርት ይሆናል | ከወርቅና ከብር ለድሆቹ ይበልጥ አመች በሆነው በመመርኮዝ ይወሰናል | የአንድ አስረኛ ሩቡ |

***የሳኢማ (ለመደለብ የተመደበች በግ፣ ከብት፣ ግመል ፣ ፍየል) ኒሷብ እና የዘካው መጠን***

## የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

| ከብት እና ጎሽ | | | ባለ አንድም ባለሁለትም ሻኛ ግመል | | | በግና ፍየል | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዘካ የሚወጣው | መጠኑ | | ዘካ የሚወጣው | መጠኑ | | ዘካ የሚወጣው | መጠኑ | |
| | ከ | እስከ | | ከ | እስከ | | ከ | እስከ |
| ተቢዕ (አመት የሞላው ወንድ ወይም ሴት ከብት /ጥጃ) | 30 | 39 | 1 በግ/ፍየል | 5 | 9 | 1 በግ/ፍየል | 40 | 120 |
| | | | 2 በግ/ፍየል | 10 | 14 | | | |
| ሙሲና (ሁለተኛ አመቷ የሆነች ጊደር) | 40 | 59 | 3 በግ/ፍየል | 15 | 19 | 2 በግ/ፍየል | 121 | 200 |
| | | | 4 በግ/ፍየል | 20 | 24 | | | |
| 2 ተቢዓ /ጥጃ | 60 | 69 | 1 | 25 | 35 | 3 በግ/ፍየል | 201 | 300 |
| | | | 1 ቢንተ ለቡን | 36 | 45 | ከዚያ በኃላ ለ 100 በግ/ፍየል 1 በግ/ፍየል | | |
| ለየ 30ው, 1 ጥጃ<br>ለየ 40ው, 1 ጊደር | | | ሒቃህ | 46 | 60 | ተከታዮቹ እንደ ዘካ ሊሆኑ አይወሰዱም: ከሲታ፣ አራስ ወይም ለመውለድ የቀረበች፣ ኮርማ እና በጣም ምርጥ የሆነ እንዲሁ ነውረኛ ገንዘብ ለዘካ አይወሰዱም | | |
| | | | ጀዝዓህ | 61 | 75 | | | |
| | | | 2 ቢንተ ለቡን | 76 | 90 | | | |
| | | | 2 ሒቃህ | 91 | 120 | | | |
| | | | 3 ቢንተ ለቡን | 121 | 129 | | | |
| | | | ለየ 40, 1 ቢንተ ለቡን. ለየ 50, 1 ሒቃህ | | | | | |

# የዘካ ፈተና

1. ሃብት በ ...... የጊዜ አቆጣጠር ሙሉ አንድ አመት እስካልሞላው ድረስ የዘካ ግዴታ የለም።

O ዓመተ ሂጅራ(በኢስላማዊ) O ዓመተ ልደት(እኤአ/እሐአ) O ልዩነት የለውም

2. አመት መሙላት ለ ........ የገንዘብ አይነት ዘካ መውጣት ቅድመ መስፈርት አይሆንም

O ማእድን O ከመሬት ለሚወጣ (ቡቃያ) O ሁሉም መልስ ይሆናል

3. የገንዘቡ ለዘካ ብቁነት ሸሪዓዊ ልኬት በወርቅ ...

O 85 ግራም O 595 ግራም O 95 ግራም

4. የገንዘቡ ለዘካ ብቁነት ሸሪዓዊ ልኬት በብር (ሲልቨር) ...

O 200 ዲርሃም O 595 ግራም O ሁሉም መልስ ይሆናል

5. *በሂመቱል አንዓም* ሲባል ግመል፣ ከብት፣ ጎሽ እንዲሁም በግና ፍየልን ያጠቃልላል

( እውነት – ሃሰት )

6. ፍራፍሬዎች የዘካ ግዴታ የለባቸውም ( እውነት – ሃሰት )

7. *ሳኢማ ማለት*... O ዋጋዋ ውድ የሆነች O ለአመትና ከዚያም በላይ የደለበች

8. በተፈቀደ የምትታገድ ሲባል ... O ጥሩ ጥሩውን የምትቀለብ O ባላባት የሌላት

9. ሚስኪኖች ከተወሱ ድሆችም በስሩ ይጠቃለላሉ ( እውነት – ሃሰት )

10. ድሃ ሲሰጥ ሊሰጥ የሚገባው ለ ...... የሚበቃውን ያክል ነው

O ለ 1 አመት O ለ 1 ወር

11. የዘካ ሰራተኞች ማለት ...

O በዘካው ዙርያ የሚሰሩት ሰራተኞች በሙሉ O አስተዳዳሪው የሾማቸው ብቻ

12. የተከታዮቹን ዘካ መጠን ቀምረህ አስቀምጥ ፡

| የገንዘቡ አይነት | የዘካው መጠን | ግዴታ የማይኖርበት ትራፊ ገንዘብ ካለ (ወቅስ) |
|---|---|---|
| 100 ዲርሃም (የብር ሳንቲም) | | |
| 300 ዲናር (የወርቅ ሳንቲም) | | |
| 400 ዲርሃም (የብር ሳንቲም) | | |
| 80 ግራም ወርቅ | | |
| 500 ግራም ብር(ሲልቨር) | | |
| 30 በጎች/ፍየሎች | | |
| 60 በጎች/ፍየሎች | | |
| 565 በጎች/ፍየሎች | | |
| 4 ግመሎች | | |
| 17 ግመሎች | | |
| 449 ግመሎች | | |
| 30 ከብቶች | | |
| 49 ከብቶች | | |
| 77 ከብቶች | | |
| 99 ከብቶች | | |
| 20 ሚልዮን ሪያል | | |
| 40 ሪያል | | |
| 45679 ሪያል | | |
| 255 ሷዕ ስንዴ | | |

13. እስልምና ይቀበላል ተብሎ ተስፋ የማይደረግበት ካፊርም “ልቦናቸው ለተዘነበሉ” በተባሉት ይካተታል ( እውነት – ሃሰት )

14. የባርነት አለቃው ከባርነቱ ነፃ ያለው ባርያ ከዘካ ይሰጠዋል ( እውነት – ሃሰት )

15. አንድ ባለሃብት ያበደረውን ገንዘብ ከ(ዘካ ከሚገባው) ተበዳሪው ገንዘቡን ጠየቀና ከፊሉን እዳውን እንደተወለትና ያም ዘካ መሆኑን አሳወቀው፤ ይህ ድርጊቱ ትክክል ነው። ( እውነት – ሃሰት )

16. 'በአሏህ መንገድ ለሚታገሉ' ሲባል መስጅድ መገንባትን የመሰሉ የኸይር አቅጣጫዎችን ሁሉ ያጠቃልላል። ( እውነት – ሃሰት )

17. የወርቅና ብር እንዲሁም ሌሎች መገበያያዎች የዘካ ገንዘብ የሚቀመረው ለ 40 እያካፈሉ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

18. በሚደለቡ(ሳኢማ) እንስሶች ላይ ዘካ ግዴታ ሲሆን በሚሰሩና በሚቀለቡ እንስሶች ላይ ግን ግዴታ አይደለም። ( እውነት – ሃሰት )

19. አትክልትና ፍራፍሬ መጠናቸው የዘካ ግዴታነት ልኬት(ኒሷብ) ላይ ከደረሱ ዘካ ሊወጣባቸው ግዴታ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

20. በጥረት ከበለፀገ አትክልትና ፍራፍሬ የሚወጣው የዘካ መጠን 1/20 ነው። ( እውነት – ሃሰት )

21. ወርቅ የዘካ ግዴታነት ልኬቱን ከደረሰ ዘካ ይወጣበታል፤ መጠኑም 20 ሚስቃል ነው። ( እውነት – ሃሰት )

22. ከሚከተሉት ዘካ ግዴታ የሚሆንባቸውን አክብብ

O ዶሮ　　O ሱቅ　　O የተቀለበች እንስሳ

O የደለበ ግመል　　O የተምር ማሳ　O ከወርቅ 25 “*ሚስቃል*”

23. *“ተቢዕ”* የምትባለው ሁለት አመት የሞላ ከብት ነች። ( እውነት – ሃሰት )

24. በጊዜያችን ያሉት የመገበያያ ገንዘቦች ዘካ የሚሰላው በ …… መሰረት ላይ ነው።

O በመገበያያ ቁሶች O በወርቅ ወይ በብር (ሲልቨር) ኒሷብ ተመን

O በወርቅና ብር(ሲልቨር) ኒሷብ ተመን

25. በጊዜያችን ያሉት የመገበያያ ገንዘቦች ዘካ መጠን O 0.025 O 1/20ኛ

26. የ 80 ግራም ወርቅ ዘካ መጠን …

O 2 ግራም O 4 ግራም O ዘካ የለበትም

27. መኖርያ ቤቶች ዘካ ይወጣባቸዋል ( እውነት – ሃሰት )

28. ጉዞ የወጣ ሁሉ ኢብኑ ሰቢል ስለሆነ ዘካ ይሰጠዋል ( እውነት – ሃሰት )

## የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

### ሶስተኛ: ፆም

በቋንቋ ደረጃ መታቀብ ማለት ሲሆን፤ በሸሪዓ ደረጃ ደግሞ ከትክክለኛው ጎህ መቅደድ ጀምሮ ፀሃይ እስክትጠልቅ ድረስ ከምግብ ከመጠጥና ከሌሎችም የሚያስፈጥሩ ነገራቶች መታቀብ ማለት ነው።

### የፆም ማእዘናት

#### 1- ኒያ

#### 2- ከሚያስፈጥሩት ነገራቶች መታቀብ

**ግዴታ ለሆነው ፆም ኒያ**

ከለሊት ማለትም ከፈጅር በፊት ጀምሮ ለግዴታ ፆም ኒያ ማድረግ የግድ ነው። ገና በወርሃ ረመዷን መግቢያ የተቋጠረ ኒያ(ሃሳብ) በቂ ነው። ቦታዋ ልብ ሲሆን ቃሏን በአንደበት አውጥቶ መናገሩ ቢድዓ ነው።

**ተጨማሪ ለሆነ ፆም የሚደረግ ኒያ**

የሚያስፈጥርን ነገር እስካላስቀደመ ድረስ በየትኛውም ሰአት ኒያውን ቢያስብ ይሆናል። ነገር ግን ኒያውን ከቋጠረበት ሰአት ጀምሮ ነው አጅሩ ሊታሰብለት የሚችለው።

### የፆም አይነቶች

**ግዴታ:**

የረመዷን ወር፣ የከፋራ እና የስለት ፆም

**ተጨማሪ:**

ከነኝህ ውጭ ያለ ፆም ሁሉ

**የፆም ግዴታነት ቅድመ መስፈርቶች**

1- ሙስሊም መሆን 2- ጤነማ አእምሮ ያለው መሆን

3- ለአቅመ አዳም መድረስ፡ ለአቅመ አዳም ካልደረሰ እንዲፆምም ይበረታታል አስተዳዳሪውም ያዘዋል፤

4- በአገሩ ላይ መሆን: ፆም በመንገደኛ ላይ ግዴታ አይደለም፤ የማያጨናንቀው እስከሆነ ድረስ ግን ቢፆም በላጭ ይሆንለታል ምክንያቱም ነብዩ ﷺ እንዲሁ ነውና ያደረጉት፤ እንዲሁም በአስቸኳይ ከተጠያቂነት መፅዳትም ተፈላጊ በመሆኑ፤ ለግለሰቡም የገራ በመሆኑ እና የረመዷንን ችሮታምለማግኘ ሲባል

5- አካላዊ ጤንነት 6- ከወር አበባ እና ከወሊድ ደም መፅዳት

## የበሽታ አይነቶች ከፆም አንፃር

### ማገገሙ ተስፋ የማይደረግበት በሽታ

መፆም የተሳናቸው ሽማግሌም በዚሁ የሚጠቃለሉ ሲሆን መፆሙ ግዴታ አይሆንበትም ነገር ግን ለእያንዳንዱ ቀን ሚስኪን ያበላል። ወይ በቀናቶቹ ልክ ቆጥሮሚስኪኖችን በመሰብሰብ ይመግባል፤ አልያም ደግሞ በቀናቶቹ ልክ ለእያንዳንዱ ሚስኪን 510 ግራም (በነብዩ ጊዜ የነበረው ሷዕ ሩ) ምርጥ ስንዴ ሊልክ ነው። እንደ ስጋ ወይም ዘይት አይነት የሚያባላውን ቢጨምርበት መልካም ይሆንለታል።

### ማገገሙ ተስፋ የሚጣልበት ሆኖ እያለ ለመፆም ግን አስቸጋሪ የሆነ

እንደ የወር አበባዋ ላይ ያለች፣ በወሊድ ደም ያለች፣ አጥቢ እና ሙሳፊር ያሉትን የሚያጠቃልል ሲሆን ከዚህ ባገገመ ጊዜ ያፈጠረባቸውን ቀናቶች ቀዷ ፁሞ ያካክሳል። ከማገገሙ በፊት ህይወቱ ካለፈች ይቅር ይባልለታል።

## የረመዷን ወር መግባቱ የሚረጋገጠው በምንድን ነው?

ወይ የረመዷን ጨረቃ ከታየች፤ አለበለዚያ የሽዕባንን ወር ሰላሳ መሙላት ነው።

## ፆምን የሚያፈርሱ ነገሮች?

1- ሆን ብሎ መብላት ወይንም መጠጣት፤ ዘንግቶ ከሆነ ፆሙ ልክ ነው(ይቀጥል)።

2- ግንኙነት መፈፀም፤ ግንኙነቱን የፈፀመው በወርሃ ረመዷን በቀኑ ክፍለጊዜ እስከሆነ ድረስ ከባድ የሆነችዋ ከፋራ ሊያወጣ ግዴታው ነው። ይህም ባርያ ነፃ ማውጣት፤ ይህን የማይችል ከሆነ ደግሞ ሁለት ወር በተከታታይ ሊፆም ነው፤ ይህን የማይችል ከሆነ ደግሞ ስሳ ሚስኪን ማብላት ይኖርበታል።

3- ወይ በመነካካት፣ ወይ በመሳም፣ ወይ በማቀፍ ወይም በመሳሰሉት አማካኝነት የዘር ፈሳሽ ማፍሰስ

4- እንደምግብ መርፌ ያለ በምግብ እና መጠጥ ምትክ የሚሆን፤ ከምግብ መርፌ ውጭ ያለው መርፌ አያስፈጥርም

5- በዋግምትና በመሳሰሉት አማካኝነት ደም መፍሰስ፤ ለምርመራ የሚሰጥ ደም ግን አያስፈጥርም

6- ሆን ብሎ ማስታወክ

7- የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ፍሰት

## አንዳንድ ለፆመኛ የሚፈቀዱ ነገራቶች

ምራቅን መዋጥ፤ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ምግብን በምላስ መቅመስ፤ ትጥበት፤ ሲዋክ፤ ሽቶ እና ራስን ማርጠብ።

## የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

## በፆም የሚበረታቱ

**1.** ሱሑርን መብላት **2.** ሱሑርን ዘግየት ማድረጉ **3.** ማፍጠርን ማፍጠኑ **4.** በእርጥብ ተምር ማፍጠር፤ ከሌለ ደግሞ በየትኛውም ተምር ማፍጠር፤ ብዛቱ ለሁለት የማይከፈልን ቁጥር ቢሆን ይመረጣል። ይህንንም ካላገኘ የሆነ ያክል ውኋ መጎንጨት፤ ምንም ካላገኘ ደግሞ ማፍጠሩን በልቡ በማሰብ ያፈጥራል። **5.** ፆሙን በሚይዝበት እና በሚያፈጥርበት ሰአት ዱዓእ ማድረግ **6.** ምፅዋት ማብዛት **7.** የለሊት ሰላትን ለመስገድ መጣጣር **8.** ቁርአን መቅራት **9.** ለሚዘልፍህ ሰው "ፆመኛ ነኝ" ማለት **10**. ዑምራ ማድረግ **11.** የመጨረሻዎቹን 10 ለሊቶች ኢዕቲካፍ ማድረግ **12.** ለይለቱል ቀድርን ማደን

## በፆም የሚወገዙ

1. ውዱእ በሚደረግበት ጊዜ አፍን እና አፍንጫን ጥግ ድረስ ማጠብ
2. አስፈላጊነቱ ባልታመነበት አጋጣሚ ወጥ መቅመስ

## ፆመኛ የተከለከላቸው ነገሮች

1. አክታን መዋጥ [ፆሙን ባያስፈጥረውም]
2. ምናልባት በዛ ምክንያት ወደሌላ እንደማይገባ በራሱ ለማይተማመን ሰው ሚስቱን መሳሙ
3. ማበል [ያም ከረመዷን ውጭ ባሉ ጊዜያቶችም የተከለከሉ ነገሮችን መፈፀም]
4. ቂላቂልነት [ያም መጃጃልና ቅጥ ያጣ መሆን ማለት ነው]
5. ዊሷል [ሳያፈጥር አከታትሎ መፆም]

## ተጨማሪ ፆም

1- የረመዷንን ወር አሟልቶ ለፆመ አስከትሎ ቢቻል በሁለተኛው ቀን ከሸዋል ወር 6 ቀን መፆም

2- ሓጅ ላይ ላልሆነ ሰው የዓረፋን ቀን መፆም

3- የዓሹራ ቀንን ከአስራ አንደኛውና ከአስራ ሁለተኛው ቀንጋ ደርቦ መፆም

4- ሰኞና ሃሙስን መፆም፤ በተለይም ሰኞ መፆም

5- ከየወሩ ሶስት ቀን መፆም፤ በተለይም በሂጅሪ አቆጣጠር 13ኛ ፣ 14ኛን እና 15ኛ ን ቀን መፆም

6- አንዳንድ ቀን እየዘለሉ መፆም 7- አሏህ ያከበረውን የሙሓረምን ወር መፆም

8- የዙልሒጃን 9ኛ ቀን መፆም

9- የሸዕባንን ወር መፆም፤ ይሁን እንጅ አይሞላውም

## የተወገዘው ፆም

እለተ ጁምዓን፣ ቅዳሜን ወይንም እሁድን በፆም መነጠል የተወገዘ ነው። የነጠለው ዓረፋ በመሆኑ ወይም መሰል ምክንያት ከሆነ ግን ችግር የለውም።

## የተከለከለ ፆም

1- የረጀብን ወር በፆም መነጠል

2- በዒዱ እለት መፆም

3- የጥርጣሬውን ቀን (ረመዷን መሆኑ የሚያጠራጥር) መፆም፤ ቀደም ብሎ ከተጠቀሱት ፆሞች አንዱን ሲፆም ከነበረና ባጋጣሚ ካልገጠመ በቀር

4- በሓጅ ስርአት እርድ ለማቅረብ የተሳነው ካልሆነ በቀር አያመ ተሽሪቅን (ከዒደል አድሓ/ዓረፋ በኋላ ያሉት ሶስት ቀናት) መፆም

5- ለዘላለሙ በየቀኑ ሳያቋርጡ መፆም

# የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

## *ፆምን ቀዷ(ያመለጠህን መመለስ) ከማውጣት ጋ ተያያዥ የሆኑ ህግጋት*

- አከታትሎ መፆሙ የሚበረታታ ነው
- ልክ ከዒዱ እለት በኋላ ማስከተሉ ተገቢ ነው
- የአንዱን ረመዷን ቀዷ ፆም ወደሌላኛው ረመዷን አቅራቢያ ድረስ ማዘግየት አይፈቀድም
- በቂ ምክንያት ሳይኖረው ካዘገየው ወንጀለኛ ይሆናል፤ ይሁን እንጅ ያልፆመውን ቀዷ ከማድረግ ውጭ ሌላ ግድ የሚለው ነገር የለም።

## *ዘካተል ፊጥር*

ትልቅም ሆነ ትንሽ፤ ወንድም ሆነ ሴት፤ ባርያም ይሁን ጨዋ ሆኖ የረመዷን ወር የመጨረሻዋ ቀን ጸሃይ እስክትጠልቅ ድረስ ሙስሊም ሆኖ የመቆየትን እድል የተሰጠው ሁሉ መስጠት ያለበት የዘካ አይነት ነው። ፀሃይዋ ከገባችበት ሰአት ጀምሮ የዒዱን ቀን መስጠት ይኖርበታል። ይህም በራሱም ሆነ በሌላው የቤተሰቡ አባላት በመሰረታዊነት ከሚቀለቡት ትርፍ ከሆነው በእያንዳንዱ አንድ ሷዕ ይመፀውታል። ማህፀን ላይ ላለ ሽል ደግሞ በሱ ስም መስጠቱ ግዴታም ባይሆን የሚበረታታ ነው። ከተደነገገባቸው ጥበቦች መካከል:

- ለፆመኛው ዛዛታና መንዘላዘል ማጥርያው ነች
- ድሆችና ሚስኪኖች የዒድ እለት ጠያቂ የሰውን ከጃይ ከመሆን ታብቃቃቸዋለች

### ዘካተል ፊጥር ስለሚሰጥበት ጊዜ

| የተከለከለ ጊዜ | የሚበረታታው ጊዜ | የሚፈቀደው ጊዜ |
|---|---|---|
| ከዒድ ሶላት በኋላ | ከፈጅር በኋላ ከሶላተል ዒድ በፊት | ከዒዱ እለት በአንድ ቀን ወይንም በሁለት ቀን ቀደም ብሎ |

## የዘካተል ፊጥር መጠኑ

የሰው ልጅ ከሚመገበው 1 ሷዕ እህል፤ ብር ነገር አያብቃቃም። የ 1 ሷዕ መጠኑ ማለት ደግሞ በጥሩ ስንዴ 2 ኪሎ ከ 40 ግራም ማለት ነው።

## የዒድ ሶላት

በነፍስ ወከፍ ደረጃ በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ ግዴታ (ፈርዱል ዓይን) ነች። የምትሰገድበት ወቅትም ፀሃይ የዘንግን ያክል ከፍ ካለችበት ጊዜ ጀምሮ መሃል አናት እስከምትሆንበት ጊዜ ድረስ ነው። ያመለጠችበት ደግሞ ቀዷ ሊያወጣት አይችልም። ሱናው ከህንፃ ውጭ በሆነ የተንጣለለ ሜዳ ላይ ቢሰገድ ሲሆን ነገር ግን መስጅድ ውስጥ መስገዱም የተፈቀደ ነው። ከዒድ ሶላት በፊት ብዛቱ ዊትር(ለሁለት የማይካፈል) የሆነ መጠን ያለውን ቴምር ቢበላም፤ ንፅህናውን ጠብቆ ከሽቶውም ተቀባብቶ ከልብሱም ምርጡን ለብሶ ቢሄድ፤ መንገዱንም ሲሄድ ባንዱ መንገድ ሂዶ ሲመለስ መንገዱን ቀይሮ ቢመለስ ሱና ይሆንለታል። አንድ ሙስሊም ሌላኛውን እንደ “ተቀበለሏሁ ሚና ወሚንኩም ” በመሰለ ዒዱን በተመለከተ እንኳን አደረሰህ ቢለው ችግር የለውም። በእለተ ዒድ ለሊትና ጸሃይዋም እስክትጠልቅ ድረስ በአምስቱ የሶላት ወቅቶች ከየሶላቱ በኋላ ልቅ የሆነውን ተክቢራ ማለቱ ሱና ነው። የሚባለውም: “አሏሁ አክበር! አሏሁ አክበር! ላ ኢላሃ ኢለሏህ፤ ወሏሁ አክበር! አሏሁ አክበር! ወሊላሂል ሓምድ” ነው። አሰጋገዱም: ከኹጥባው በፊት ሁለት ረከዓ የሚሰገድ ሲሆን በመጀመርያው ረከዓ ልክ ተክቢረተል ኢሕራም እንዳለ ስድስት ጊዜ “አሏሁ አክበር!” ይላል፤ በሁለተኛው ረከዓ ደግሞ ለመቆም ብሎ አሏሁ አክበር ካለው ውጭ አምስት ጊዜ አሏሁ አክበር በማለት ነው።

# ስለፆም ፈተና

1. የፆም ማእዘናት ስንት ናቸው?   O 2   O 3   O 4

2. ፆም ግዴታ የሆነው በማን ላይ ነው?

ሀ. ..................................................................................

ለ. ..................................................................................

ሐ. ..................................................................................

መ. ..................................................................................

3. በሽታ ሁሉ ከፆም ያቅባል። ( እውነት – ሃሰት )

4. የተከታዮቹን ጉዳዮች ኢስላማዊ ፍርድ ጥቀስ:

| ጉዳዩ | ኢስላማዊ ፍርዱ |
|---|---|
| መፆሙን የወሰነው(የነየው) ከፈጅር በኋላ ነው | |
| ያለ ኒያ ቢፆም | |
| የልጅ ፆም | |
| የሙሳፊር(የመንገደኛ) ፆም | |
| በወሊድ ደም ያለች ሴት ፆም | |
| የ(የተሳነው ሰው) ደካማ ሽማግሌ ፆም | |
| ፆሞ እያለ ቢበላ | |
| ፆመኛ ምግብ መርፌ ቢተከልለት | |
| የአይን ጠብታ ለፆመኛ | |
| ፆመኛ ማደንዘዣ ቢወጋ | |
| ፆመኛ ቢታገም | |

## የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

| | |
|---|---|
| ማስታወክ | |
| ምራቅን መዋጥ | |
| ያመኛ ምግብ ቢቀምስ | |
| ያመኛ ቢተኛ | |
| ያመኛ ገላውን ቢታጠብ | |
| ራስን ማቀዝቀዝ | |
| ሲዋከ ለያመኛ | |
| እጣን | |
| የሱሑር ወቅት | |
| በምንድን ነው ሱሑር የሚታሰረው | |
| በምንድን ነው የሚፈጠረው? | … … … … … … .. ካላገኘ… … … … … … … … … .. ካለገኘ ደግሞ … … … … … ... … .. ካላገኘ ……………………… ያፈጥራል። |
| የተራዊሕ ሶላት | |
| በረመዷን ወር ዑምራ ማድረግ | |
| ያመኛ ሆኖ አፍን ሲያጥቡ ጥግ ድረስ ማፅዳት | |
| ያመኛ ሆኖ መሳም | |
| ዊሷል (ሳያፈጥሩ) አከታትሎ ለሁለት ቀናት መፆም | |
| ከሸዋል ወር ለ 6 ቀናት መፆም | |
| የዓረፋን ቀን መፆም | |

## የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

| | |
|---|---|
| የጥርጣሬን ቀን (ረመዷን መሆን አለመሆኑ ያልተረጋገጠን ቀን) መፆም | |
| የዒድን ቀን መፆም | |
| ከዒድ አልአድሓ በኋላ ያሉትን ሶስት ቀናት መፆም | |
| የሙሓረምን ወር መፆም | |
| የረጀብን ወር መፆም | |
| ሁልጊዜ በየቀኑ እያከታተሉ መፆም | |
| የጁምዓን ቀን መፆም | |
| ቀዷን እስከሌላኛው ረመዷን ማዘግየት | |

## የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

### አራተኛ: ሓጅ

ሓጅ ከእስልምና ማእዘናት 5ኛው ማእዘን ነው። ሙስሊም፣ ጤናማ አእምሮ፣ ለአቅመ አዳም/ሄዋን መድረስ፣ ጨዋ መሆን እና መቻል የሚሉትን መስፈርቶችን ባሟላ ላይ ሁሉ ግዴታ ነው። ሴት ልጅ ሓጅ ለማድረግ ጉዞ መውጣት የሚጠበቅባት ከሆነ መሕረም የሆነ ሰው አብሯት መሆኑ ተጨማሪ መስፈርት ነው። የሓጅ ማእዘናት አራት ናቸው:

**ኢሕራም**
ሓጅን ለመጀመር የሚደረገው ኒያ ሲሆን ያ ማለት ተልቢያን ወይም ደግሞ የሓጅን ሽርጥና ግልድሙን ማድረግ ማለታችን አይደለም፤

**ዓረፋ ላይ መገኘት**
ጊዜውም ከዙልሒጃ 9ኛው ቀን የፀሃይ መዘንበል ጀምሮ እስከ የዒዱ እለት ፀሃይ መውጫ ድረስ ነው። ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል: "***ሓጅ ማለት ዓረፋን ነው***"

**ጡዋፈል ኢፋዷ**
የዚያራው ጡዋፍ፤ ይህም በዓረፋ ሜዳ ላይ ከመቆም በኋላ የሚሆን ሲሆን ጡዋፈል ቁዱምን ማለት አይደለም።

**በሁለቱ ተራሮች መካከል ሰዕይ ማድረግ**
በሰፋ እና መርዋ ተራሮች መካከል ዱብዱብ ማለት፤ አሏህ እንዲህ ይላል: "**በርግጥ ሰፋ እና መርዋ ከአሏህ ምልክቶች ናቸው።**" (2:158).

### የስርአተ ሓጅ አይነቶች

**ተመቱዕ**
በሓጅ ወራት ዑምራን ኒያ አድርጎ ካጠናቀቀ በኋላ ይፈታና በዛው አመት ለሓጅ ኢሕራም ያደርጋል። ሃድይ (እርድ) ማቅረብ ይጠበቅበታል።

**ቂራን**
ሓጅና ዑምራን አንድላይ ኒያ ያደርግና ሁለቱንም በየተራ ያከናውናል። ሃድይ (እርድ) ማቅረብ ይጠበቅበታል።

**ኢፍራድ**
ሓጅን ብቻ ኒያ ያደርግና ሓጁን ብቻ ያከናውናል

## የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

### የሓጅ ግዴታዎች

ከነኝህ ግዴታዎች መካከል አንዱን የተወ በመስዋእት ሊጠግነው ግዴታው ነው፤ ይህም በሓረም ታርዳ ለመካ ድሆች የምትከፋፈል በግ ወይም ፍየል ነች። ከሷ ሊበላ ግን አይፈቀድለትም።

- ከሚቃቱ (ከመግቢያው አንፃር ለኢሕራም በተወሰነለት ቦታ) ሆኖ ኢሕራም ሊያደርግ
- በቀኑ ክፍለ ጊዜ በዓረፋ ሜዳ ለተገኘ ፀሃይ እስክትጠልቅ ድረስ መቆም
- ሙዝደሊፋ ላይ መቆየት
- የአያመ ተሽሪቅ ሌሊቶችን በሚና ላይ መቆየት
- ፀጉርን መላጨት ወይንም ማሳጠር
- ጠጠሮቹን መወርወር
- ከሓጅ ወራት ውጭ እንኳ ቢሆንም መካን ለቆ ሊወጣ ባለበት ጊዜ የመሰናበቻውን ጡዋፍ ማድረግ፤ የወር አበባዋ ወይም የወሊድ ደም ላይ ካለች ሴት በቀር።

### *የሓጅ እና የዑምራ መቼት (ሚቃት):*

**ቦታ**

-***ዞልሑለይፋ*** ለመዲና እና በመዲና በኩል ለሚያልፉ ሰዎች
-***አልጁሕፋህ*** ከሻም፣ ለግብፆችና ለሞሮኮዎች
-***ቀርነል መናዚል*** ለነጅዶች
-***የለምለም*** ለየመኖች
-***ዛቱ ዒርቅ*** ለዒራቆች

**ጊዜው**

የሓጅ ወራቶች ናቸው: ***ሸዋል፣ ዞልቃዒዳህ,*** እና ***ዞልሒጃህ***

የጊዜ መቼቱ ሓጅን ነው እንጅ የሚመለከተው ዑምራ ለማድረግ የተገደበ ጊዜ የለውም።

## የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

### ተወዳጅ የሓጅ ክንውኖች

ነጩን የሓጅ ሽርጥና ግልድም መልበስ

ለኢሕራም መተጣጠብና ሽቶ መቀባት

*ከኢሕራም ጀምሮ እስከ ጀመረቱል ዓቀባ የጠጠር ውርወራ ድረስ ተልቢያ (ለበይክ አሏሁመ ለበይክ ...) ማለት*

የኢሕራምን ኒያ ከማለት በፊት ጥፍርንም ሆነ መቆረጥ ያለበትን ፀጉር መቁረጥ

ተመቱዕ አይነቱን የሓጅ ስርአት ለሚያደርግ ሰው በጡዋፈል ቁዱም እና በዑምራ ጡዋፍ የመጀመርያዎቹ ሶስት ዙሮች በሶምሶማ ይዞራል። ሶምሶማ ስንል ዱብዱብ ማለት ወይም እጅግ ፈጣን እርምጃ ማለታችን ነው።

የኢፍራድና የቂራን ስርአተ ሓጅ ለሚያደርግ ሰው ጡዋፈል ቁዱም ማድረግ

ሙዝደሊፋ እንደደረሰ ዒሻን ወደ መግሪብ አምጥቶ ጀምዕ ተቅዲም በማድረግ ይሰግዳል

ተመቱዕ አይነቱን የሓጅ ስርአት ለሚያደርግ ሰው በበጡዋፈል ቁዱም እና በዑምራ ጡዋፍ ኢድጢባዕ አይነቱን አለባበስ ይለብሳል፤ ይህም ቀኝ ትከሻውን ገልጦ መልበሱ ነው

ሓጀረል አስወድን መሳም

የዓረፋን ለሊት ሚና ላይ ማሳለፍ

ከፈጅር ጀምሮ ፀሃይ ልትጠልቅ እስከምትቃረብበት ጊዜ ድረስ ሙዝደሊፋ ላይ በተለይም መሽዓረል ሓረም ላይ መቆም፤ መላ ሙዝደሊፋም ግን መቆሚያ ነው።

## በኢሕራም የተከለከሉ ነገሮች

**ዘጠኝ ናቸው:** የራስ ቅልንም የሌላ አካልንም ፀጉር መላጨት፤ ጥፍርን መቁረጥ፤ ለወንዶች የራስ ቅልን በሆነ ነገር መሸፈን፤ በሆነ የሰውነት ቅርፅ የተሰፉ ልብሶችን መልበስ፤ ለሴት ልጅ ኒቃብ ወይንም ጓንት መልበስ፤ ሽቶ መቀባት [ሽታ ያለው ሳሙናም እንዲሁ]፤ የየብስ አደን ማደንና መግደል፤ ለራሱም ይሁን ለሌላ ኒካሕ ማሰር፣ ግንኙነት መፈፀም ወይም ከባለቤትህ ጋ መተሻሸት የተከለከሉ ናቸው። ዘንግቶ ወይ ባለማወቅ ወይም ደግሞ ተገዶ ከነኝህ ነገራቶች መካከል አንዱን የፈፀመ አንዳችም ነገር የለበትም፤ ምናልባት አደን ማደን ካልሆነ በቀር እንደዛ ያደረገ በልቁ "ፊድያ" የማድረግ ግዴታ አለበት። ሆን ብሎ የፈፀመ ግን ክልክላቶች አራት አይነት ናቸው:

### ፊድያ የማይጠበቅበት

ለራሱም ይሁን ለሌላ ሰው ኒካሕ ማሰር፤ ከባለቤት ጋ መተሻሸትም እንዲሁ ነገር ግን የዘር ፈሳሽ በሚያወጣ መልኩ ካልሆነ ወይም ካላወጣ ማድረግ የሚጠበቅበት ነገር ባይኖርም ተውባ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

### አምሳያውን ፊድያ ማቅረብ ያለበት

የየብስ አደንን መግደልና ማደን፤ የገደለ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ መስዋእት ማቅረብ ይኖርበታል። ይህም : በግ ወይ ፍየል፣ ወይ ከብት ወይ ግመል ሚዛናዊየሚባሉ ሰዎች ባስቀመጡት መልኩ

### ከባድ ፊድያ የሚጠበቅበት

ግንኙነት መፈፀም : ከመጀመርያው ተሕሊል በፊት የፈፀመ ከሆነ ሓጁ ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል፤ ነገር ግን ይቀጥላል አያቋርጥም፤ በሌላኛው አመት ይደግመውና መስዋእትንም ያቀርባል።

### ፊድያው የ "አዛ" ፊድያ የሆነ

ይህ ቀሪው ክልከላን ያጠቃልላል፤ ፊድያው ደግሞ በምርጫ ይሆንለታል : ወይ ሶስት ቀን መፆም፣ ለእያንዳንዱ ሚስኪን ግማሽ ሷዕ እያደረገ ስሳ ሚስኪን መመገብ፣ ወይም ደግሞ በሓረም ድሆች መካከል የምትከፋፈል የሆነችን በግ/ፍየል ማረድ።

# የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

**የሓጅ ቀናት ስያሜ**

- እለተ ተርዊያህ (የመጠጫ ቀን) ፡ ይህም 8ኛው ቀን ይህም የተባለበት ውኋ ወደ ሚና ያግዙ የነበሩ ከመሆናቸው አንፃር ነው።
- የዓረፋ ቀን ወይም ወቅፋህ፡ ይህም 9ኛው ቀን ነው።
- የዒድ እለት የእርዱ ቀን፤ ይህም 10ኛው ቀን ነው።
- እለተ “ቀር” ይህም 11ኛው ቀን ነው።
- ቀዳሚው እለተ “ነፈር” ይህም 12ኛው ቀን ነው።
- ሁለተኛው እለተ “ነፈር” ይህም 13ኛው ቀን ነው።

ለይለቱ ጁመዕ የሚባለው የስብስቡ እለት የዒድ እለት ነው። ይህም የተባለው ሰዎች በዓረፋ ከቆሙ በኋላ የሚሰባሰቡበት ቀን በመሆኑ ነው። ምክንያቱም በዘመነ ጃሂሊያ የመካ ሰዎች ወደ ዓረፋ አይወጡምና ነው።

**በሓጅ ሂደት ለየት ባለ መልኩ ዱዓእ የሚደረግባቸው 5ቱ ቦታዎች**

- በ 9ኛው ቀን በእለተ ዓረፋ ፀሃይ ካዘነበለች ጀምሮ እስክትጠልቅ ድረስ።
- ሙዝደሊፋ ላይ የዘጠነኛው ቀን ፈጅር እስከ ፀሃይ መውጫ አቅራቢያ
- ከዒድ በኋላ ባሉት ሶስት ቀናት ከትንሹና መካከለኛው የጠጠር ውርወራ በኋላ
- ጡዋፍ በምናደርግበት ጊዜ
- በሰፋና መርዋ መካከል ሰዕይ በምናደርግበት ጊዜ

## የሓጅና ዑምራ ማብራርያ

## ሸይኽ ኢብኑ ዑሠይሚን –አሏህ ይዘንላቸውና- እንዲህ ብለዋል:

ክቡር ሓጅ አድራጊ ሆይ! ለኢሕራም ወደ ተዘጋጀው ቦታ ከደረሱ በኋላ ገላዎን ይታጠቡ፤ ወንዶች በሰውነትዎ ፣ በጭንቅላትዎ ወይም በጢምዎም ላይ ሽቶ ይቀቡ። ከዚያም በሚያደርጉት ስርአተ-ሓጅ መሰረት [ለምሳሌ “ተመቱዕ” ከሆነ የሚያደርጉት] ለዑምራ ኢሕራም በማድረግ ተልቢያ እያሉ ወደ መካ ይሂዱ፤ በተከበረው ካዕባ ሲደርሱ ለዑምራ 7 ዙር ጡዋፍ ያድርጉ። ከካዕባ አንፃር ቅርብም ይሁን ሩቅ ሆኖ በመስጊዱ ውስጥ እስከሆነ ድረስ በማንኛውም ቦታ ጡዋፎን ማድረግ እንደሚችሉ ይወቁ። ሆኖም በሰው ጭንቅንቅ ካልተቸገሩ ወደካዕባው መጠጋቶ የተሻለ ነው። በጣም የተጨናነቀ ከሆነ ግን ራቅ ይበሉ። ምስጋና ለአሏህ ይገባውና በዚህ ረገድ ነገሩ የተጣበበ አይደለም።

አንዴ ጡዋፎን ካጠናቀቁ በኋላ ከመቃሙ ኢብራሂም - ዓለይሂ ሰላም- በስተጀርባ ሁለት ረከዓ ሶላት ይስገዱ። ከተቻለ ተጠግተው መስገድ፤ ካልቻሉ ደግሞ መቃሙ ኢብራሂም በእርሶ እና በካዕባ መካከል እስከሆነ ድረስ የትም ቢሆን መስገድ ይችላሉ። ከዚያ ወደ የዑምራ “ሰዕይ” ይሂዱ እና ከ “ሰፋ” ይጀምሩ። 7 ቱን ዙሮች ካጠናቀቁ በኋላ ከመላው ጭንቅላቶ ላይ ፀጉር ይከርክሙ፤ በብዙዎች ድርጊት ተታለው ከጭንቅላቶ የሆነ ክፍል ላይ ብቻ ፀጉር መቁረጦ በቂ አይደለም።

በዙል ሒጃ 8ኛ ቀን ገላዎን ይታጠቡ፤ ወንዶችም ሽቶ ይቀቡ። እርስዎ ካረፉበት ለሓጅ ኢሕራም ያድርጉ። ወደ ሚና ሄደው ዙህርን፣ ዓስርን፣ መግሪብን፣ ዒሻን እና ፈጅርን ይስገዱ። ሶላቶቹን ያሳጥሩ እንጅ ጀምዕ አያድርጉ። ምክንያቱም ነቢያችን ﷺ ሶላትን በሚና እና በመካ ሲሰግዱ ያሳጥሩ ነበርንጅ አያጣምሩም ነበርና። በእለተ ዓረፋህ ፀሐይ በምትወጣበት ጊዜ ለአሏህ በመተናነስ ተልቢያህን እያሉ ወደ ዓረፋ ይሂዱ። ከዚያም የዙህርንና የዓስርን ሶላት በዓረፋህ ጀምዕ በማድረግ ሁለት ሁለት ረከዓ አድርገው ይስገዱ።

ከዚያም አላህን በመማፀን እና በመለመን ይጠመዱ፤ ከውዱእ ውጭ ላለመሆን የተቻለዎትን ሁሉ ይሞክሩ፤ ወደ ቂብላም ይቅጣጩ፤ ያ የተደነገገው ተራራው ከኋላዎ ቢሆንብዎም እንኳ ቂብላዎን መቅጣጨቶ ነውና። የዓረፋን ድንበሯን እና የተዘጋጁትን ምልክቶች በጥንቃቄ ያስተውሉና በዚያ ውስጥ መሆኖን እርግጠኛ ይሁኑ፤ ምክንያቱም ብዙዎች ዓረፋ ውስጥ መቆም ሲኖርባቸው ከሷ ውጭ እየቆሙ ነውና። በዓረፋ ለማይቆም ደግሞ ሓጅ የለውም፤ ነብያችንም ﷺ **"ሐጅ ዐረፋ ነው"** ብለዋልና። መላ ዓረፋ ደግሞ ምስራቋም፣ ምዕራቧም፣ ሰሜኗም ሆነ ደቡቧ ሁሉ ከዑርና ሸለቆ በቀር መቆሚያ ነው። ነቢያችን ﷺ **"እኔ እዚሁ ቆሜያለሁ፤ እናም በዓረፋ በየትኛውም ቦታ መቆም ትችላላችሁ።"** ብለዋልና።

ፀሐይ መጥለቋን ካረጋገጡ በኋላ ለአሏህ በመተናነስ ተልቢያህን እያሉ ወደ ሙዝደሊፋ ያቅኑ። ነብያችሁ ﷺ እንዳዘዟችሁ መረጋጋትን አጥብቃችሁ ያዙ፤ በርግጥም ኮ ነብዩ ﷺ የግመሏን ልጓም አጥብቀው ከዓረፋ ሲሄዱ ግመሏም ከመረጋጋቷ አንፃር ራሷ ኮርቻቸውን የሚነካበት አጋጣሚም ነበረ። የተከበረው እጃቸውን እያወዛወዙም ***"ሰዎች ሆይ! እርጋታን ተላበሱ። እርጋታን ተላበሱ።"*** ይሉ ነበር።

ሙዝደሊፋ ከደረሱ በኋላ መግሪብንና ዒሻእን ሰግደው እስከ ፈጅር ድረስ እዚያው ይቆዩ፤ ነብያችን ﷺ ከፈጅር በፊት ከሙዝደሊፋ ተነስቶ መጓዝን ለማንም አላገሩም፤ ምናልባት ደካሞች ካልሆኑ በቀር እነሱም በሌሊቱ መገባደጃ አካባቢ ነው የሚጓዙት። ፈጅርን ከሰገዱ ወደ ቂብላ ተቅጣጭተው አሏህን በማላቅ "አሏሁ አክበር" ማለትን ያብዙ፤ ያመስግኑት፤ ወጋገኑ ፈንጥቆ ሊነጋጋ እስኪል ድረስ ይለምኑት፤ ከዚያም ፀሃይዋ ከመውጣቷ በፊት ወደ ሚና ይንቀሳቀሱ። ከዚያም 7 ጠጠሮችን ለቅመው ከመካ ቀጥሎ የመጨረሻ ወደሆነው ወደ ጀመረቱል ዓቀባህ በመሄድ በእያንዳንዱ ውርወራ "አሏሁ አክበር!" እያሉ ከፀሐይ መውጣት በኋላ ለአሏህ በመተናነስና እሱኑ እያላቁ 7ቱን ጠጠሮች ይወርውሩ።

ጠጠሮችን የመወርወሩ አስፈላጊነት አላህን ለማክበር እና እርሱን ለማስታወስ መሆኑን ይወቁ። ጠጠሮቹን ሲወረውሩ በጉድጓዱ ውስጥ መውደቃቸው ግዴታ ሲሆን ችካሉን መምታቱ ግን መስፈርት አይደለም። ጠጠሮቹን መወርወርን ካጠናቀቁ እርድዎን ይሰው። ለኡዱሒያ የሚያብቃቃ መስዋእት ካልሆነ በቀር ለሃድይም አያብቃቃም። እርስዎን ወክሎ አንድ ሰው እንዲሠዋ መሾሞ የተፈቀደ ነው። ከእርዱ በኋላ ራስዎን ይላጩ፤ ሲላጩም መላ ራስዎን መሆን ይኖርቦታል፤ ከፊሉን ላጭተው ከፊሉን መተው አይፈቀድሎትም። ሴቶችም ከፀጉራቸው ጫፎች የጣት አንጓ ያህል ይቆርጣሉ።

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ የመጀመርያው ተሓሉል (በሓጁ ስነስርአት ምክንያት የተከለከሉትን ሓላል የሚሆንሎት ሁኔታ) ላይ ነዎት፤ የተለመዱ ልብሶቾንም ለመልበስ ጥፍሮትንም ለመቁረጥ ሽቶንም ለመቀባት ነፃ ነዎት፤ ነገር ግን ከባለቤትዎ ጋር ግንኙነት አይፈቀድሎትም። ከዚያም ከዙህር ሶላት በፊት ወደ መካ ይውረዱ፤ ለሓጅ ጡዋፎንም ሰዕዮንም ያድርጉ። ከዚያም ወደ ሚና ተመልሰው ጡዋፎን እና ሰዕዮን በማድረጎ ፀጉሮን ከመላጨቶም ጋ የጠጠር ውርወራውን በማድረግ የሁለተኛው ተሓሉል ላይ ነዎት። በዚህም ከባለቤቶ ጋ መገናኘትን ጨምሮ የተፈቀደ ይሆናል።

ሰዎች ሆይ! አንድ ሓጅ አድራጊ በዒድለት አራት ስርአተ ሓጅን ይፈፅማል፤ እነሱም፡ ጠጠር መወርወር፣ ከዚያም እርድ፣ ከዚያም መላጨት፣ ከዚያም ጡዋፍና ሰዕይ ናቸው። የተሟላው ቅደም ተከተል ይህ ነው። ነገር ግን ከፊሉን ከከፊሉ ቅደም ተከተል አዛብተው እንደሆን፤ ለምሳሌ እርድን ከመፈፀምዎ በፊት ራስዎን ቢላጩ ችግር የለውም፤ ጡዋፍንና ሰዕይን ወደሚና እስኪዘልቁ ድረስ ቢያዘገዩትም ችግር የለውም፤ እርዱንም አዘግይተው በአስራ ሶስተኛው ቀን ወደ መካ በሄዱ ጊዜ ቢያደርጉትም ችግር የለውም፤ በተለይም ደግሞ አስፈላጊና የተሻለ ሆኖ ከተገኘ።

የ11ኛውን ሌሊት በሚና ያሳልፉት። ፀሃይዋ ዘንበል ካለች በኋላ ሶስቱንም የጠጠር ውርወራዎችን ከትንሹ ጀምረው ከዚያም መካከለኛው ከዚያም ደግሞ ትልቁ አለት ላይ የጠጠር ውርወራዎን ያድርጉ። እያንዳንዱ ውርወራዎ ሰባት ሰባት ጠጠር፤ በእያንዳንዱ ውርወራዎም “አሏሁ አክበር!” እያሉ ይሁን። በእለተ ዒድ የውርወራ ሰአቱ ለሚችል ሰው ፀሃይዋ ከወጣችበት ሰአት ጀምሮ፤ ለደካሞች ደግሞ በሌሊቱ መገባደጃ ሲሆን የመጨረሻ ሰአቱ ደግሞ ፀሃይዋ እስክትጠልቅ ነው። ከዒዱ በኋላ ሰአቱ ደግሞ ፀሃይዋ ዘንበል ካለችበት ጀምሮ ፀሃይዋ እስከምትጠልቅበት ድረስ ነው። ፀሃይዋ ዘንበል ከማለቷ በፊት አይፈቀድም፤ በቀኑ ክፍለ ጊዜ ብዙ መጨናነቅ ካለ ግን በሌሊቱ ክፍለ ጊዜ ውርወራውን ማድረግ ይፈቀዳል። ከእድሜ አንፃር ወይም ከህመም አንፃር መወርወር የሚሳነው ሰው በሱ ምትክ ሆኖ የሚወረውርን መወከል ይችላል። ተወካይም ለራሱም ለሌላም እዛው በቆመበት አከታትሎ መወርወር ይችላል፤ ነገር ግን ለራሱ በመወርወር ይጀምራል። በአስራ ሁለተኛው ቀን ውርወራዎን ካደረጉ ሓጅዎን ቋጭተዋልና ከፈለጉ መሄድ፤ ከፈለጉ ደግሞ አስራ ሶስተኛውን ለሊት እዛው አሳልፈው የቀጣዩ ቀን ፀሃይ ዘንበል ካለች በኋላ ሶስቱንም የጠጠር ውርወራ ማድረግ ይችላሉ፤ ይህ የተሻለው ነው። ምክንያቱም ነቢዩ صلى الله عليه وسلم ያደረጉት እንዲሁ ነውና።

መካን ለቀው ሊወጡ ከሆነ የመሰናበቻውን ጡዋፍ ያድርጉ። በወር አበባና በወሊድ ደም ያሉ ግን የመሰናበቻ ጡዋፍ አይጠበቅባቸውም፤ ወደመስጅዱ በር መምጣታቸውም ሆነ እዛው መቆማቸው የተደነገገም አይደለም።

# የሓጅ ጥያቄዎች

1. ሓጅ ግዴታ የሚሆነው በማን ላይ ነው?

ሀ. ..........................................................................................

ለ. ..........................................................................................

ሐ. ..........................................................................................

መ. ..........................................................................................

ሠ. ሴት ከሆነች በተጨማሪ...............................................................

2. የሓጅ ማእዘናት ስንት ናቸው? O 2 O3 O4

3. *ኢሕራም* ከሓጅ ማእዘናት አንዱ ሲሆን ይህም የሓጅ ሽርጥንና ግልድሙን መልበሱ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

4. *ጡዋፈል ኢፋዷ* ከ *ጡዋፈል ዚያራ* የተለየ እና የመጀመርያው ሩክን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሱና ነው። ( እውነት – ሃሰት )

5. ነብዩ ﷺ ሶስት ጊዜ ነው ሓጅ ያደረጉት። ( እውነት – ሃሰት )

6. አንድ ሰው ሓጅ የማድረግ አቅም እንዳገኘ ወድያውኑ ሓጅ ግዴታ ይሆንበታል። ( እውነት – ሃሰት )

7. የመዲና ሰዎች ኢሕራም የሚያደርጉት ከየለምለም ነው። ( እውነት – ሃሰት )

8. ዑምራ ከጊዜ አንፃር መቼቱ ረመዷን ላይ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

9. በተከታዮቹ አረፍተ ነገር ያሉ ክፍት ቦታዎችን ሙላ: ሓጅና ዑምራ ....... ... .......... ከእድሜ ልክ ........ ግዜ ነው። ሓጅን ሲያከናውን ............... እና ...................... ላይ ያላረፈ ልክ እናቱ እንደወለደችው ሆኖ ከወንጀሉ ይላቀቃል። እጅግ መልካም የሆነ ሓጅ ከ ................... ውጭ ምንዳ የለውም።

10. የመካ ሰዎች ከተንዒም ነው ኢሕራም የሚያደርጉት። ( እውነት – ሃሰት )

11. ሴት ልጅ ሓጅ ስታደርግ ነጩን ልብስ ትለብሳለች። ( እውነት – ሃሰት )
12. ሓጅ ለሚያደርግ ሰው ሽቶ በ …………… ያደርጋል በ………………..አያደርግም።
13. ለሴት ልጅ ተለምዷዊ የሆነው የተሰፋ ልብስ አይፈቀድላትም። ( እውነት – ሃሰት )
14. በኢሕራም ጊዜ ቀበቶ መታጠቅ አይፈቀድም። ( እውነት – ሃሰት )
15. ሴቶች በኢሕራም ጊዜ …………..ም ……………ም አይለብሱም።
16. ኢድጢባዕ የተሰኘውን ቀኝ ትከሻ የሚገለጥበት የአለባበስ አይነት የሚበረታታው በ…

O *በጡዋፈል ዑምራ* O በጡዋፈል ቁዱም(የመግቢያው ጡዋፍ)

O *የዚያራ ጡዋፍ* O በመጀመርያውና በሁለተኛው ጡዋፍ ብቻ O ሁሉም መልስ ነው

17. ሰዕይ በሚያደርግበት ጊዜ በከባድ ፍጥነት መሆን ይኖርበታል። ( እውነት – ሃሰት )
18. *ሰዕይ* የሚጀመረው ከ………….. ሲሆን የሚጠናቀቀው ደግሞ በ …………… **ነው።**
19. ሓጅ የሚያደርጉ ሰዎች ፀሃይ ከመጥለቋ በፊት ነው ከዓረፋ ሜዳ የሚንቀሳቀሱት። ( እውነት – ሃሰት )
20. በዓረፋ ሜዳ መቆም ከሓጅ ግዴታዎች መካከል አንዱ ግዴታ ነው። ( እውነት – ሃሰት )
21. የሓጅ ስነስርአት በ ……. እለት ጀምሮ በ …… እለት ነው የሚጠናቀቀው።
22. በዓረፋ ተራራው ላይ መውጣቱ የተደነገገ አይደለም። ( እውነት – ሃሰት )
23. እርድ መሰዋት ለሙተመቲዕ እና ለቃሪን ግዴታ ሲሆን ለሙፍሪድ ሱናው ነው። ( እውነት – ሃሰት )
24. ተልቢያን ማለት የሚያቆመው በዒድ እለት የጀመረቱል ዓቀባ የጠጠር ውርወራ ነው። ( እውነት – ሃሰት )
25. አንድ ሓጅ አድራጊ ጠጠር ሲወረውር ጠጠሩ ምሰሶውን ሳይነካ በጉድጓዱ ቢያርፍም ውርወራው ትክክል ነው። ( እውነት – ሃሰት )
26. አንድ ሓጅ አድራጊ በአስረኛው ቀን ሶስቱንም የጠጠር ውርወራ ነው የሚወረውረው። ( እውነት – ሃሰት )

27. ከዒድ በኋላ ባሉት ሶስት ቀናት ጠጠር የሚወረወረው ከፀሃይ መዘንበል ጀምሮ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

28. በጀመረተል ዓቀባህ ጠጠር ከተወረወረ በኋላ ዱዓእ ማድረጉ የተደነገገ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

29. ጡዋፈል ኢፋዷን ከመካ እስከሚወጣበት ጊዜ ድረስ ቢያዘገየው ከመሰናበቻው ጡዋፍ ያብቃቃዋል፤ እንዲሁም ጡዋፈል ኢፋዷ በ ……………… እና በ ………………. ካልሆነ በቀር ልክ እንደ የዑምራው ጡዋፍ ነው።

30. ቂራን የሚያደርግና ሙፍሪድ ……… ሰዕይ የሚያደርጉ ሲሆን ሙተመቲዕ ደግሞ ……….. ነው ሰዕይ የሚያደርገው።

31. የተከታዮቹን ድርጊቶች ኢስላማዊ ብይን አስቀምጥ:

| ድርጊት | ብይኑ |
|---|---|
| ንኡሱ ሓጅ [ዑምራ] | |
| መሕረም የሌላት ሴት ሓጅ ብታደርግ | |
| እዳ እያለበት ሓጅ ቢያደርግ | |

# አስራ አምስተኛው ትምህርት

## ለሁሉም ሙስሊም የተደነገጉ በሆኑ ስነምግባር ማጌጥ

ከነዚህም: እውነተኝነት፣ አደራ መጠበቅ፣ ጥብቅነት፣ አይነ አፋርነት፣ ጀግንነት፣ ቸርነት፣ ቃልን መጠበቅ፣ አሏህ ሓራም ካደረገው ነገር ሁሉ መጥራት፣ መልካም ጉርብትና፣ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው በተቻለ መጠን መርዳት እና ከነዚህም ውጭ ያሉ ቁርአንና ሓዲሥ ጥቆማ የሰጠባቸውን መልካም ስነምግባሮች ሁሉ።

## አሳሳቢ ማስታወሻዎች

- (እውነተኝነት) ከአሏህ ጋ በቃልም፣ በድርጊትም በእምነትም ደረጃ ታማኝ ሆኖ መገኘት፤ ከአሏህ ባርያዎችም ጋ ታማኝ ሆኖ መገኘት፤ የዚህ ተቃራኒ ውሸት ነው።
- (አደራ መጠበቅ) የሰው ልጅ የተሸከማት የሆነች ታላቅ ሃላፊነት ነች፤ የኺያና (ማበል) ተቃራኒ ነች።
-(ጥብቅነት) ያም ከሓራም መታቀብ ማለት ነው።
- (አይነ አፋርነት) መልካምን ለመስራት የሚያነሳሳና ፀያፍን ከማድረግ የሚያቅብ ባህሪ ነው።
- (መልካም ጉርብትና) ይህ ግድ ከሚያደርጋቸው ነገሮች መካከል አይንን ሰበር ማድረግ፣ የጎረቤትን ነውር አለመከታተል ተጠቃሾች ናቸው።
- (እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው መርዳት) ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል: **"በዱንያ ከአንድ አማኝ አንድ ችግሩን ያቃለለ አሏህ ከሱ የአኼራ ችግሮች አንድ ችግሩን ያቃልልለታል፤ ለተጨናነቀ ያግራራ አሏህ በዱንያም በአኼራም ያገራለታል፤ የአንድን ሙስሊም ነውር የሸፈነ አሏህ በዱንያም በአኼራም ነውሩን ይሸፍንለታል፤ የአሏህ ባርያ ወንድሙን በመርዳት ላይ እስከሆነ ድረስ አሏህም እሱኑ በመርዳት ላይ ነው።"** ሙስሊም ዘግበውታል

# አስራ ስድስተኛው ትምህርት

## ኢስላማዊ ስርአቶችን መላበስ

ከነዚህም: ሰላምታ መስጠት፤ ፈገግታ፤ በቀኝ እጅ መብላትና መጠጣት፤ ሲጀምሩ በአሏህ ስም ይሁን፤ በልተው ሲያጠናቅቁ በማመስገን ይሁን፤ ሲያስነጥሱ ማመስገን፤ አስነጥሶ አሏህን ያመሰገነን አሏህ ያዝንለት ዘንድ አሏህን መለመን፤ ህመምተኛን መጠየቅ፤ ሶላተል ጀናዛን ለመስገድ መከተልና መቅበር፤ መስጅድም ቤትም ሲገባም ሲወጣም ያሉ ሸሪዓዊ ስርአቶችን መጠበቅ፤ ጉዞ በሚወጣበት ጊዜ ያሉ አዳቦችን መጠበቅ፤ ከወላጆችም ጋ፣ ከቤተ ዘመድም ጋ፣ ከጎረቤቶችም ጋ፣ ከትልቁም ከትንሹም ጋ ስርአትን መላበስ፤ የተወለደለትን የእንኳን ደስ ያለህ ምኞትን መግለፅ፤ ያገባን ከአሏህ በኩል በረካ እንዲያገኝበት አሏህን መማፀን፤ ሃዘን ላይ ያለን ማፅናናት እና ሌሎችም ኢስላማዊ የሆኑ በመልበስም በማውለቅም ጊዜ ያሉ በመጫማትም ያሉ ስርአቶችን ሁሉ መጠበቅ።

### አሳሳቢ ማስታወሻዎች

"ሰላምታ መስጠት" ሲባል መለዋወጥ ለማለት ነው። የተሟላ የሆነው: "አሰላሙ ዓለይኩም ወረሕመቱሏሂ ወበረካቱሀ" የሚለው ሲሆን ለምታውቀውም ለማታውቀውም ሰላምታን ትሰጣለህ፤ ሰላምታን ለሰጠውም ሁሉ ትመልስለታለህ።

"በቀኝ እጅ መብላትና መጠጣት" የተባለው ግዴታ ሲሆን፤ በሶስት ጣት ቢሆንና በቀኝ እጅ መስጠትና መቀበሉ ደግሞ የሚበረታታ ነው።

"ሲጀምር በአሏህ ስም ይሁን" ሲባል "ቢስሚላህ" ይበል ለማለት ነው።

"ሲያጠናቅቅ ማመስገኑ" ሲባል ከነብዩ ﷺ በመጣው መልኩ "አልሓምዱ ሊላሂ ል-ለዚ አጥዓመኒ ወረዘቀኒሂ ሚን ገይሪ ሓውሊን ሚኒ ወላ ቁዋህ" ትርጉሙም "የኔ ሃይልም ብልሃትም ሳይታከልበት ይህንን ላበላኝና ላጠጣኝ አሏህ ምስጋና ይገባው"

-ከፊት ለፊቱ ባለው ሊበላና ምግቡንም ላያነውር የተደነገገ ነው።

ሲያስነጥሱ አሏህን ማመስገን ሲባል “አልሓምዱ ሊላህ” ይበል ለማለት ነው። አስነጥሶ አሏህን ያመሰገነን አሏህ ያዝንለት ዘንድ አሏህን መለመን ሲባል “የርሓመከሏህ” ይበለው ለማለት ነው። ከዚያም ያስነጠሰው “የህዲኩሙሏሁ ወዩስሊሑ ባለኩም” ብሎ ይመልስ።
ህመምተኛንም ይጠይቅ ሲባል ይጠይቀው፤ አሞቾ በሆነ አጋጣሚ እየተመላለሰ ዚያራውንም ያብዛ፤ ሂዶ ግን ቆይታውን አያርዝመው ከአሏህም እዝነት ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ውስጥ እንዲገባም አያድርገው።
ሶላተል ጀናዛን ለመስገድ መከተልና መቅበር ሲባል ወንዶችን ነው እንጅ ሴቶችን አይመለከትም።
መስጅድም ቤትም ሲገባም ሲወጣም ያሉ ሸሪዓዊ ስርአቶችን መጠበቅ ሲባል መስጅድ ሲገባ ቀኝ እግሩን አስቀድሞ ሊገባና እንዲህም ሊል ነው፡ “ቢስሚላሂ ወሶላቱ ወሰላሙ ዓላ ረሱሊላሂ አሏሁመፍተሕሊ አብዋበ ራሕመቲክ” ትርጉሙም “በአሏህ ስም! ሶላትና ሰላምም በአሏህ መልእክተኛ ላይ ይስፈን፤ አሏህ ሆይ! የእዝነት በሮችህን ክፈትልኝ።” ከዛ በሚወጣበት ጊዜ ደግሞ ግራ እግሩን በማስቀደም እዲህ ይበል፡ “ቢስሚላሂ ወሶላቱ ወሰላሙ ዓላ ረሱሊላሂ አሏሁመ ኢኒ አስአሉከ ሚን ፈድሊክ” ትርጉሙም “በአሏህ ስም! ሶላትና ሰላምም በአሏህ መልእክተኛ ላይ ይስፈን፤ አሏህ ሆይ! ከችሮታህ እለምንሃለሁ።” ቤትን በማስመልከት ደግሞ ሲገባም ሲወጣም በቀኝ እግሩ ሲሆን ሲወጣ እንዲህ ይላል፡ “ቢስሚላሂ ተወከልቱ ዓለሏሂ ወላ ሓውላ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላህ አሏሁመ ኢኒ አዑዙቢከ አን አዲለ አው ኡዶለ አው አዚለ አው ኡዘለ አው አዝሊመ አው ኡዝለመ አው አጅሂለ አው ዩጅሀለ ዓለየ” ትርጉሙም “በአሏህ ስም፤ በአሏህም እመካለሁ፤ በአሏህ እንጅ ሃይልም ብልሃትም ያለው የለም፤ አሏህ ሆይ! በሌሎች ምክንያት ከመጥመምም ሆነ በኔው ምክንያት ሌሎች ከመጥመማቸውም ባንተው እጠበቃለሁ፤ ወይም ከመንዳለጥም ሌሎችን ከማንዳለጥም፤ ሌሎችን ከመበደልም በሌሎች ከመበደልም፤ ከመጃጃልም ሌሎች በኔ ከመጃጃላቸውም ባንተው እጠበቃለሁ።” ሲገባ ደግሞ እንዲህ ይበል “አሏሁመ ኢኒ አስአሉከ ኸይረል መውሊጂ ወኸይረል መኽረጂ ቢስሚላሂ ወለጅና ወቢስሚላሂ ኸረጅና ወዓለሏሂ ረበና ተወከልና” ትርጉሙም “አሏህ ሆይ! ሰላማዊ መግባትንና ሰላማዊ መውጣትን እለምንሃለሁ፤ በአሏህ ስም ገባን በአሏህም ስም ወጣን፤ በጌታችን አሏህም ተመካን።” በማለት ቤት ውስጥ ላሉት ሰላምታን ይሰጣል።
ያገባን ከአሏህ በኩል በረካ እንዲያገኝበት አሏህን መማፀን ሲባል “ባረከሏሁ ለኩማ ወባረከ ዓለይኩማ ወጀመዓ በይነኩማ ፊ ኸይር” ብሎ ማለት ነው።
ሃዘን ላይ ያለን ማፅናናት ሲባል በሶስት ቀን ገደብ ነው፤ ከዛ መጨመር አይገባም።

# አስራ ሰባተኛው ትምህርት

## ከሽርክና ከመሳሰሉት ወንጀሎች ማስጠንቀቅ

ከሽርክና ከመሳሰሉት ወንጀሎች መራቅና ማስጠንቀቅ
ከነዚህም: ሰባቱ አውዳሚና አጥፊ ወንጀሎች ይገኙበታል። እነዚህም: በአሏህ ማጋራት፣ ድግምት፣ ተገቢ በሆነ ሸሪዓዊ ምክንያት ካልሆነ በቀር አሏህ ክብር ያደረጋትን ነፍስ ማጥፋት፣ ወለድ መብላት፣ የየቲምን ገንዘብ መብላት፣ በፍልሚያ ጊዜ ማፈግፈግ፣ ጥብቅ የሆነችን ዝንጉ ሴትን ስም በዝሙት ማጠልሸት።
ከነዚህም: ወላጆችን መጨቆን፣ ዝምድናን መቁረጥ፣ የውሸት ምስክርነት፣ የውሸት መሃላ፣ ጎረቤትን ማስቸገር፣ ከደም መቃባት ጋ በተያያዘ፣ ከገንዘብ ጋ፣ ከክብር ጋ በተያያዘ ሰዎችን መበደል፤ አስካሪ መጠጥ፣ ቁማር መጫወት፣ ሃሜት፣ ነገር ማዋሰድ፣ ከዚህም ውጭ አሏህ ወይም መልዕክተኛው ﷺ የከለከሏቸው ነገሮች ሁሉ።

## አሳሳቢ ማስታወሻዎች

“ሽርክ” ሲባል ትልቁንም ትንሹንም ሽርክ የሚያጠቃልል ነው።
“ድግምት” ሲባል እንደመስተፋቅር እና መስተፃርር መሰልንም የሚያካትት ሲሆን ያንን ያደረገ ወይም ያንኑ የወደደ ካፊር ይሆናል። ወደነሱ መሄድም ይሁን ድረገፃቸውን መጎብኘት የተከለከለ ነው። እንዲሁም የድግምት ጣብያዎችን መከታተልም ሆነ ጥንቆላዎቻቸውን የሚለቁባቸውን መፅሄቶችንና ጋዜጦቻቸውን ማንበብም የተከለከለ ነው። ድግምትን በድግምት ለመፍታት መጣርም ተገቢ አይደለም። ይልቅ ሸሪዓዊ በሆነ ሩቃ እና በዱዓእ እንዲሁም ዋግምትን በመሰሉ የተፈቀዱ በሆኑ ህክምናዎች ይፈወሳል እንጅ።

"ተገቢ በሆነ ሸሪዓዊ ምክንያት ካልሆነ በቀር አሏህ ክብር ያደረጋትን ነፍስ ማጥፋት" ተገቢ በሆነ ሲባል ከሶስቱ አንዱን ለማለት ነው: እነሱም "ነፍስ ላጠፋ ነፍሱ ይጠፋል፤ አግብቶ የሚያውቅ ዝሙት ሲፈፅም፤ ዲኑን ትቶ ከሙስሊሞች ስብስብ የተገነጠለ"። ናቸው።

"የቲም" ሲባል ለአቅመ አዳም ከመድረሱ በፊት አባቱ የሞተበት ማለት ነው።

"በፍልሚያ ጊዜ ማፈግፈግ" ሲባል በአሏህ መንገድ ለመታገል የዘመቱትን ለማለት ነው።

"ጥብቅ የሆነችን ዝንጉ ሴትን ስም በዝሙት ማጠልሸት" ሲባል ጨዋ ሴቶችን ለማለት እንጅ ያገቡትን ብሎ ለመነጠል አይደለም የተፈለገበት።

"የውሸት መሃላ" ስንል ከአሏህ ውጭ ባሉት መማለንም ያጠቃልላል፤ ልክ በነብዩ ﷺ መማል፤ ወይም በክብራቸው ወይንም በህይወታቸው ወይንም በጥበቃቸው ወይንም በመሳሰሉት መማልንም ያጠቃልላል።

"ቁማር መጫወት" ሲባል ማሸነፍና መሸነፍ ያለበትን ጨዋታ ሁሉ እንደሎተሪ ያለውንም ጭምር

"ሃሜት" ሲባል ነብዩ ﷺ በዚህ መልኩ ገልፀውታል "ወንድምህ በሚጠላው መልኩ ማውሳትህ ነው"

"ነገር ማዋሰድ" ሲባል በሰዎች መካከል ወሬ ማመላለስ ማለት ነው

## የአስራ ሰባተኛው ትምህርት ማብራርያ

### የውድድሮችና ፉክክሮች ብይን

ከማስያዣ ጋ የሚፈቀድ:
የፈረስ፣ የግመል፣ የቀስት ውርወራ ውድድር፤ ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋልና:
**“በቀስት፣ በግመል ውድድርና በፈረስ ውድድር ካልሆነ በቀር ማስያዝ መወዳደር አይቻልም”**

ሙሉ በሙሉ ሓራም የሆነ:
ነርድ (ዳይስ መሰል ጨዋታ) ቼዝ እና መሰል ጨዋታዎች

አስይዘህ ከሆነ የተከለከለ ሳታስይዝ ግን የተፈቀደ:
ከተጠቀሱት ውጭ ያሉት ጨዋታዎች ሁሉ።

አስራ ስምንተኛው ትምህርት

## ሙትን መገነዝና በሱም ላይ መስገድ እና መቅበር

የዚህ ማብራርያው እንደሚከተለው ነው:

**በመጀመርያ**: ሞት አፋፍ ላይ ያለን “ላ ኢላሃ ኢለሏህ” እንዲል ቃሉን ማስያዝ፤ ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋልና **“ሙታኖቻችሁን ላ ኢላሃ ኢለሏህ አስይዟቸው”** “ሙታኖቻችሁን” ሲባል ሞት አፋፍ ላይ የተጣዱትን እነኝህም የሞት ምልክት ጎልቶ የሚታይባቸው የሆኑት ናቸው።

**ሁለተኛ**: መሞቱ ከተረጋገጠ አይኖቹ እንዲጨፈኑ ይደረግና ፂሙም ይቋጠራል፤ ከነብዩ ﷺ የመጣው ሱና ይህን የሚያመልክት ነውና።

**ሶስተኛ**: የሙስሊም ሬሳ ከሆነ ማጠቡ ግዴታ ነው። ምናልባት መስዋእት ሆኖ በጦር መስክ ሸሂድ የሆነ ካልሆነ በቀር፤ ይህ አይታጠብምም አይሰገድበትምም ይልቅ ከነልብሱ ነው የሚቀበረው። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ የኡሑድ ዘመቻ ሸሂዶችን አልሰገዱባቸው አላሳጠቧቸውምና።

**አራተኛ**: የሙት አተጣጠብ ሁኔታው: ሃፍረተ ገላው ይሸፈናል፤ ከዚያም ከፍ ተደርጎ ይያዝና ከሆዱ በኩል ለስለስ ባለ መልኩ ጫን ይደረጋል፤ ከዚያም አጣቢው/ዋ እጅ ላይ ብጣሽ ጨርቅ ነገር ይጠቀለልና በዚያው ያሸዋል። ከዚያም ሬሳውን የሶላት ውዱእ እንደሚደረገው ውዱእ ያስደርገዋል፤ ከዚያም የሙቱን ጭንቅላትና ፂም በውኃና በቁርቁራ ዛፍ ወይም መሰል ነገር አድርጎ ያጥበዋል፤ ከዚያም በቀኙ በኩል ካጠበ በኋላ በግራው በኩል ያጥበዋል፤ ከዚያም ለሁለተኛና ለሶስተኛም ጊዜ እንዲሁ አድርጎ ያጠበዋል፤ በሆዱ አካባቢ ባጣበው ቁጥር ከስር አንዳች ነገር የሚወጣው ከሆነ አፅጅው በታውንም በጥጥ ነገር ይዝጋው፤ አሁንም አላቆም ካለ ግን በአንዳች አፈር ነገር ወይም ዘመን አመጣሽ በሆነ ህክምናዊ ስሪት፤ ማለት እንደፕላስቲክና መሰል በሆነ ነገር ይዝጋው።

ውዱኡም ይደገምለት፤ ሶስቴ በቂ ሆኖ ካልተገኘ ወደ አምስቴ ወይንም ወደሰባት ጨመር ተደርጎ ይታጠብ። ከዚያም በልብስ ነገር ያደራርቁት። በየመገጣጠሚያዎቹም ላይ፣ (ማለትም በብብቶቹ እና በታፋው ውስጥ) በሱጁድ አካላቶቹ፣ ከተቻለ ደግሞ መላ አካላቱንም ሽቶ ቢቀባው መልካም ነው። ከፈኑም በዕጣን ነገር ማጠን፤ ቀድሞ ቀመሱ ወይንም ጥፍሩ የረዛዘሙ ከሆኑ ይቀነጠባል። ቢተወውም ግን ችግር የለውም። ፀጉሩ መወገድ አይኖርበትም፤ ሃፍረተ ገላው አይላጭም፤ (ያልተገረዘ ከነበረ) አይገረዝም ምክንያቱም ይህን የሚያመላክት ማስረጃ የለምና፤ ሴት ከሆነች ደግሞ ፀጉሯ ሶስት ጉንጉን ተደርጎ በጀርባዋ ይለቀቃል።

**<u>አምስተኛ</u>**: ሙትን መከፈን: ለወንድ በላጭ የሚሆነው ልክ ነብዩ ﷺ ላይ እንደተደረገው ቀሚስና ዒማማ (ጥምጣም) ሳይታከልበት በሶስት ነጫጭ ልብስ ተደርጎ መከፈኑ ሲሆን ታዳጊ ሴት ልጅ ደግሞ በቀሚስና በሁለት ፎጣ ተደርጋ ነው የምትከፈነው።

በሁሉም ላይ ግዴታ የሆነው መላ ሰውነትን የሚሸፍን አንድ ልብስ ነው። ሟቹ በሓጅ ስርአት ኢሕራም ላይ ያለ ከሆነ በውሃና በቁርቁራ ዛፍ ይታጠብና በሽርጡና በፎጣው ወይም መሰል በሆነ ነገር ይከፈናል። ራሱና ፊቱ ግን አይሸፈንም፤ ሽቶም አይቀባም ምክንያቱም የውመል ቂያማ ተልቢያውን እያለ ነውና የሚቀሰቀሰው። ልክ ከነብዩ ﷺ ሶሒሕ በሆነ ሓዲሥ እንደመጣው።

በሓጅ ኢሕራም እያለች የሞተችዋ ሴት ከሆነች ግን የምትከፈነው እንደሌሎቹ ሴቶች ነው። ነገር ግን ሽቶ አትቀባም፤ ፊቷንም በኒቃብ እጆቿንም በጓንት አትሸፈንም፤ ነገር ግን ፊቷንም ሆነ እጆቿን በተጠቀለለችበት ከፈን ነው የምትሸፈነው። የሴትን ልጅ አከፋፈን ሁኔታን በማስመልከት ቀደም ብለን ባብራራነው መልኩ ማለት ነው።

**ስድስተኛ**: ከማንም በበለጠ ለመገነዝ ተገቢ የሚሆነው አደራ የተጣለበት ሲሆን ከዚያም አባት፤ ከዚያም አያት፤ ከዚያም ካለው የዝምድና ቅርበት አኳያ እየታየ ይሆናል። ይህ ወንድን በማስመልከት ነው።

ሴትን በማስመልከት ደግሞ ከማንም ይበልጥ ተገቢ የምትሆነው ሟቿ አደራ የጣለችባት ስትሆን ከዚያም እናት፤ ከዚያም ሴት አያቷ ከዚያም ካላት የዝምድና ቅርበት አኳያ እየታየ ይበልጥ በዝምድና የምትቀርባት ሴት ትገንዛታለች። የትዳር አጋሮች ደግሞ እርስ በራሳቸው ይተጣጠባሉ። ምክንያቱም አቡበክር ሲዲቅን ያጠበቻቸው ባለቤታቸው ነችና፤ እንዲሁም ዓልይም ባለቤታቸውን ፋጢማን ያጠቡት ራሳቸው ናቸውና።

**ሰባተኛ**: በሟች ላይ ሶላት መስገድ: "አሏሁ አክበር!" የሚለው አራት ጊዜ ነው። ከመጀመርያው ተክቢራ በኋላ ፋቲሓን (አልሓምዱ) ይቀራል፤ አብሮ አንዷት አጠር ያለች የቁርአን ሱራ ወይንም አንድ ሁለት አንቀፅ ቢያክልባት መልካም ነው። ኢብኑ ዓባስ በዘገበውና ከነብዩ ﷺ ከመጣው ሶሒሕ ሓዲሥ አንፃር፤ ከዚያም በነብዩ ﷺ ላይ ልክ ሶላት ላይ እንደሚባለው አድርጎ ሶለዋት ያወርዳል፤ ለሶስተኛ ጊዜ "አሏሁ አክበር!" ካለ በኋላ እንዲህ በማለት ዱዓእ ያድርግ **"አሏሁመ-ግፊር ሊሓይና ወመይቲና፡ ወሻሂዲና ወጋኢቢና፡ ወሶጊሪና ወከቢሪና፡ ወዘከሪና ወኡንሣና፡ አሏሁመ መን አሕየይተሁ ሚና ፈአሕይሂ ዓለል ኢስላም፡ ወመን ተወፈይተሁ ሚና ፈተወፈሁ ዓለል ኢማን፡ አሏሁመ-ግፊር ለሁ ወርሓምሁ ወዓፊሂ፡ ወዕፋ ዓንሁ፡ ወአክሪም ኑዙለሁ፡ ወወሲዕ መድኸለሁ፡ ወግሲልሁ ቢልማኢ ወሠልጂ ወልበረዲ፡ ወነቂሂ ሚነልኸጧያ ከማ ዩነቀ-ሥ-ሠውቡል አብየዱ ሚነደነስ፡ ወአብዲልሁ ኸይረን ሚን ዳሪሂ፡ ወአህለን ኸይረን ሚን አህሊሂ፡ ወአድኺልሁል ጀነተ፡ ወአዒዝሁ ሚን ዓዛቢል ቀብሪ፡ ወዓዛቢ-ን-ናሪ ፡ ወፍሰሕ ለሁ ፊቀብሪሂ፡ ወነዊር ለሁ ፊሂ፡ አሏሁመ ላተሕሪምና አጅረሁ ወላ ቱዲለና ባዕደሁ"** ትርጉሙም፡

ትርጉሙም **"አሏህ ሆይ! ለህያዋኑም ለሙታኑም ምህረትህን ለግስ፤ በቅርብም በሩቁም ላለው፣ ለትልቆቻችንም ለትንሾቻችንም፣ ለወንዶቻችንም ለሴቶቻችንም ምህረትህን ለግስ። አሏህ ሆይ! ከኛ መካከል ህያው ያደረግከውን ኑሮውን በኢስላም አድርግለት፤ ከኛ መካከል ሞት የወሰንክበትን ሞቱን በኢማን አድርግለት፤ አሏህ ሆይ! ምህረትህን ለግሰው፣ እዘንለትም፣ ጠብቀውም፣ ይቅር በለውም፣ መኖርያውንም የተከበረ አድርግለት፣ መግቢያውንም አስፋለት፣ በውኋ በበረዶና በቀዝቃዛ እጠበው፣ ልክ ነጭ ልብስ ከጉድፍ እንደሚፀዳው ሁሉ ከወንጀሉም አፅዳው፤ ከሃገሩ የተሻለ ሃገር፣ ከቤተሰቡ የተሻለ ቤተሰብ ተካለት፤ ጀነትንም አስገባው፣ ከቀብር ቅጣትም ጠብቀው፣ ከእሳት ቅጣትም ጠብቀው፣ ቀብሩንም አስፋለት፣ ውስጡንም አብራለት፣ አሏህ ሆይ! አጅሩንም አትንፈገን ከሱ በኋላም አታጥምመን።"** ከዚያም ለአራተኛ ጊዜ አሏሁ አክበር ካለ በኋላ በቀኙ በኩል ብቻ አንድ ጊዜ በማሰላመት ያጠናቅቃል።

ከእያንዳንዱ ተክቢራ ጋ እጁን ማንሳቱ የሚበረታታ ነው።

ሟች ሴት ከሆነች እንዲህ ነው የሚለው "አሏሁመ-ግፊር ለሃ..." *[ማለትም በዱዓው ወንድ ጠቋሚ የሆነውን መጨረሻቸው "... ሁ" የሚል መቋጫ ያላቸውን ቃላቶች እየቀየረ ሴትን በሚገልፀው "... ሃ" በሚል ይተካዋል እላይ በተጠቀሰው ምሳሌ መሰረት፤ የሚያውቅን ሰው ቢጠይቁ በተሻለ መልኩ ይረዳዎታል]*

ሟቾቹ ሁለት ከሆኑ እንዲህ ነው የሚለው "አሏሁመ-ግፊር ለሁማ... " እያለ ሁለትን ጠቋሚ በሆነ የዓረብኛው ምእላድ ይቀጥላል\

ሟቾቹ ከዚህ በላይ ከሆኑ ደግሞ እንዲህ ነው የሚለው "አሏሁመ-ግፊር ለሁም... " እያለ ብዛትን ጠቋሚ በሆነ የዓረብኛ ምእላድ ነው ዱዓውን የሚያደርገው።

ሟቹ ጨቅላ ህፃን ከሆነ ምህረትን ከመለመን ይልቅ እንዲህ ነው የሚባልለት "አሏሁመ-ጅዓልሁ ፈረጠን ወዙኽረን ሊዋሊደይሂ፡ ወሽፊዐን ሙጃነን፡ አሏሁመ ሠቂል ቢሂ መዋዚነሁማ፡ ወአዕዚም ቢሂ ኡጁረሁማ፡ ወአልሒቅሁ ቢሷሊሒ ሰለፊል ሙእሚኒን፡ ወጅዓልሁ ፊከፋለቲ ኢብራሂም ዓለይሂ-ስሶላቱ ወ-ስ-ሰላም ወቂሂ ቢራሕመቲከ ዓዛበል ጀሒም" ትርጉሙም "አሏህ ሆይ! ለወላጆቹ የሚያሰናዳ እና ድልብ አድርገው፤ ተቀባይነት ያለውም አማላጅ፤ አሏህ ሆይ! በሱ ምክንያትም የወላጆቹን ሚዛን የሚያመዝን፤ በሱ ምክንያትም አጅራቸው ከፍ የሚልላቸው፤ የቀደሙትን ደጋጎችንም የሚቀላቀል አድርገው፤ በኢብራሂም ዓለይሂ ሰላም ስር ከሚሆኑትም አድርገው፤ በእዝነትህም የጀሃነምን እሳት ከምትጠብቃቸውም አድርገው።"

ሱናው ኢማሙ በወንድ ላይ ከሆነ የሚሰገደው በራስጌው ልክ፤ በሴት ላይ ከሆነ የሚሰገደው በስትክክል መሃል ሆኖ መቆሙ ነው። በርከት ያሉ ከሆኑ የሚሰገድባቸው ወንዱ ሟች በኢማሙ በኩል ተደርጎ ሴት ሟች ደግሞ በስተቂብላ መሆን፤ ከነሱ መካከል ጨቅላዎች ካሉ ደግሞ ወደ ቂብላው በኩል ጨቅላ ቀዳሚ ይሆንና ከዚያም ሴት ከሱ ቀጥላ ከዚያም በድጋሚ ጨቅላው ይደረጋል። የወንድ ህፃን ልጅ ራስ በወንድ ራስ በስትክክል ሲሆን የሴት ልጅ አዋቂም ይሁን ህፃን ሽምጥ ደግሞ በወንዱ ራስ እስትክክል ይሆናል። ሰጋጆችም ባጠቃላይ ከኢማሙ በስተጀርባ ይሆናሉ፤ ምናልባት ብቸኛ ሆኖ ከኢማሙ በኋላ ለመቆም ቦታ ያላገኘ ካልሆነ በቀር ይህ በቀኙ በኩል ነው የሚቆመው።

**<u>ስምንተኛ</u>**: የሙት አቀባበር አኳኋን: የሚበረታታው ቀብሩን እስከሽምጥ አካባቢ ድረስ ጥልቅ አድርጎ ከበስተቂብላውም በኩል ወደ ጎን መቆፈር ነው። ሟችም በቀብሩ በተቆፈረለት ላሕድ በቀኙ እንዲተኛ ይደረጋል፤ የከፈኑ ቋጠሮም ይፈታና ግን ሳይወልቅ እንዲሁ ይተዋል። ሟች ሴትም ትሁን ወንድ ፊቱ አይገለጥም። ከዛም ጡብ(ብሎኬት ነገር) ይተከልለትና አፈር እንዳይዘልቅበት ይመረጋል፤ ጡብ ካልተገኘ ጣውላ አልያም ድንጋይ ወይም ደግሞ አፈር ማቀብ የሚችል እስከሆነ ድረስ ሌላ እንጨት ማድረግም ይቻላል። ከዚያም አፈሩ በላዩ ላይ ይለቀቃል፤ የዚህኔ እንዲህ ማለቱ የሚበረታታ ነው። **"ቢስሚላሂ ወዓላ ሚለቲ ረሱሊላሂ"** ትርጉሙም "በአሏህ ስም! በመልዕክተኛውም ጎዳና" ቀብሩም የስንዝርን ያክል ወደላይ ጉብ ይደረጋል። አመቺ ከሆነ ቾካል ነገር በላዩ ላይ ይተከልበትና ወኋም ይርከፈከፍበታል።

ቀባሪዎቹ በቀብሩ ሳሉ ለሟቹ ዱዓእ ቢያደርጉለት የተደነገገ ነው። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ሟችን ቀብረው ካጠናቀቁ በኋላ ቆመው እንዲህ ይሉ ነበርና **"ለወንድማችሁ መሃርታን ለምኑለት፤ ፅናትን ይለግሰው ዘንድም አሏህን ተማፀኑለት፤ ምክንያቱም አሁን መጠየቁ ነውና።"**

**ዘጠነኛ**: ሶላተል ጀናዛ ያልሰገደበትም ካለ ከተቀበረ በኋላም ቢሆን ሊሰግድበት የተደነገገ ነው። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ይህን አድርገዋልና፤ ይሁን እንጅ ይህ የሚሆነው ጊዜው እስከወርና ከወር ባነሰ የጊዜ ገደብ ነው። ጊዜው ከዚህ ካለፈ ግን በሟቹ ላይ መስገዱ የተደነገገ አይደለም። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ሟች ከተቀበረ ወር ከሞላው በኋላ በሟች ላይ ሰግደዋል የሚል የተዘገበ የለምና ነው።

**አስረኛ**: የሟች ቤተሰብ ለእድምተኛው ምግብ ማሰናዳታቸው የተፈቀደ አይደለም። ምክንያቱም ሱሓብዩ ጀሪር ቢን ዓብዲላህ አልበጀሊይ (በሶሓቦች ጊዜ ስለነበረው) እንዲህ ብሏል **“በሟች ቤተሰብ መሰባሰብና ከተቀበረም በኋላ ምግብ ማሰናዳትን ከሙሾ ማውረድ እንቆጥረው ነበር።”** ነገርግን ለራሳቸው አልያም እንግዳ ሆነው ለመጡባቸው መስራታቸው ችግር የለውም። እንዲሁም ዘመድና ጎረቤት ደግሞ ለሟች ቤተሰብ ምግብ መስራታቸው የተደነገገ ነው። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ከሻም በኩል የጃዕፈር ቢን አቢ ጧሊብ መርዶ በመጣላቸው ጊዜ ቤተሰቦቹን ለጃዕፈር ቤተሰቦች ምግብ እንዲያሰናዱ አዘው ነበርና ነው። እንዲህም ብለው ምክንያት አዘል መልዕክትን ተናግረዋል **“... የሚጠምዳቸው ነገር መጥቶባቸዋል ...”** የሟች ቤተሰብም ጎረቤቶቻቸውን ወይም ሌሎችን ጠርተው ከመጣላቸው ምግብ አብረው እንዲቋደሱ ቢያደርጉ ችግር የለውም። እስካሁን በምናውቀው ለዚህ በሸሪዓ የተገደበ ጊዜ እንደሌለው ነው።

**አስራ አንደኛ**: ለሴት ልጅ ከሶስት ቀን በላይ ሃዘን ላይ ሆና ልትቀመጥ የተፈቀደ አይደለም፤ ምናልባት ሟቹ ባሏ ካልሆነ በቀር፤ ሟቹ ባሏ ከሆነ ግን ለአራት ወር ከአስር ቀን ሃዘንተኛ ሆና ልታሳልፍ ግዴታዋ ነው። ምናልባት ነፍሰጡር ከሆነች ግን የሃዘንተኛ ጊዜዋ በወለደችበት ጊዜ የሚነሳ ይሆናል። ይህም ከነብዩ ﷺ ከመጡ የተረጋገጡ ሶሒሕ ሓዲሦች አንፃር ነው።

ወንድ ከሆነ ግን ለዘመድም ይሁን ወይም ለሌላ ለማንም ብሎ ሃዘንተኛ ሆኖ ሊቀመጥ አይፈቀድለትም።

**አስራ ሁለተኛ**: ለወንዶች በየጊዜው እየሄዱ ቀብር እየዘየሩ ለሟችም ዱዓእ አድርገው፤ ምህረትን ከአሏህ ተማፅነው በሞትና ከሞት በኋላ ባለው ሁኔታ ተግሳፅን ቀስመው መምጣታቸው የተደነገገ ነው። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋልና "ቀብርን ዘይሩ ከሞት በኋላ ያለውን ህይወት ታስታውሳችኋለችና።" ባልደረቦቻቸውንም ቀብርን ለመዘየር በሚሄዱበት ጊዜ እንዲህ እንዲሉ ያስተምሯቸው ነበር። **"አሰላሙ ዓለይኩም አህለ ዲያሪ ሚነል ሙእሚኒነ ወልሙስሊሚን ወኢና ኢንሻአሏሁ ቢኩም ላሒቁን ነስአሉሏሃ ለና ወለኩሙል ዓፊያህ የርሓሚላሁል ሙስተቅዲሚነ ሚና ወልሙስታእኺሪን"** ትርጉሙም "እናንተ ከሙእሚንም ከሙስሊምም መካከል የሆናችሁ የቀብር ነዋሪዎች ሆይ! አሏህ ባለው ጊዜ እኛም እናንተኑ የምንቀላቀል ነን፤ ለኛም ለእናንተም አሏህ ይቅር ባይነቱን ይለግስ ዘንድ እንማፀነዋለን፤ ከኛ መካከል ቀዳሚ የሆኑትንም የዘገዩትንም አሏህ መሃርታውን ይለግስ።"

ሴቶች ግን ቀብርን መዘየራቸው ተገቢ አይደለም፤ ምክንያቱም ነብዩ ﷺ **"ሴት የቀብር ዘያሪዎችን ረግመዋል"** እንዲሁም የቀብር ዚያራ ቢያደርጉ ምናልባት የሚፈተኑበት ነገር እና የትእግስት እጦትም ሊኖር ይችላልና።

እንዲሁም ሟች ወደ ቀብር ሲሄድ ጀናዛውን መከተልም አይፈቀድላቸውም፤ ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ከዚህ ከልክለዋቸዋልና። መስጅድ ውስጥ ሆነ አልያም በሌላ ቦታ ሆነው በጀናዛው ላይ መስገድ ግን ለወንዱም ለሴቷም ባጠቃላይ የተፈቀደ ነገር ነው።

መሰብሰቡ የገራልን ይህን ይመስላል፤ ወሶለሏሁ ወሰለመ ዓላ ነብይና ሙሓመዲን ወአሊሂ ወሷሕቢህ

## ቀብርን የመዘየር አይነቶች

**የተደነገገው ዚያራ**

ከሞት በኋላ ስላለው ህይወት አስታውሶ መገሰፅን ሊያቅድ፤ ምንም አይነት ነገር ሳይሰንቅ ሊሆን፤ ለሱም ሆነ ለሌሎች ሟቾች ከነብዩ ﷺ በመጣው መልኩ ዱዓእ ሊያደርግላቸው አቅዶ የተነሳ እና ሸሪዓው የሚቃወመውን አንዳችም ነገር ከማድረግ የሚቆጠብ ከሆነ ነው።

**መጤ የሆነው ዚያራ**

ቀብሩ ላይ ሆኖ አሏህን ለማምለክ አቅዶ የተነሳ እንደሁ ነው።

**ሽርክ ያለበት ዚያራ**

የቀብሩን ባለቤት(ሟቹን) ራሱን ለመለመን አቅዶ የተነሳ እንደሆነ ነው።

# ስለ መገነዝና ስለ ስርአት ፈተና

1. ስርአትና ሸሪዓዊ አደቦችን መጠበቅ ከሙስሊም ባህርያት ናቸው። ( እውነት – ሃሰት )
2. ሃይማኖቴ ከክፎውች ጋ እንድወዳጅና ደጋጎችን እንድርቅ ያዘኛል። ( እውነት – ሃሰት )
3. ኢስላም ከአስተናጋጆችና ከሰራተኞችም ጋ በመልካም መስተጋብር እንድንኗኗር ነው ያስተማረኝ። ( እውነት – ሃሰት )
4. በምላሱም በእጁም ሌሎችን አዛ የሚያደርግን ሰው እወዳጃለሁ። ( እውነት – ሃሰት )
5. የሰደበኝን ሰው መልሸ በመስደቤ ያስደስተኛል። ( እውነት – ሃሰት )
6. የሚያስፈልጋቸውን እና ደካሞችን እንዳግዝ ነው ኢስላም ያስተማረኝ። ( እውነት – ሃሰት )
7. አንድ ሙስሊም በሌላኛው ሙስሊም ላይ ካለው ሓቅ መካከል በታመመ ጊዜ ሊጠይቀውና አሏህ እንዲፈውሰውም ዱዓእ ሊያደርግለት ነው። ( እውነት – ሃሰት )
8. የጎረቤትን ሚስጥር መፈላፈል ከአማኞች ባህሪ ነው። ( እውነት – ሃሰት )
9. አሏህ ዘንድ ከማንም በበለጠ ተወዳጁ ከማንም በላይ ሰዎች ጠቃሚ የሆነው ነው። ( እውነት – ሃሰት )
10. ከቤት ሲወጣ የሚባለው ዚክር እንዲህ ነው "ቢስሚላሂ ወለጅና ወቢስሚላሂ ኸረጅና ወዓላ ረበና ተወከልና" ( እውነት – ሃሰት )
11. ባስነጠስኩ ጊዜ "የርሓመከሏህ" ላለኝ እኔ የምለው "የህዲኩሙሏሁ ወዩስሊሑ ባለኩም" ነው። ( እውነት – ሃሰት)
12. አሏህን ማስታወስ አንድን ሙስሊም ከክፋት ትጠብቀዋለች ወደ አሏህም ታቃርበዋለች። ( እውነት – ሃሰት )
13. ኢስላማዊ ወንድምህን ወይንም እህትሽን የመውደድህ/ሽ ምልክቱ ምንድን ነው?

..............................................................................

14. የኢማንህን መዳከም ከሚያመላክቱ ነገራቶች መካከል ሙስሊም ወንድምህን መመቅኘት ይገኝበታል። ( እውነት – ሃሰት )
15. ሙሓባን የሚያመጡ ሰበቦችን ጥቀስ/ሺ።

    ................................................................................

16. ከሚያሰክሩ ነገራቶች የተከለከለው ኸምር ተብሎ የሚጠራውን ነው። ( እውነት – ሃሰት )
17. በሚጠጡትና በሚበሉበት ላይ መተንፈስ የተወገዘ ነው። ( እውነት – ሃሰት )
18. ምግብ በልተው እጅን ከመታጠብ በፊት ጣትን መላስ የሚበረታታ ነው። (እውነት – ሃሰት)
19. በአመጋገብም ይሁን በመጠጥ እንዲሁም በአለባበስ መካከለኛ መሆን ተፈላጊ አካሄድ ነው። ( እውነት – ሃሰት )
20. ከሰዎች መካከል ጀናዛን ለማጠብ፣ በሱ ላይ ለመስገድና ለመቅበር ይበልጥ ተገቢ የሆኑ በቅድሚያ … … … … … ከዚያም…. … … … … …ከዚያም … … … … … ከዚያም … . … … … … …
21. የሟችን እዳ መክፈል ... … …

    O ግዴታ ነው   O የሚበረታታ ነው   O የተፈቀደ ነው

22. ሟችን መቅበር ብይኑ … … …  O የሚበረታታ ነው   O ግዴታ ነው

    O ፈርዱ ኪፋያ ነው (ማህበራዊ ግዴታ) ነው

23. ሞት አፋፍ ላይ ያለን “ላ ኢላሃ ኢለሏህ” እንዲል ማስደረግ ብይኑ… …  O ግዴታ ነው

    O የሚበረታታ ነው   O የተከለከለ ነው

24. ሙታን በሚታጠቡበት ጊዜ ላያጥቡ ነገር በቦታው መገኘት ብይኑ … ……

    O የተከለከለ ነው   O የተፈቀደ ነው   O የተወገዘ ነው

25. የከፈኑ ቋጠሮ የሚፈታው ሟቹን በቀብሩ ጉድጓድ ካስገቡት በኋላ ነው። ( እውነት – ሃሰት )
26. ባልና ሚስት አንዱ ሌላኛውን አያጥብም፤ ምክንያቱም ኒካሓቸው በሟች ሞት ምክንያት ውድቅ ሆኗልና። ( እውነት – ሃሰት )

27. … … … … ያለውን ወንድም ሴትም ሊያጥቡ ይችላሉ።

28. በሟች ላይ መስገድን ያመለጠው …………. መስገድ ይችላል፤ ይህም የሚሆነው ግን በ…………….. የጊዜ ገደብ ነው።

29. በሟች ላይ ማልቀስ ልቅ በሆነ መልኩ የተፈቀደ ነው። ( እውነት – ሃሰት )

30. ሟች ቀብሩ ውስጥ በተዘጋጀለት ላሕድ ቂብላን ተቅጣጭቶ ነው እንዲጋደም የሚደረገው። ( እውነት – ሃሰት )

# ርእስ ማውጫ

የሸይኹ መግቢያ ማብራሪያ ……………………………………………………….3

የመጀመሪያው ትምህርት: ሱረቱ -ል- ፋቲሓ እና አጫጭር ሱራዎች ……………………4

ከ"ተይሲር አል-ከሪሙ-ር-ሯሕማን ፊ ተፍሲሪ ከላም አል-መናን" የተወሰኑ ቅንጫቢዎች ……6

የመግቢያውና የተፍሲሩ ፈተና ……………………………………………......27

ሁለተኛው ትምህርት-የኢስላም ማእዘናት …………….……………………..…..43

ሶስተኛው ትምህርት: የኢማን ማእዘናት ………………………………………..51

አራተኛው ትምህርት: የተውሒድ አይነቶች እና የሽርክ አይነቶች ………………………..56

አምስተኛው ትምህርት: ኢሕሳን……………………………………………..........…61

ተውሒድ ነክ ፈተና ………………………………………………………...…62

ስድስተኛው ትምህርት: የሶላት ቅድመ መስፈርቶች……………………………….…..67

ሰባተኛው ትምህርት: የሶላት ማእዘናት……………………………………………….71

ስምንተኛው ትምህርት: የሶላት ዋጅቦች(ግዴታዎች) ……………………………...73

ዘጠነኛው ትምህርት: ተሸሁድ (አት-ተሒያቱ) ………………………………..…..74

# ማውጫ


አስረኛው ትምህርት: የሶላት ተጨማሪ ሱናዎች ..........................................75

አስራ አንደኛው ትምህርት: ሶላትን ውድቅ የሚያደርጉ ነገራቶች ............................77

አስፈላጊ ጥቆማዎች ..........................................................................78

የሶላት አሰጋገድ ሁኔታ ስእላዊ ማጠቃለያ..........................................80

ሶላቶች በጥቅሉ.................................................................................90

ስለሶላት ፈተና ...............................................................................93

አስራ ሁለተኛው ትምህርት: የውዱእ ቅድመ ሁኔታዎች..................................98

አስራ ሶስተኛው ትምህርት: የውዱእ ግዴታዎች ........................................100

አስራ አራተኛው ትምህርት: ውዱእ የሚያፈርሱ ነገራቶች...............................101

የውዱእ አደራረግ ሁኔታ ስእላዊ ማጠቃለያ..........................................103

ከንፅህና ጋ ተያያዥ የሆኑ አንዳንድ ነጥቦች...........................................106

ንፅህና ነክ ጥያቄዎች .........................................................................110

ሁለተኛው : ዘካ ...............................................................................113

ዘካ ነክ ጥያቄዎች ...........................................................................118

ሶስተኛ: ፆም.....................................................................................122

ፆም ነክ ጥያቄዎች……………………………………………………..………..129

አራተኛ፡ ሓጅ……………………………………………..……………..…….132

የሓጅና ዑምራ ማብራርያ………………………………………………..…..137

የሓጅ ጥያቄዎች ………………………………………………..………..140

አስራ አምስተኛው ትምህርት፡ በኢስላማዊ ስነምግባር ማጌጥ ……………………..…143

አስራ ስድስተኛው ትምህርት፡ ኢስላማዊ ስርአቶችን መላበስ………..……..……..……144

አስራ ሰባተኛው ትምህርት፡ ከሽርክና ከመሳሰሉት ወንጀሎች ማስጠንቀቅ ……………….146

አስራ ስምንተኛው ትምህርት፡ ሙትን መገነዝ……………………………….…….149

ስለ መገነዝና ስለ ስርአት ፈተና ……………………………………………...157

# ማጣቀሻ መፃህፍት

[1]. ቁርአነል ከሪም

[2] "ተይሲር አል-ከሪሙ-ር-ሯሕማን ፊ ተፍሲሪ ከላም አል-መናን" የታላቁ ሸይኽ ዓብዱ-ር-ራሕማን አስሰዕዲይ

[3]. “ሶሕሕ ቡኻሪይ” የእውቁ ዓሊም ኢማም አቢ ዓብዲላህ ሙሓመድ ቢን ኢስማዒል አልቡኻሪይ

[4]. “ሶሒሕ ሙስሊም” የእውቁ ዓሊም ኢማም አቢል ሑሰይን ሙስሊም ቢን አልሓጃጅ

[5] “ሸርሒል ሙምቲዕ ዓላ ዛዲል ሙስተቅኒዕ” የታላቁ ሸይኽ ኢብኑ ዑሠይሚን

[6]. “አል ቀውሉል ሙፊድ ዓላ ሸርሒ ኪታቡ ተውሒድ” የታላቁ ሸይኽ ኢብኑ ዑሠይሚን አሏህ ሁሉንም መሃርታውን ይለግሳቸውና።